# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው-ሕዝብ
(ወዛደር፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣ ወታደር፣ ምሁር፣)
መብቱና ጥቅም
የሚታገል-ጋዜጣ

ቁ. 67

ሐምሌ 15/1970

## መኢሶን ከህብረቱ ስለመወገዱ

### 1. መግቢያ

ይገርማል! እንዳንዱ ሰዎች ወሮች አለፈው ወሮች ቢተኩ ነገሮችን የመርሳት ዝንባሌ አላቸው:: ነገር ግን ደግሞ፣ ከሁሉም ነገር ይልቅ በቀደሚያ ለመርሳት የሚፈልጉት ራሳቸው ተጠያቂ የሚሆኑባቸውን ጉዳዮች ነው:: ከህሊናቸው ጋር ለማስታረቅ የሚያስቸግሯቸውን ጉዳዮች ነው:: ስለዚህም፣ የማይፈልጉት ምክንያት፣ የማይፈጥሩት ሰበብ፣ ራሳቸውን ለማታለል የማያደርጉት ጥረት የለም:: ጉድጓዳቸን እየቆፈረ ራሳቸውን ለመቅበር፣ ግድፈቶቻን እየገነቡ በበበ ተደርገባቸው ለመሸሸግ፣ በዚህም በዚያም በለዉ ህሊናቸውን "ለማባረር" ... እያሉ አስደናቂ ጥረቶችን ያካያሉ:: አስደናቂ የሆኑ የሴራ አክሮባቶችን ይሠራሉ::

ይሁንና እንደዚህ ያሉት ሰዎች ደግሞ፣ ባንድ ወገን ካለፈው ስህተታቸው ምንም አይማሩም:: በሌላው ወገን ወደሚቀጥለው ከባድ ስህተት በቀላሉ ይገባሉ:: የመወረሻ መወረሻም ወዳቂዎች ናቸው::

በፖለቲካ ድርጅቶችም በኩል እንደዚሁ ነው::

የፖለቲካ ድርጅቶች እውነተኛ ማርክሲስት ሌኒኒስት /ማሌ/ እስከሊሆኑ ድረስ፣ "ኦርግ" የሚገፉት እንደተባሉት ሰዎች ይሆናሉ:: ስለዚህም ቁራኞችን ለይተው በመለስ በመለካቸው አይመለከቱም:: የነገሮችን ምንነት ከሁሉም አንፃር አያጤኑም:: በተቃራኒ፣ ለነርሱ ለጊዜው የሚጠቅሟቸውን ነገሮች በማወባት ብቻ ይወሰናሉ:: የሌላውን ወገን የከርከርና የአቋም ነጥቦች ወይ ፈጽሞ አያቀርቡም ወይ ደግሞ ቀነፅፅለውና አጣመው በማቅረብ መሠረት ሊያገኙቸው ይጥራሉ:: ነገሮችን ይሸፋፍናሉ:: ራሳቸውን በጣም በቀላሉ ያጸድቃሉ:: ሌሎችን በጣም በቀላሉ ይኮንናሉ:: በነባራዊ ሁኔታዎች ላይ ተመርኩዘው፣ ቃተኛ ትንተናዎችን ከማድረግ ይልቅ፣ በሚቶችን በመቀባቀብና በመማጸን ላይ ያተኩራሉ:: በሚቶችን የሚማጸኑ ያሏቀቸንና ሃረጎችን በመደርደር ከእውነት ለማምለጥ ይሞክራሉ:: በተለይ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያዎችንና መድረኮችን እስከያዙ ድረስ ደግሞ፣ ደጋግሞ በመለፈፍ በዚህም በዚያም ማሳመኑ ቀላል ነው ብለው ያምናሉ:: ይህንኑ አድራጎታቸውን ደግሞ ራሳቸው ተመሰበው እንደአብዮታዊ ሥራ፣ እንደአብዮታዊ ድል ይቆጥሩታል:: ይኩራሩበታል:: እስከሚቀጥለው ተርምስ ድረስ እንደዚሁ ይቀጥላል:: ከዚያም እንደዚያው::

ኢማሌድህ፣ "መኢሶን ከኢማሌድህ አባልነት ተሰረዘ" በማለት "ከሕብረተ ድምፅ" /ሕ.ድ ቅ.1 ቁ.4 ሚያዝያ 1970/ ላይ ያወጣውን ጽሑፍ ወሳኙ ሰገመለከት በመጀመሪያ የተገነዘበነው ከዚህ በላይ የተናገርነውን እውነት ነው:: ስለዚህም ነገሮችንና ቁራኞችን ... ወዘተ ተመሰብ በተከበሰ የማስታወስና በተከከለኛ መለኪያቸው የማስቀመጡ ተግባር የኛው ተግባር ሆኗል:: ይህም ጽሑፍ የዚሁ ዝኩር ነው::

ነገር ግን በመቀጠላችን በፊት ደግሞ መኢሶን ዘረም ቢሆን ሃቀኛ፣ ታጋይ፣ አብዮታዊና ዲሞክራሲያዊ የሆነ የተራማጆች ሕብረት እንዲመሠረት የሚጠይቅና ለዚህ የተቀደሰ ተግባር ሳያቋርጥ የሚታገል መሆኑን ደግመን ለናበውቅ እንወዳለን:: በሃቀኛ ተራማጆች መካከል ያሉት ቅራኔዎች ዘረም ቢሆን በወይይትና በዲሞክራሲያዊ ዘዴዎች ሊፈቱ እንደሚችሉ የመኢሶን ጽኑ እምነት መሆኑን በድጋሚ እናስታውቃለን::

መኢሶን በዚህ በኩል ከረጅም ጊዜ ጀምሮ የሚያደርገውን ጥረት በሃቅ እንደሚገፋበት እንደዚሁ በድጋሚ እንገልፃለን:: የተራማጆች በዚህም በዚያምና በሆነው ባልሆነው መካረር ለፀረ አብዮት እንጂ ለአብዮታችን መገፋት እንደማይጠቅም የመኢሶን እምነት ነው:: መኢሶን ከተባለው ወገኑ በኋላ ቢሆን ወይይትን በመጠየቅ ለኢማሌድህ ገለጸ ደብዳቤ እንደፃፈ በተጨማሪ እናስታውቃለን::

መኢሶን ከረጅም ጊዜ ጀምሮና ዛሬም የሚያቀርባቸው ጥያቄዎች ግልጽ ናቸው:: እነርሱም የሚከተሉት ናቸው::

1/ ለውይይት አመቺ የሆኑ ሁኔታዎች ይፈጠሩ፣
2/ ለዚህም የታሠሩት የመኢሶን አባሎች፣ ደጋፊዎችና ወዳጆች ይፈቱ፣

.../2

3/ በመኢሶን ላይ የሚደረገው የገድያ፣ የከተተለና የእሥራት ዘመቻ ይቁም፣
4/ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ይታወቁ፣ ይከበሩ::

መኢሶን ስህተቶች ካሉ፣በበኩሉ በመጀመሪያ በውስጥ ከዚያም በኋላ በይፋ ሂስና ገለፃ ለማድረግ ዝግጁ ነው:: ነገር ግን ለዚህም ቢሆን ምቹ ሁኔታዎች መፈጠር ይቀድማል::

ከገንዘቡም ወደ "ሕብረት ድምፅ" ጋዜጣ እንመለስና ድሕፈገና ውሳኔውን አንድ በአንድ እንመለከት፣ አስተያየታችንን እንገልፀ:: በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በተለይ ካልተመለከተ በስተቀር በርዘቶችና ቀንፎች የኛ ናቸው:: እንደዚሁም በተለይ ካልተመለከተ በስተቀር በቀንፎች ውስጥ የሚገኙት ቁጥሮች /የ"የሕብረት ድምፅ"/ ቁ.1 ቁ.4 መጽሔትን ገጾች የሚያመለከቱ ናቸው::

ግንቦት 15 1970 ተጠናቀር ያለቀ

## 2. ዘመኑ ወሮች — "ከቀይ ታ"እስከ "ውጊኑ"

የኢማሌድህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ገጾች ስናገላብጥ የምናገኘው የመጀመሪያው ጉዳይ፣ በሕብረት ዘመኑ ወሮች ውስጥ ኢማሌድህ በመኢሶን የተገለ በስተ ለውጥ ላይ የወሰዳቸውን ሁለት አቋሞች ነው:: እነርሱም እንደሚመለከተው ተገለጸዋል::

ኢማሌድህ በመጀመሪያ የወሰደው አቋም፣

"መኢሶን ከሌሎች የኢማሌድህ አባል ድርጅቶች ጋር ያሉት ልዩነቶች ሊፈቱ ይችላሉ" /12/ የሚል ነበር::

ኢማሌድህም ለዚህ፣

"ለቀይ ታው ፖሊሲ ምክንያት አለው:: ኢማሌድህ መኢሶን የሠራውን ስህተት አርሞ፣ ካንደለበት አደገና አዝማሚያ ተነስቶ ሕብረቱን ለማጠናከር፣ እስቲቶን ለማራመድ እንደ ድሮ ትግሉን ይቀጥላል የሚል ግምት ስለነበረው ነው:: በኋላ ግን" ይላል ጽሑፉ ቀጠል አድርጉ፣

"ከኋላ ግን መኢሶን አገገገኛ የተመለከቸነት፣ አገዳገኛ ከአድሃሪያን ጋር በተባበር በመተባበር ላይ በመሆኑ፣ በፖለቲካ አቋሙ ወደ ኢሕአፓ እየተጠጋ በመምጣቱ፣ ኢማሌድህ ዛሬ ነገ ብይል ቁርጥ ያለ አቋም መውሰዱን ውጊኑ መስጠት አስፈላጊና ወቅታዊ መሆኑን አምኖበታል" /12/

እንገዲህ መኢሶን በነሐሴ 1969 የትገለ በስተ ለውጥ ካደረገበት ጊዜ ደምሮ ዘመኑ ወሮች አለፈዋል:: በኢማሌድህ "የቀይ ታ ፖሊሲና ዛሬ ነገ የማያስገኝ ወቅታዊ ውጊኑ" መካከል እንደዚሁ ዘመኑ ወሮች አለፈዋል:: ይሁንና ከዚህ በላይ የጠቀስነውን ያነበበ ሰው "ለመሆኑ በመካከሉ ምን ተካሄደ"በማለት ራሱን መጠየቁ አይቀርም:: ይህችን "ከኋላ ግን ..." የተባለችን ነገር ለማወቅ መጓጓትም አይቀርም::

የኢማሌድህን ጽሑፍ ይህንኑ ጥያቄ በመመለስ ይመስላል "ከኋላ ግን..." በማለት ደምሮ ነበር:: ነገር ግን እንገባቡ በጽሑፉ ውስጥ መኢሶን ፣አገዳገደ ተመለከቸ፣ እንገኙ ከአድሃሪያን ጋር ተባባረ፣ ደግሞ በፖለቲካ አቋሞች ወደ ኢሕአፓ የተጠጋ መሆኑን" የሚያስረዳ እንደም ነገር አያገኝም:: አገባቡ ከመሥመር መሥመር ያነባል:: እስከመጨረሻው ድረስ ይወጣዋል::ተመልሶ እንደገና እስከመጨረሻው ድረስ በአርጋታ ያነባል:: ... ወዘተ:: ትርፉ ድካም ይሆናል:: በቻ በመጨረሻው ላይ፣ የውሳኔውን ቁጥር 5 ሲያነብ የሚከተለውን "ነገበ" ያገኛል፣

"ካደረገው ስብፋሪና ፀረ አብዮት ሸሸተ እንደኢሕአፓ ጭለጥ ብሎ ወደ ፀረ አብዮት ካንፕ በመግጉ" /27/

በዚህ "ሸሸተ" በሚባለው ጉዳይ ላይ ዝቅ ብለን እንመለስበታለን:: ይሁንና ከመቀጠላችን በፊት ደግሞ፣ ኢማሌድህ "ከኋላ ግን..." በማለት የደመረውን ነገር በተጨባጭ ማስረጃና ማረጋገጥ ይኖርበታል እንላለን:: በዚህ በኩል በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብና በታሪ ሚደረገው አሰባሰቦቹ፣ የወረወረዎችና የፈጠራ መረጃዎች ተደርድረው ነገሮችን እንገባበና በኩል ግን ለኢማሌድህ ሃቢዊ ከስ የምንጠብቀው ቀጥተኛ መልስ ከዘረው ገለጸ መሆኑን ለናሰውቅ እንወዳለን::

መኢሶንን በሚመለከት ኢማሌድህ የሚገኘበት ገለጸ ችግር ቢኖር፣ ኢማሌድህ መኢሶንን በፖለቲካ መሥመርና በርዕዮተዓለም ጥያቄዎች ላይ በሃቀና በዲሞክራሲያዊ መንገዶች ተከራክሮ ለመርታት አለመቻሉ ነው:: የመኢሶንንም የፖለቲካ መሥመር ከሰፊው ሕዝብ ውስጥ "ታገሉ" ለማውጣት አለመቻሉ ነው:: በለዚህም ኢማሌድህ መኢሶንን ለመምታት ያገኘው "ቀላል" መንገድ መኢሶንን "እንደ ኢሕአፓ" ማድረግ በቻ የሚለው ነው:: ዘመኑ ወሮች ሙሉ "ቀን

.../3



መንገደና" ቢል "ፈርጣጭ" ቢል የሚሰማው፣ የሚያምነውና የሚያጣምጠው አጥቷል::መኢሶን ወጣው አልቻለም:: ችግሩ ይህ ነው:: ደግሞ ከሁሉም የሚያስገርመው ነገር፣ ይልቁኑ ኢማሌድህ"ከፖለቲካ" በቻ ባይሆን በድርጅታዊ ሥራዎች ጭምር "ወደ ኢሕአፓ እየተጠጋ በመምጣቱ" አያሌ መረጃዎችእየተገኙ ናቸው:: ለዚህም፣ በኢማሌድህ አባል ድርጅቶች ውስጥ ተሰገሰገው የሚገኙትን /የቀደሞ/ የኢሕአፓ አባሎች ልናስታውስ እንችላለን :: በኢማሌድህ ዘባዊ ድርጅቶች ውስጥ በማገስራራት ላይ መገኘታቸውን ለገጠቀስ እንችላለን:: ... ወዘተ

ለማገናወም እና ደግሞ "ለመሆኑ በመካከሉ ምን ተካሄደ?" የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እንሞክር:: ኢማሌድህም ሆነ የሃቀና ተራማጆችን ሕብረት በሚመለከት የመኢሶንን አቋምና የወሰዳቸውን እርምጃዎች እናስታውቃ:: የአንድ የፖለቲካ ድርጅት አቋም የሚገለጸው መቼም በለሳኑ አማካኝነት ነውና፣ እሱን በመጥቀስ እንደምራለን:: አንባቢያች ቁኖችንና ወቀቶችን ልብ ብለው እንዲያገናዝቡ እናስታውሳለን::

<u>ሰሕድ 61/ ነሐሴ 1969</u>

"መኢሶን አሁንም ቢሆን የተራማጆችን ሕብረት በጥብቅ ይፈልጋል:: ነገር ግን ከበረት የጠነከረ ህብረት ሊፈጠር የሚችለው ከእድርባይነት፣ ለሥልጣን፣ ለቡታና ለስም ከመስገብገብ ይልቁንም ደግሞ ሰፊውን ሕዝብ ከመፍራት ነፃ ሆነን፣ በሃቀና በዲሞክራሲያዊ ስነስርዓት በሰፊው ሕዝብ ፊት ስንገናኝ ነው:: ...እውነተኛ ህብረት ለመፍጠር ከተፈለገ በልዩነት ነጥቦች ላይ ሁሉ፣ የየድርጅቶች አባሎች በሙሉና ሰፊው ሕዝብም ምንም ዓይነት ተፅእኖ የሌለባቸው ዲሞክራሲያዊ ውይይቶችን ለማካሄድ መቻል አለባቸው::"

<u>ሰሕድ ልዩ እትም/7.1.70</u>

"የተራማጆችን ሕብረት በሚመለከተው በኩል፣ <u>መኢሶን አሁንም ቢሆን የሃቀና ተራማጆችን ህብረት ይፈልጋል</u>:: ግን ከዚህ በፊት እንደነበረው፣ በወረቀት ላይ ህብረት፣ በተግባር ሽኩቻ ለኢትዮጵያ አብዮት አይጠቅምም:: እነ እንዲ እንዲህ ናቸው: እንደዚያ ያደርጋሉ ማለትን ተተን በሚያስማሙንና በሚለያዩን <u>መሠረታዊ ነጥቦች ላይ እንወያይ</u>:: ለዐውነተኛ ውይይት ዲሞክራሲያዊ ውይይት በቻ ባይሆን፣ ሃቅም ያስፈልጋል::... ፀረ መኢሶን ዘመቻ የያዙ ድርጅቶችም የደብብቀጠ ዉዋታውን ወደጉን ይተውና <u>በሃቅ እንወያይ</u>::"

<u>ሰሕድ 62/25.1.70</u>

"የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ በእስቸኳይ መለቀቅ፣ በአብዮቱ ሰፈር ለሚገኙት ብዙ ችግሮች መፍትሄ ይሰጣል::

"1. ... በአብዮቱ ሰፈር የተሰለፉት ልዩ ልዩ ኃይሎች በመካከላቸው ያለውን ገንኙነት በየወቅቱ ለማስተካከልና ያሉትንና ሊነሱ የሚችሉትን ልዩነቶች ለማቻቻል ያስችላቸዋል:: በትግልም ውስጥ የሚገጥሟቸውን የጋራ ችግሮች ለመፍታትና ለማስወገድ <u>ለውይይት የሚያስችላቸውን ዲሞክራሲያዊ መድረክ ይከፍትላቸዋል</u>::"

"2. <u>የተራማጆችን ህብረት እውነተኛ ያደርገዋል</u>:: በተግባር የሚተረጎምበትን ሁኔታ በጣም ያፋጥነዋል:: የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አለመለቀቅን ተገን አድርገው አሉባልታና ሃሜትን የሚነዙትን ለማጋለጥ ያስችላል::"

<u>ሰሕድ 63/17.2.70</u>

"ነፃና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ርዕዮተዓለማዊ ትግሎችን ማካሄድ አብዮታዊ ቱፓሪን ያስፋፋል ወይስ ያፍናል?

አብዮታዊያን ያስፋፋል ይላሉ::

ነፃና ዲሞክራሲያዊ ውይይቶች ቢካሄዱ፣ አድሃሪያች በሰፊው ሕዝብ የነፃ ትግል እየተጋለጡ አይቀሩም፣ ወይገስ እንደዘረው በየስርቻው መሸገው የተሳካን ፀረ አብዮት ያከናውናሉ?

አብዮታዊያን ተጋለጠው ይቀራሉ በማለት ይመልሳሉ::... ወዘተ"

<u>ሰሕድ 64/7.3.70</u>

ይህ "<u>ለሃቀና ተራማጆች የትግል አንድነት ጥሪ</u>" በሚል ርዕስ በ16 ገጾች የታተመው ሰሕድ፣ <u>እንዳል</u> ለውይይት፣ ለሃቀና የተራማጆች ሕብረት፣ ለትግል አንድነት ጥሪ የሚያደርግ ነው:: ለመጥቀስም በገፈለገ ጽሑፉን በሙሉ መጥቀስ ይኖርብናል:: እንዱን እንስቶ እንደናውን ለመተው አይቻልም:: አንባቢያች ሰሕድ 64ን እንደገና ተመልሰው እንዲያጠኑት በቻ ጋበዝን እንመለሳለን::

<u>ሰሕድ 65/21.5.70</u>

"መኢሶን በአገራችን አብዮት አንገብጋቢ ጥያቄዎች ላይ ለትግሉ ይበጃሉ የሚላቸውን አቋሞች ከመስገዘር ተቆጥቦ አያውቅም:: <u>በተራማጆች መካከል ልዩነቶች እንዳሉና እነዚህ ልዩነቶች በውይይት እንዲፈቱ ተደጋጋሚ ጥሪዎችን አድርጓል</u>::

.../4

በሁን ጊዜ ገለጻ አቋም የሌላቸው ወይም ደግሞ ያላቸውን አቋም በይፋ በሕዝብ
ፊት ማብራራት የማይደፍሩ አደርባዮች ያሉትን መሠረታዊ ልዩነቶች በማቃለል የሰው-
ምርት ሃሳብ አብዮታዊ መሥመር ላይ የተገነባ ከኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች
ድርጅቶች ውህደት የሚፈለቅ ከበረት የጠነከረ የወዛደር ፓርቲ ለመመሥረት እስ
ተቃጻለ ለማድረግ ነው::"

ሌሎች ለገጠቀባቸው የምንቸላቸው አያሌ ጽሑፎች አሉ:: ይሁንና በሰሕድ እትሞች ላይ
ብቻ ተወስነን እዚሁ ላይ እናቁም:: ጽሑፉ አለቀጥ አንጓይረዝም በለገም እናስባለን::
በተረፈ ከዚህ በላይ ከጠቀስናቸው ጽሑፎች ብቻ እንኳ፣ የመኢሶን ያለተናወጸ አቋምና
መሥመር ገለጻ ነው:: ገን እንገኚህ፣ በነዚህ ሁሉ ወራቶች ውስጥ ከባድ ጥፋና አያሌ
ገለጸና ስውር ጥቃቶች ቢደርሱብተም ማለተም ጥምር ነው::

ከንገኚህም፣ መኢሶን ወደወሰዳቸው ተጨባጭ እርምጃዎች እንሻገርና ስለነርሱ ደግሞ እን
ናገር::

መኢሶን የትገል ስልት ለውጥ ካደረገም በኋላ ቢሆን፣ ከጊ.ወ.አ. ደርግና ከኢማሌዶህ
ጋር ለመገናኘትና ለመወያየት አያሌ ጥረቶችን አድርጓል:: በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ዝርዝር
ነጥቦችን ለማገባት ባንፈልገም፣ በመኢሶን ቀስቃሽነት በአዲስ አበባ ውስጥ ከሚገኙ አንዳንድ
ወጣት ኢንባሲዎች ደምር እስከ መንግሥታትና የውጭ አገሮች ተራማጅ የፖለቲካ ድርጅቶች ድረስ
ጥሪዎቹውን አሰምተዋል:: በተጨማሪ ውይይቶች እንዲካሄዱ መኢሶን አያሌ ቀጥተኛ እርምጃዎችን
ወስዷል:: የዚህ "ታሪክ" እንደሚከተለው ነው:: ይሁንና፣ ወደ "ታሪኩ" ከመገባታችን
በፊት ደግሞ፣ በተባለው የመኢሶን ጉዱ ላይ እርምጃ እንዳይወሰድበት እንጠይቃለን::

በጥር ወር ውስጥ መኢሶን አንድ አባሉን በመጀመሪያ በኢንፎርማል ደረጃ ውይይት ለይ
ወር የሚቸለበትን መንገዶች እንዲሻ ይመድበዋል:: ጓዱም በዚህ ወር ውስጥ /በ24.5.70/
ከአንድ በአብዮታዊ ሰደድ ድርጅት ውስጥ አነስተኛ ቦታ ካለው ከማይበለ ጓዱ ጋር ይገናኛል::
በተራማጆች መሰባሰብና በውይይት ጉዳይ ላይ የሃሳብ ለውውጥ ያደርጋል:: "መኢሶን አሁንም
ቢሆን አብሮ የመሥራት ፍላጎት እንዳለው" ያስረዳል:: የአብዮታዊው ሰደድ ጓዱም፣ የራሱን
አንዳንድ አስተያየቶች ይሰነዝራል:: በመጨረሻም "የመወሰን መብት እንደሌለውና ጉዳዩን
እንደሚያስተላልፍ" ገለጸለት ይለያያሉ::

በ29.5.70 እነዚሁ ሁለት ጓዶች እንደገና ይገናኛሉ:: የአብዮታዊው ሰደድ ጓዱ
"ከበስተ ሰዎች ጋር መገናኘትንና መወያየትን" ይገልጻል:: እነዚህ ሰዎች "ከታራማጆች
መሰበሰብ ላይ የሚገኛው መሆናቸውንና መኢሶንም ወደሕብረቱ መገባት የሚፈልግ ከሆነ፣ ደስ
የሚሳቸው መሆኑን እንደገለጹ" ያስውቃል:: ይሁን እንጂ፣ "ከበስቱ ሰዎች መካከል፣ ሁለቱ
መኢሶን የተባባተ እርምጃ የወሰደ መሆኑን በሰባኖቹ ላይ እንዲገለጽ እንደጠየቁና አንደኛው
ገን ስህተትን በአመራር ደረጃ ካመነበት ይበቃል የሚል አቋም እንደወሰደ" በተጨማሪ ይገል
ጻል::

በዚህ ጊዜ የመኢሶን ጓዱ "እንደዚህ አይነቶቹን የቅድሚያ ገዴታዎች /ኮንዲሽንስ/
ከመጀመሪያው ማስቀመጥ ችግሮችን እንደሚፈጥር" ያስረዳል:: "በቅድሚያ የተከረረው ቅራኔ
እንዲለዘብ፣ ውይይቶች እንዲካሄዱ፣ የታሠሩት ጓዶች እንዲፈቱ፣ በመኢሶን ላይ የሚደ
ረገው ክትትልና አሰራት እንዲቆም፣ በአጠቃላይ ለውይይት አመቺ የሆኑ ሁኔታዎች እንዲ
ፈጠሩ" ይጠይቃል:: በተጨማሪ "ህገን" በሚመለከተው በኩል፣ "መኢሶን ስህተቶች ካሉ
እንደማንኛውም ማሌ ድርጅት በመጀመሪያ በውስጥ ከዚያ በኋላ በይፋ ሂስና ገለሂስ እንደ
ሚያደርግ" ያስውቃል:: ከዚህ በኋላ፣ የአብዮታዊው ሰደድ ጓዱ "የታሠሩትን የመፍታቱ
ጉዳይ የደርግ ጉዳይ መሆኑን" ይናገራል::

ሰበተኛው ገገኙነት እጅግ ከፍተኛ በሆነ ደረጃ የተካሄደ ነበር:: መኢሶን በወቅቱ
በወሰደው ገምቶ፣ ይህ ሰበተኛው ገገኙነት ጉዳዩ ወደከፍተኛ ደረጃ እንደ ተሻገረ የሚያመ
ለክት ነበር::

በ21.6.70 ከመኢሶን በኩል ለዚሁ ሥራ ለተመደበው ጓዱ ከከፍተኛ ስፍራ ስለክ
ይደወላል:: ጓዱም ተጠርቶ ወደ ስፍራው ይሄዳል:: በቦዙ አርዕስት ላይ 45 ደቂቃ የፈጀ
ውይይት ያካሂዳል:: ውይይቱ በመጨረሻ ምገም እንኳ ለድጋሚ ገገኙነት ቢቀጠርም፣ አያሌ
ናገሮችን የሚስጥና ለውይይት አመቺ ሁኔታዎች ሊፈጠሩ እንደሚቸሉ የሚያመለክት ነበር::
የመኢሶንም ጓዱ፣ "ድርጅቱ ስህተቶች ካሉ እርማቶችን ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን፣ ነገር ገን
ባለው ተጽእኖ ምክንያት ይህንን ለማድረግ እንኳ አመቺ ሁኔታ እንዳላተገኘ" ያስረዳል::
ከዚሁም በማያያዝ "የታሠሩት ጓዶች እንዲፈቱ፣ በመኢሶን ላይ የሚደረገው ክትትልና አሰራት
እንዲቆም፣ ለውይይት አመቺ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ጠይቀ" ቀጠሮውን በመጠበቅ ይሰናበታል::
ከዚህስ በኋላ?

ከዚህ በኋላ መኢሶን በተባለው ቀጠሮ መሠረት የገገኙነቱን መቀጠል ይጠብቃል:: ነገር
ገን ቀጠሮው ተራዝሞ ይቆያል:: ሆኖም፣ መኢሶን እስከዚሁ ጊዜ ድረስ በተደረጉት ኢንፎ
ርማል ውይይቶች ላይ በመመርኮዝ፣ ውይይቱን ወደፎርማል ደረጃ ለማሳደግ ጥረቶችን ያደርጋል::





ይህንንም ሃሳቡን በ21.7.70 በተጻፈ በአንድ ደብዳቤ አማካኝነት በቀጥታ ያሳውቃል::
በተጨማሪ በዚሁ ወር ውስጥ በአብዮታዊ ሰደድ በኩል ለጊ.ወ.አ. ደርግ በተላለፈ ደብዳቤ
አንደኛ ከስስት - አምስት ተወካዮች የሚገኙበት አንድ የውይይት ኮሚቴ እንዲቋቋም ይጠይ
ቃል:: ሁለተኛ የመኢሶንን ጥያቄዎች ዝርዝር ያስታውቃል:: ሰስተኛ መኢሶን ከመጀመሪያው
የሚቀበላቸውን ነጥቦች ይገልጻል:: በመጨረሻም፣ ውይይቱ ወደፎርማል ደረጃ እንዲሸገር
ሃሳብ ያቀርባል:: በዚህም አቀጣጫ አንዳንድ እርምጃዎችን የወሰደ መሆኑን ያስታውቃል::
... ወዘተ::

እንገኚህ አያሌ ዝርዝር ነገሮችን ወደጉን ትተን፣ መኢሶን በነሐሴ 1969 እና በ
ሚያዝያ 1970 ዓ.ም. መካከል የወሰዳቸው አቋሞችና እርምጃዎች ከዚህ በላይ የተመለከቱት
ነበሩ:: አሁን በሚያዝያ ወር፣ መኢሶን ለውይይት እንዲያመች በማለት "ከጊዜው የኢትዮጵያ
ሁኔታ ላይ ያሉትን አስተያየቶችና አቋሞች" በዝርዝር ጽፎ /ጽሑፉ በሰሕድ 66 ታትሞ
ወቷል/ ለመላክ በመዘጋጀት ላይ እንዳለ፣ ከሌላው መሥመር "ዝሬ ነገ ሳይል ቁርጥ ያለ
አቋም መውሰድና ውሳኔ መስጠት አስፈላጊና ወቅታዊ መሆኑን አምኖበታል" የሚል "ውሳኔ"
ደረሰው:: መኢሶን በዚህ ሰዓት "ዝሬ ነገ የሚያሰኝ" ምን ጉድ ተፈጠረ! "ወቅታዊውን"
ወቅትስ ምን አይነት ታምር ወቅታዊ አደረገው? በማለት ከመጠየቅ በስተቀር የሚጨምርለትን
ነገር አጥቷል!!! የፖለቲካ ድርጅቶች ዘሬም ቢሆን በመኢሶን ላይ ለመወሰንና ለመረባረብ
የሚያደርጉትን ጥረት በመገረም "ጥምር!!!" እየተመለከተው ነው::

ውሳኔውስ ይሁን፣ ይወሰን:: ነገር ገን ኢማሌዶህ ስለ "ቀይ ታው ፖሊሲ" ከተነገረ
አንቀር፣ ከዚህ በላይ ያነሳናቸውን ጉዳዮች ሁሉ የሸፈናቸው ለምንድነው? ይህንን ጉዳይ
በማመለከት፣ 9 ወሮች ሙሉ ምን ሲያደርግ ነበር "የቀየው"? ኢማሌዶህ የመኢሶንን
ተደጋጋሚ ጥያቄዎች እንዲት "ሊረሳቸው" ቻለ? "ከኋላ ገን..." የሚለውን የሚያረጋግጠው
በምንድነው? ወይንስ "መቀየት" የና ፋንታ፣ ውይይትና መሻት የነርሱ በሚል "ዝሬ ነገ
ሳይባል" ከመጀመሪያው ተወስና ነበር? ይህ ከሆነ "ያሉት ልዩነቶች ሊፈቱ ይቸላሉ"፣
ስለዚህም "የቀይ ታን ፖሊሲ" ተከተሉን በማለት የተጻፈው ከማን ፊት ለመመጻደቅ ነው?
ከማን ፊት ለመመጻደቅ ነበር? ኢማሌዶህ መኢሶንን አስመስከቶ እንደጠየቀው ለመጠየቅ ያህል፣
"ለመሆኑ ኢማሌዶህ ማንን ነው የሚሸነገለው? የሚያታልለው? ራሱንና አባላቱን? ኢማሌዶህን?
ወይንስ ሰፊውን ሕዝብ? " /21/

እርገጥ ነው:: እነዚህን የሃቀ ጥያቄዎች በማቅረባችን የበለጠ የጥቅና አመጽ እንዳይ
ወርድብን ደግሞ እናስባለን:: ይሁንና፣ መኢሶን አሁንም ቢሆን በአቋሙ የፀና መሆኑን ደግሞ
እዚሁ ላይ በድጋሚ እናሳውቃለን:: ሃቀኛ ተራማጆች ችገሮቻቸውንና ቅራኔዎቻቸውን በውይይትና
በዲሞክራሲያዊ ዘዴዎች ሊፈቱ ይቸላሉ:: የጊዜው የተራማጆች ቀንና የትገል መሥመር ሃቀኛ፣
ቋሚ አብዮታዊና ዲሞክራሲያዊ የሆነ የተራማጆች ሕብረት እንዲመሠረት መታገል ነው:: መኢሶን
ያሳው ነገር ቢደርስ፣ ከዚህ ቀንና መሥመሩ ዝገፍ አይልም:: ትክክለኛው መሥመር ይህ ብቻ
ነው በሚለው መሥመሩ የጸና ነው::

ሆኖም፣ አመቺ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የሚቸለው ደግሞ ጊ.ወ.አ. ደርግ ነው:: የታሠሩት
የመኢሶን አባሎች ይፈቱ፣ ወዳጆችና ደጋፊዎች ይፈቱ:: በመኢሶን ላይ የሚደረገው የክትትልና
የአሠራት ዘመቻ ይቁም:: መኢሶን ለውይይት፣ ለሂስና ለገለሂስ፣ ለሃቀኛ የተራማጆች ሕብረት
አመቺ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ይጠይቃል::ለዚህም ይታገላል:: ትግሉ ይቀጥላል::

## 3. ስለልዩነት ጥያቄዎች

የኢማሌዶህ ጽሑፍ እንደሚያስረዳው ከሆነ፣ መኢሶን የትገል ስልት ለውጥ ከማድረጉ በፊት
የነበረት የልዩነት ጥያቄዎች ሁለት ናቸው:: እነዚህም የብሄረሰቦችን ጥያቄና የዲሞክ
ራሲ መብቶችን ጥያቄ የሚመለከቱ ነበሩ::

እስከዚህ ድረስ እናም እንስማማለን:: ይሁንና፣ ወደኋላ በአያሌ ጥያቄዎች ላይ ልዩነ
ቶች ተፈጥረው እንደነበረም የሚታወቅ ነው:: ብቻ በነዚህናት ላይ ዝቀ ብለን የምንመለስ
ባቸው ስለሆነ እነሱን ለጊዜው ትተን ወደኢማሌዶህ ጽሑፍ እንመለስ::

ኢማሌዶህ ባነሳቸው የልዩነት ነጥቦች ላይ የጻፋቸውን ሃተታዎች በአንከሮ የተመለከተ
ሰው፣ ከመጀመሪያው የሚያነሳው ጥያቄ "ታዲያ እነዚህ ልዩነቶች ናቸው ወይ?" የሚለውን
ጥያቄ ነው:: በእውነትም ደግሞ የልዩነቶቹ አቀራረብ ጠርቦ ልዩነቶችን የሚያሳይ ፈይደለም::
እንዲያውም በኢማሌዶህ በራሱ አባባል "ስበቦች" ብቻ እንጂ ልዩነቶች የሉም የሚል ነው:: ስለ
ዚህም የኢማሌዶህን ጽሑፍ ከተወጣነው በኋላ፣ እናም ሆነን እንገባቢው፣ መኢሶን የትገል
ስልት ለውጥ እንዲያደርገ የተገደደባቸውን ምክኒያት ሆነ፣ በመኢሶን ላይ ያገን የሚያህል
ውሳኔ ለምን እንደተላለፈ ሳገረን እንቀራለን:: እንዲያው በአጥሩ ሁለቱም ነገሮች የታ
ሪክ አንቀፋቶች መስለው ቀጥ ይላሉ::

ብቻ ነገሮችን ለመሸፋፈን ካለሆነ በስተቀር፣ ለመገላለጥ ከሆነ እንደዚህ በቃላሉ
ለመዝለል የሚቻል አይመስለንም:: እናው ብገቀጥል የተሻለ ነው::

ጸሐፊን ያነበቡት ሰዎች እንደሚረዱት፣ ኢማሌድህ ባነሳቸው ሁለት ጥያቄዎች ላይ ያሉትን ልዩነቶች "አማባየት" የሚፈልገው በድርጅቶቹ የፕሮግራም ነጥቦች ላይ ብቻ በመወሰን ነው:: ስለዚህም ነው ኢማሌድህ ስለልዩነቶች "ሲናገር" እንጓቸም ልዩነቶች አጥቶ ቀዋ የሚለው:: እንዲያውም "ክቦቦች" ብቻ እንጂ፣ የፖለቲካ ልዩነቶች የማይታዩት:: ይሁንና ከመጀመሪያው እንኳ ደግሞ ኢማሌድህ ይህንን አይነትን አቀራረብ መርጦ መነሳቱ በራሱ የሚያስገርም ነገር ነው::

በብሔረሰብ ጥያቄ ላይ ለማተት ሲሞክር፣ በቅድሚያ አምስቱ ድርጅቶች በፕሮግራማቸው ውስጥ ስለዚሁ ጉዳይ ያሰፈሩትን ነጥብ ይጠቅሳል:: ምንም አይነት "የመርህ ልዩነት" ያጣበታል:: ስለዚህም በመጨረሻው ላይ፣ "ይህን ደግሞ" ይልና፣

"ይህን ደግሞ እንደፕሮግራማቸው ከሆነ ሁሉም ውጠውታል:: እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ፣ መኢሶን ልዩነት በመርህ ደረጃም እንደሆነ አድርጎ ያቀርበዋል:: ይህ መቸም አለባይነት ነው:: የኢማሌድህ አባል ድርጅቶች የሚያምኑበትን፣ የሚሉትን፣ እንደማያምኑበት፣ እንደማይሉት አድርጎ የሕዝቡን አስተያየት ለማወናበድ ነው" /16/

በማለት ይደመድማል::

ኢማሌድህ ስለዲሞክራሲ መብቶችም ሲናገር የሚከተለው ይህንኑ መሥመር ነው:: በዚህም በኩል፣

"የያንዳንዱ ድርጅት አቋም /በዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥያቄዎች ላይ — ቀገፍ የሕ.ዱ./ ባጭሩ ከፕሮግራማቸው ላይ በመጥቀስ ማሳየቱ ለአመለካከታችንና ለምንወስደው አጠቃላይ አቋም ይጠቅማል" /18/

በማለት ይጀምርና ይቀጥላል:: በመጨረሻም ሁሉም ፕሮግራም፣

"መሠረታዊ የሕዝብ መብቶች በሚደነግገው "ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ" ውስጥ እንደሚረጋገጡ ይገልጻሉ /ሁሉም ድርጅቶች/... በሕዝባዊ ስርዓት ውስጥ መሆኑን በፕሮግራማቸው አማካኝነት ያረጋግጣሉ" /19/

በማለት ይደመድምና "ልዩነት" ያጣበታል::

በእውነቱ በዚህ በኩል እንዳለነው፣ ይህ ከሆነ መኢሶን ለምን የትግል ስልት ለውጥ እንዳደረገ አንገነዘብም:: በመኢሶን ላይ ያንን የሚያክል "ውሳኔ" ለምን እንደተላለፈም አንረዳም::

ነገር ግን ጸሐፊ ደግሞ ይቀጥላል:: እንደእውነቱ ከሆነ የሚደመደመው፣

"መኢሶንና ኢጭአት ይህንን ሁሉ ይበቱና "የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ለሁሉኑ በአስቸኳይ ይታወጁ" እያሉ ከሰፊው ሕዝብ ዘንድ አደገኛ ውዥንብር መንዛት ጀምረው ነበር:: /ሆኖም ይህ/ መሰሪና ተጥቀ አሰራቸ መፈክር በርዕዮተዓለማዊ ትግል ተሸንፏል:: ተጋልጧል:: ሰፊው ሕዝብ አልተቀበለውም::" /19-20/

በሚል ፍርድ ነው::

መቸም በዚህ በኩል ጠበቃውም ዳኛውም አንዱ አካል እስከሆኑ ድረስ፣ "ይግባኙን" በፅታዊ ትግል አማካኝነት እናመለክታለን ከማለት በስተቀር ሌላ አማራጭ የለንም:: ብቻ በዚሁ ከመቀጠላችን በፊት ደግሞ፣ የመጀመሪያው ሥራችን ስለፕሮግራምና የፖለቲካ አቋም ጥያቄ መናገር ባይሆን አይቀርምና በርሱ እንጀምር:: "በርዕዮተዓለም ትግል ተሸንፏል:: ተጋልጧል:: ሰፊው ሕዝብ አልተቀበለውም" የሚለውን ለራሱ የተሰጠ የስልጣን ፍርድ እስቲ ሰፊው ሕዝብ በዲሞክራሲያዊ መንገድ አቋሙን እንዲገልጽ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለሁሉኑ ይሰጡትና ይታይ ብለን እናልፈዋለን::

## 3.1. የፕሮግራምና የፖለቲካ አቋም ጥያቄ

መቸም ለአንድ የፖለቲካ ድርጅት፣ ፕሮግራምን የማርቀቅ ያህል ከሰማያት በታች የቀለለ ነገር የለም:: ይሁንና አንድን የፖለቲካ ድርጅት ደግሞ ለፕሮግራሙ የመታገልን ያህል ከባድ ፈተና አይገጥመውም:: በተጨማሪ፣ የአንድ ድርጅት ማንነት በፕሮግራሙ ነጥቦች ብቻ የሚገለጽ ቢሆን ኖሮ የርዕዮተዓለም ሆነ የፖለቲካ መሥመር ትግል... ጨርሶ አስፈላጊ ባልሆነ ነበር፣ እንደዚሁም ድርጅቶች በፕሮግራማቸው ላይ አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ነጥቦችን በማስፈራቸው ብቻ የሚተባበሩ ቢሆኑ ኖሮ፣ እንደሕብረትም የቀለለ ነገር ባልኖረ ነበር:: በመጨረሻም፣ ፕሮግራም የሚባለው ነገር ብቻ በቂ ቢሆን ኖሮ፣ ድርጅቶች ልሳኖችን መጽሔቶችን መግለጫዎችን... ወዘተ ለማውጣትና በየጊዜው አቋማቸውን ለመግለጽ ባልተገደዱ ነበር:: ለኛም ቢሆን ይህ አድካሚ ጽሑፍ ወዲያ በቀረልን ነበር::

ነገር ግን ያንዱ የፖለቲካ ድርጅት ፕሮግራም የድርጅቱን ርዕዮተዓለማዊ እምነትና የመደብ አቋም የሚያሳይ፣ ድርጅቱ የሚመራባቸውን መርሆዎች ባጭር ባጭሩ የሚገልጽ፣ የድርጅቱን የቅርብና የሩቅ ጊዜ ዓላማና ግብ የሚዘረዝር አጭር መግለጫ ነው:: የአንድ ድርጅት የድርጊት አጠቃላይ መመሪያ ነው:: ከዚህ ውጪ ሌላ ትርጉም ምንም አይኖረውም::

ይሁንና የአንድ ድርጅት ማንነት ደግሞ በፕሮግራም መግለጫዎች ብቻ አይታወቅም:: አይገለጸም:: የአንድ ድርጅት ማንነት ይልቁኑ የሚታወቀው፣





አንደኛ፣ ድርጅቱ ለፕሮግራሙ ባለው ታማኝነት:: ሁለተኛ፣ ፕሮግራሙን ለማሟላት በሚያካሂደው ፅኑና ቆራጥ ትግል:: ሶስተኛ፣ ከፕሮግራሙ ጋር እንደተዛመደ በየጊዜው በሚነሱት የፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ ሁሉ በሚወስደው የፖለቲካ አቋሙ:: አራተኛ፣ የድርጅቱን የውስጥ የፖለቲካ መሥመርና የርዕዮተዓለም ጥራት ለመጠበቅ በሚያካሂደው ትግል:: አምስተኛ፣ በመደብ ደረጃ ከሚቃረኑትና ከሌሎችም አድርባይና በራዥ ክፍሎች ጋር በሚያካሂደው የፖለቲካ መሥመር፣ የርዕዮተዓለምና ሌሎችም ትግሎች:: ስድስተኛ፣ የድርጅቱን የመደብ መሠረት አጥርቶ ለመጠበቅ በሚያካሂደው ትግል:: ሰባተኛ፣ በጠቅላላ የትግል ዘዴውና ታክቲኩ... ወዘተ ነው::

ፕሮግራም አጠቃላይ መግለጫ፣ አጠቃላይ መመሪያ ነው:: ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ነው:: የፖለቲካ ሁኔታዎች ግን በየጊዜው ይቀያየራሉ:: የፖለቲካ ጥያቄዎች በየጊዜው ይፈልቃሉ:: አንዳንዴም በየዕለቱና በየሰዓቱ ሊሆን ይችላል:: በዚያው ልክ ደግሞ፣ ለአንድ የፖለቲካ ድርጅት በየጊዜው ጥያቄዎች ላይ አቋሙን መግለፅ ግዴታ ነው:: የአንድ የፖለቲካ ድርጅት ማንነትና ምንነት የሚታወቀውም ይልቁኑ በየጊዜው ጥያቄዎች ላይ በሚወስዳቸው አቋሞች ነው::

እነዚህ ሁሉ የፖለቲካ እውቀት ሀሁ ናቸው:: የኢማሌድህ አባል ድርጅቶች እነዚህን ሁሉ የመጀመሪያ ደረጃ ዘርዝሮች ያጤኗቸዋል ብለን አንገምትም:: እኛም የዘረዘርናቸው "ለአስኩባይነት" አይደለም:: ይሁንና፣ እንደምን እንደረሷቸውም ባይደንቀን አልቀረም:: ወይንስ ነጥቦቹን ሁሉ አንስቶ ልዩነቶችን ማሳየት "ለምንወስደው አጠቃላይ አቋም የሚጠቅም" /18/ ባይሆን ቀርቶ ይሆን?

ጥያቄውን መመለስ የኢማሌድህ ጉዳይ ነው:: እኛ ግን፣ ልዩነቶች ግልፅ ሆነው የሚታዩት በፕሮግራም ነጥቦች ሳይሆን፣ በየጊዜው የሚነሱት የፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ በሚወስዱት ወይንም በማይወስዱት የፖለቲካና የርዕዮተዓለም አቋሞች ነው እንላለን:: እንደውም ዋነኛው መመዘኛ ይኸው ነው እንላለን:: ነገር ግን ደግሞ አንዲት የመጨረሻ ነጥብ፣—

አንድ የፖለቲካ ፕሮግራም እንዳለነው፣ የአንድ የፖለቲካ ድርጅት የቅርብና የሩቅ ጊዜ ዓላማና ግብ ያሳያል:: በመሆኑም፣ በኢማሌድህ በትክክል እንደተጠቀሰው ለምሳሌ መኢሶን በእውነትም በፕሮግራሙ ውስጥ:—

"ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ስትመሠረት የሰፊው ሕዝብ የንግግር፣ የጽሑፍ፣ የጋዜጣ፣ የመሰብሰብ፣ በፖለቲካም ሆነ በሙያ የመደራጀት ነፃነቶች፣ ሰላማዊ ሰልፍና የሥራ ማቆም መብቶች ያለአንዳች ገደብ ተከብረው በሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል" ይላል::

ታዲያ እኮ ኢማሌድህ ለማሳመን እንደሚፈልገው፣ ይህ "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለሁሉኑ" እንዲገኙ ከመጠየቅና ከመታገል አያግድም:: የፕሮግራም ነጥብም ገገርት አይደለም:: በቀላሉ እናስረዳ::

የኢትዮጵያ ተማሪዎች በኃይለ ሥላሴ ዘመን "መሬት ላራሹ" የሚለውን ፕሮግራም በድርጅቶቻቸው ፕሮግራምና አርማ ላይ ጽፈውት ነበር:: በዚያን ጊዜ የነበረው የመኢሶን ፕሮግራምም እንደዚሁ "ሕ.ዲ.ሪ.ሊ. ስትመሠረት መሬት ላራሹ እንዲሆን ይደረጋል" ይላል::

ታዲያ ይህ በመሆኑ፣ የኢትዮጵያ ተራማጆች በኃይለ ሥላሴ ዘመን "መሬት ላራሹ" ሳይታገሉ ቀሩ ወይ? "መሠረታዊ የሕዝብ መብቶች የሚረጋገጡት ሕዝባዊ ሥርዓት ሲመሠረት ብቻ መሆኑን በፕሮግራማቸው አማካኝነት አረጋገጠው" /19/ በቀጠሮ አሳደሩት ወይ? በመጨረሻ "በትግላችን" የምትለው ተቀፀላ ኖረች አልኖረች፣ ትግሉ ሊቀር ነው ወይ? የመደብ ትግሉን ተቀብሉ "በትግላችን" ብሎ መፈክር አከ፣ ራስን እንደመደቦች ትግል ፈጣሪ አድርጎ እንደማቅረብ የሚያስቀጥር ነው:: የመደብ ትግል እንዲሁ፣ ብንወደውም ብንጠላውም አለ:: አለ:: ይልቁኑ የጦፈውን የመደቦች ትግል ተራማጆች እንዴት ተባብረው ይምሩት? አንገብጋቢው ጥያቄ ይኸው ነው::

ወደ ልዩነቶቹ ጥያቄ እንመለስ::

## 3.2. የብሔረሰቦች ጥያቄ

እንደተመለከትነው፣ ኢማሌድህ በብሔረሰቦች ጥያቄ ላይ "በመርህ ደረጃ" ልዩነት የለም ይላል:: እኛ ደግሞ፣ በብሔረሰቦች ጥያቄ ላይ ያለው ልዩነት አሁንም ቢሆን "በመርህ ደረጃ" ጭምር ነው እንላለን:: ይህ ልዩነት ደግሞ፣ በተለይም ከወዝ ሊግ ጋር ከፕሮግራም ነጥብ አንስቶ ይጀምራል:: እንደሚከተለው ነው::

በእውነትም፣ የኢማሌድህ ጸሐፊ በትክክል እንደጠቀሰው፣ ወዝ ሊግ በፕሮግራሙ ውስጥ፣

"የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከመገንጠል ድረስ የሚለው ሌኒኒስት ስታሊኒስት መርህ ሳይንሳዊና ትክክለኛ መርህ መሆኑን ይቀበላል" /14/

ይሁንና፣ ወዝ ሊግ በፕሮግራሙ ውስጥ ቀጥሎ ደግሞ፣

"ይሁንና፣... በአሁኑ የኢትዮጵያና የዓለም ሁኔታ... ይህ የሌኒኒስት መርህ ሁለት ገጾች /የመገንጠል ገፅና የአንድነት ገፅ — ቀገፍ ሕ.ዱ./ በአንደኛው ላይ፣ በአንድነት ገጽ ላይ፣ እና ተኩራለን:: ይህ አንድነት የፌደራል አውቶኖሚን /የራስን በራስ አገዛዝ — ቀገፍ ሕ.ዱ./ ቅርጽ መያዝ አለበት ብለን እናምናለን" /14-15/ ይላል::

እንግዲህ፣ ከጡራን የኢማሌድህ ጓዶች ! እዚህ ላይ "ከማርክሲስት ሌኒኒስቶች" መካከል "ከመርህ ደረጃ" ጭምር ልዩነት አይነሳም ወይንም የለም ለማለት ማርክሲዝምን ሌኒኒዝምን ማስናበት ያስፈልጋል:: ምክኒያቱም በዚህ ረገድ፣ "ሌኒኒስት መርህ" በምንም ዓይነት ቢሆን "ሁለት ገጽታ" የሉትም:: እንደዚህ ቢሆን ኖሮ፣ ሌኒን "ብሔረሰቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው ለመወሰን ያላቸውን መብት መገንጠልን ጨምሮና እስከመገንጠል ድረስ ነው" በማለት ደጋግሞ ባልተናገረ ነበር:: ታዲያ በዚህ "ሌኒኒስት መርህ" ውስጥ፣ በምን ዓይነት ተአምር "ሁለት ገጽታ" ሊወጡ ይችላሉ? ልዩነቱስ "ከመርህ ደረጃ" ካልሆነ፣ በምን "ደረጃ" ላይ ያለ ልዩነት ሊሆን ነው? ሌኒን አዘውትሮ ይጠቀምበት የነበረውን ምሳሌ እንጠቀምና "ትዳር መፋታትንም ጨምሮ እስከመፋታት ድረስ ነው" ወይንስ "ሁለት ገጽታ" አሉት? በእውነቱ ሌኒን ስለነዚህ "ሁለት ገጽታ" ቢሰማ ኖሮ፣ ሌኒን እራሱ "እኔ ሌኒኒስት አይደለሁም" ይል ነበር::

ሁለተኛው ልዩነት በብሔር ወይንስ ብሔረሰቦች በሚለው ጥያቄ ላይ የሚነሳው ነው:: እንደሚታወቀው በዚህ ጥያቄ ላይ አንዳንዶቹ በኢትዮጵያ ውስጥ ከብሔር /ነሽን/ ደረጃ የደረሱ ክፍሎች እንዳሉ ሲናገሩ፣ ሌሎቹ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በብሔረሰብ /ናሽናሊቲስ/ ደረጃ የሚገኙ ናቸው ይላሉ:: ይህንን ጥያቄ በሚመለከተው በኩል፣ መኢሶን እስካሁን የወሰደው አቋም፣ አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በብሔረሰብ ደረጃ እንደሚገኙ ነው:: ይሁንና፣ መኢሶን በተጨማሪ ደግሞ፣ የበለጠ ጥናት መደረግ እንዳለበት ያምናል:: በኢትዮጵያ ውስጥ ስለብሔረሰቦች ያለን እውቀት እጅግ ዝቅተኛ እንደሆነ እውቅ ነው::

ያም ሆነ ይህ፣ የልዩነቱ መሠረታዊ ጥያቄ ይህ አይደለም:: ልዩነቱ የሚነሳው፣ በተለይ ወዝ ሊግና አብዮታዊ ሰደድ፣ በቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ማሌሪድም ተጨምረው፣ "በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ብሔረሰቦች ብቻ በመሆኑ፣ እስከመገንጠል ድረስ የሚለው ሌኒኒስት ስታሊኒስት ባይገባዊና ትክክለኛ መርህ ለነርሱ አይውለም:: ይህ መርህ የሚውለው ለብሔሮች ብቻ ነው" ብለው ነው::

መኢሶን ደግሞ /እና እስከምናውቀው ድረስ ኢጭአትም ጭምር/ የሌኒን መርህ ለብሄርም ለብሔረሰቦችም የሚውል ነው ይላል:: ለብሔረሰቦች ቁራሽ ዓብ፣ ለብሔሮች "ሙሉ" ዓብ የሚል ሌኒኒስት ስታሊኒስት መርህ የለም ይላል:: በዚህ መርህ መፋለስ ምክኒያት በብሔረሰቦች ላይ የሚጣለውንም ፀረ ዲሞክራሲያዊ ገደብ ይቃወማል::

እንግዲህ ኢማሌድህን እንጠይቀውና፣ ለመሆኑ በዚህ ጥያቄ ላይ ያለው ልዩነት "ከመርህ ደረጃ" ጭምር ካልሆነ፣ በምን ደረጃ ላይ ያለ ልዩነት ነው? ወይንስ ኢማሌድህ የብሔረሰቦችንና የብሔሮችን መብት "የሚያውቀው" ለአለሉ ባይነት ነው?

ሦስተኛው፣ የልዩነት ነጥብ፣ "ሪጂናል አውቶኖሚ አማራጭ የሌለው ተግባራዊ መፍትሄ ነው" ከሚለው አቋም የሚመነጭ ነው:: ይህንን አቋም ወዝ ሊግና አብዮታዊ ሰደድ አጠንክረው ሲይዙት፣ ማሌሪድ በቅርብ ጊዜ ወዲህ ተጨምሮበታለች:: እነዚህ ድርጅቶች ዛሬ በይፋ ቀስቀሳ እያካሄዱበት ናቸው::

መኢሶን ግን /እና እስከምናውቀው ድረስ ኢጭአትም/፣ አንድ "አማራጭ የሌለው ተግባራዊ መፍትሄ" ብቻ አለ ብሎ አያምንም:: በዚህ በኩል መኢሶን የወሰደው አቋም፣ "ተግባራዊው መፍትሄ እንደሁኔታውና እንደጊዜው" መታየት አለበት የሚል ነው:: ይህም እንደሁኔታውና እንደጊዜው ቢሻው በጠበቀ ወይንም በላላ ኮንፌዴሬሽን፣ ቢሻው በጠበቀ ወይንም በላላ ፌዴሬሽን፣ ቢሻው በሪጂናል አውቶኖሚ፣ ቢሻው አውቶኖመስ ሪጅን፣ ቢሻው በውህደታዊ... ወዘተ ሊፈታ ይችላል ማለት ነው:: በአንድ አስቀድሞ በተገተረ በተወሰነ "አማራጭ በሌለው መፍትሄ" መመሪያ ግን አያሌ ችግሮችንና አደጋዎችን ይፈጥራል ማለት ነው::

ሆኖም፣ ይላል የኢማሌድህ ጽሑፍ ግን:-

"ተግባራዊውን መፍትሄ በሚመለከተው በኩል ያለውን ልዩነት ውይይት እንዲፈታው አባል ድርጅቶች ባለተስማሙ ጉዳዩ በጣም አሳሳቢ ሊሆን ባልተገባው ነበር" /16/

ዐርገጥ ነው:: በየካቲት 1969 በእንደዚህ ዓይነቱ ስምምነት ላይ ተደርሶ ነበር:: ይሁንናም፣ በአንድ በኩል በአንዳንዶቹ አባል ድርጅቶችና በመንግሥት ደረጃ ጭምር "አማራጭ በሌለው ተግባራዊ መፍትሄ" በይፋ ቀስቀሳው ሲጠናና፣ በሌላው በኩል በሃገሪቱ በመላ የብሔረሰቦች ጥያቄ ገፍቶ ሲመጣ በተለይ ማሌ ድርጅቶች አቋማቸውን ከማሳወቅ ይልቅ ሲያደፍጡ ደግሞ፣ ይህንኑ እንደአቋም አለመቁጠር የቆህነት ይሆናል:: የሰጎንን ፖለቲካ መጫወት ይሆናል::

በዚህ በኩል ለምሳሌም ያህል፣ የአፋር ብሔረሰብ ጠይቆት የነበረውንና እስከዛሬም የሚታገልለትን የሪጂናል አውቶኖሚ መብት ጥያቄ ልንጠቅስ እንችላለን:: በጠረርጌ ውስጥ የሲቪል/ሚሊቴሪው ቢሮክራሲ የቀድሞ ፊውዳሎችን አስታጥቆ በአርሶዎችና በሌሎች ብሔረሰቦች ላይ የፈፀመውን ጭፍጨፋ ልናስታውስ እንችላለን:: በባሌ/ሲዳሞ በአርሲና በጉጂ ብሄረሰቦች ላይ የደረሱት ጭፍጨፋዎች ልናወሳ እንችላለን:: እንደዚሁም፣ ካለፈው ዓመት ጀምሮ በተለይ በደቡብ ክፍላተ ሃገር እየገፋ የመጣውን የብሔረሰብ ጥያቄና የሚሰጡትን ቀላል መልሶች /"ጠባብ ብሔረተኛ"... / ልናመለክት እንችላለን:: በዚህም፣ ብሔረሰቦች መብታቸውን ለማስከበር የሚያደርጉት ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴዎች እየተገደቡ ናቸው:: እየታፈኑ ናቸው:: ይህ በራሱ ትምክህተኝነትን የሚያጠናክሩ ሁኔታዎች ፈጥሯል:: በዚህ በያዝነው ዓ.ም. እንኳ በከንባታ/ሃድያ ብሄረሰቦች ላይ ከፍተኛ ጭፍጨፋ ተፈፅሟል:: በየምፍራው "ጠባብ ብሔረተኞች" እየተባሉ አያሌ የጭቁን ብሔረሰብ ታጋዮች እስር ቤቶች ውስጥ ተወርውረዋል::





ወይንም በጭፍን ተረሽነዋል::

በሌላው በኩል ጉዳዩን "ለማጥናት" አያሌ ኮሚቴዎች እየተቋቋሙ ተሰብስበው ፈርሰዋል እንጂ፣ የተወሰደ ተጨባጭ እርምጃ የለም:: አሁን ደግሞ፣ "ከተጨባጭ እርምጃዎች በፊት የብሔረሰቦች ኢንስቲቱት" የሚል መፈክር እየተስተጋባ ነው:: ይሁንና፣ በመካከሉ ደግሞ የብሔረሰብ እንቅስቃሴዎች ሰፊት እያገኙ፣ እየተሰበሰቡና እየተደራጁ በመምጣት ላይ ናቸው::

እንግዲህ አቋማችን ምንድነው?

የኢማሌድህ ጽሑፍ በትክክል እንደጠቀሰው፣ መኢሶን በሁኑ ወቅት /እንደገና! በሁኑ ወቅት/፣ "በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ብሔረሰቦች /በኤርትራ የሚገኙትንም ብሔረሰቦች ጨምሮ ቅንፍ ሕ.ዱ./ መገንጠል አይበጃቸውም፣ እንደገፍም ብሏል" /17/

ይህናው ዛሬም ቢሆን የመኢሶን አቋም ነው:: በተጨማሪ፣ ወዝ ሊግ እንደሚለው "የብሔረሰቦች ኢንስቲቱት" ቢቋቋም መኢሶን ይደግፋል:: እንደዚሁም፣ መኢሶን እንደሚለው "የብሔረሰቦች ሸንጎ" ቢቋቋም፣ ለብሔረሰቦች አብሮ መኖርና ለአብዮታችን መገፋት የሚጠቅም ይሆናል ... ወዘተ:::

ነገር ግን መፈክሮች ብቻ ጥጋ የላቸውም:: የብሔረሰቦችን ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴዎች "ጠባብ ብሔረተኛ" በሚል ብቻ ወደጉን መገፍተርም አያዋጣም:: "የብሔረሰቦች ኢንስቲትዩትና የብሔረሰቦች ሸንጎ" አንድ እርምጃ ወደፊት የሆኑትን ያህል፣ መሠረታዊ መፍትሄ አይሰጡም::

የመኢሶን ጥያቄ፣ ተግባራዊ እርምጃዎች አሁኑኑ ይወሰዱ የሚል ነው:: በዲሞክራሲያዊ ጥያቄዎች አካባቢ የብሔረሰብ እንቅስቃሴዎች አይታፈኑ:: እንዲያውም ይታወቁ:: ከነርሱ ጋር ውይይት ይደረግ:: እንደሁኔታው መንግሥታዊ ድጋፍ ጭምር ይሰጣቸው የሚል ነው:: መንግሥትና ተራማጅ የፖለቲካ ድርጅቶች እነኚን በእንደዚህ የተደራጁትን ቀርቶ፣ ያልተደራጁትን ለማደራጀትና ለመደገፍ አሁኑኑ መጣር አለባቸው የሚል ነው::

ዐርገጥ የባህል ችግሮቻቸው ጥሬ ናቸው:: ሆኖም፣ በፖለቲካዊ ትርጉሙ መሠረታዊ አይደሉም:: የብሔረሰቦች ጥያቄ ከቴያትር ቤትና ከቴሌቪዥን መድረኮች አልፎ እንደሚሄድ ሁላችንም እናውቃለን:: የጊዜው ጥያቄ፣ በርግጥ ድፍረት የሚጠይቀውን ተጨባጭ ተግባራዊ እርምጃዎች የመውሰድ ያለመውሰድ ጥያቄ ነው:: ይህናው፣ የራስን ፈደሎች ከማውጣት መብት አንስቶ እንደሚጀምር ሁላችንም መቀበል ይኖርብናል:: ነገር ግን ምን ዓይነት አስተሳሰብ አለ?

በዛሬው ወቅት አንዳንድ ክፍሎች ብሔረሰቦችን በአባታዊነት /ፓቴርናሊዝም/ ሊያዩ ይጥራሉ በሌላውበኩል ትምክህተኝነት እየተስፋፋ ነው:: የጭቁን ብሔረሰቦች ዲሞክራሲያዊ ትግሎች በሌኒን ስም እየታፈኑ እየተወገዙ ናቸው::

የኤርትራን ጥያቄ በሚመለከተው በኩል፣ ወታደራዊ ኃይላችን በምስራቅ ላይ ቆሞ ወደሰሜን መጠናከሩ ትክክለኛ ነው:: ይሁንና፣ የኤርትራ ጥያቄ ወታደራዊ የሆነውን ያህል ፖለቲካዊ፣ ፖለቲካዊ የሆነውን ያህል ወታደራዊ ነው:: ስለዚህም በሁለቱ ጉዳዮች መካከል ያለው ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት በጥንቃቄ መጠበቅና መታየት አለበት:: ለኤርትራ ጥያቄ በሁኑ ወቅት ከመገንጠል በስተቀር፣ በኢትዮጵያ የግዛት አንድነት ውስጥ ማናቸውም የፖለቲካ መፍትሄ የሚያዋጣ ነው:: ወታደራዊ መፍትሄ ብቻ ግን፣ ገና ለረጅም ጊዜ አያሌ ችግሮችን ያስከትላል:: ስለሁሉም ጉዳይ ከዛሬው ለመናገር የሚቻል አይሆንም::

እንግዲህ ይህናውን ክፍል በዚህ እንጨርሰው:: ይሁንና የመጨረሻ መጨረሻ ደግሞ፣ ይህንን ሁሉ የተናገርነው "ለአለሉ ባይነት" እንዳልሆነ አሳውቀን ወደሚቀጥለው ክፍል እንለፍ:: የኢማሌድህ አባል ድርጅቶች እንደኛ "ካሉ" ደስታችን ነው:: እንደኛም "የማይሉ" ከሆነ፣ ለመወያየት ዝግጁ ነን:: በተረፈ፣ የብሔረሰቦችን ጥያቄ ለመፍታት በሚወሰዱ ዲሞክራሲያዊ እርምጃዎች ሁሉ ባለን አቅም መጠን ከመሳተፍ ወደኋላ እንደማንል እንገልፃለን:: ለተቃራኒው፣ አስተሳሰባችን ምንጊዜም ቢሆን የትምክህት ጥቃት አጾ ከሚወርድባቸው ጭቁን ብሔረሰቦች ጋር ይሆናል:: ነገር ግን እዚሁ ላይ ደግሞ፣ በጥያቄው ላይ ማርክሳዊ ፖሊሲ ከስን ለማካሄድ፣ አስቀድሞ ማርክሲስት መሆን እንደሚያስፈልግ ለኢማሌድህ ባናሳስበው እናልፍም:: በተረፈ፣ "አዚምሬ! ወሬ አዚምሬ"::

## 3.3. የዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ

የኢማሌድህ ጽሑፍ በዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄም ላይ ያሉትን ልዩነቶች እንዴት እንዳቀረባቸው ከዚህ በላይ አመልክተናል:: ይሁንና ኢማሌድህ በጽሑፉ ውስጥ የየካቲት 1969 ዓ.ም. "የጋራ መግለጫ" እንደዚያ ደጋግሞ ሲጠቅስ፣ ስለነበሩ ስምምነቶች እንደዚያ ደጋግሞ ሲያስታውስ፣ በዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ ላይ የተደረሰበትን የጋራ አቋም ግን አንድም ጊዜ እንኳ አለማውሳቱ እጅግ አስገርሞናል:: ለምን ይሆን? ለማንኛውም፣ ኢማሌድህ ከረሳው አይቀር፣ እኛ እናስታውስና እንጥቀሰው:: በዚህ ጥያቄ ላይ በየካቲት 1969 የተደረገው ስምምነት የሚከተለው ነበር::

"... በአሁኑ ወቅት አብዮቱን ለመቀልበስ ያሰፈሰፉትን አድሃሪያን በይበልጥ ለመቋቋም በስውር ታፍነው የሚሠሩ ተራማጅ ድርጅቶች ትግላቸውን በይፋ ለማካሄድ እንዲችሉና በተለይም ደግሞ፣ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ለመመሥረት የሚያስችሉትን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲዎችና ሰፋፊ ድርጅቶችን ለማቋቋም እንዲችሉ፣ በበቂ ችሎ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ መታወጅ አለባቸው::"

ስምምነቱ ይህ ከሆነ፣ እንግዲህ በየካቲትና በነሐሴ 1969 መካከል ድርጅቶቹን ምን ነካቸው? ስምምነቱንስ ያፈረሰው ማነው? በተጨማሪ በበሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ውስጥ ስለዚህ ጉዳይ የተፃፈውን ለናስታውስ እንችላለን:: በርሱ ውስጥ፣ የፕሮግራሙን "ዓላማዎች ከሥራ ላይ ለማዋል... ዝግጅትና አጣዳፊ ተግባሮች" በሚለው ክፍል የሚከተለው ሠፍሯል:-

"ፃ. ሕዝቡ በአብዮቱ መገፋት የሚችለው ነቅቶ፣ ተደራጅቶ፣ ታጥቆ ለትግሉ የተሟላ ዝግጅት ሲኖረው ብቻ በመሆኑና ይህ ዝግጅት የሰመረ ውጤት ሊሰጥ የሚችለው የሰፊው ሕዝብ ወገኖች በሙሉ ለመማር ለማስተማር፣ ለመደራጀትና ለማደራጀት፣ ፈላጊ የሆኑትን ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለገዳቸ ገደብ ከሥራ ላይ ሲውሉ ብቻ ስለሆነ፣ ለፀረ ፊውዳል፣ ፀረ ቢሮክራሲያዊ ቡርዧ፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች በሙሉ የመናገር፣ የመፃፍ፣ የመሰብሰብ፣ በሰላማዊ ሰልፍ የማውረግ፣ የመደራጀትና የመሳሰሉት ሰበዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች በአስቸኳይ ከሥራ ላይ ማዋል" /25/

የጠቀስናቸው እነዚህ ስምምነቶችና የጋራ አቋሞች እንደኩሉ ውሃ ጥርት ያሉ ናቸው:: ተወዳዳሪ የማይገኝለት የህግ ሊቅ እንኳ፣ ቢፈልግ ቢውል አንድም የሚያሻማ ነገር አያወጣላቸውም:: ደግሞ "ከበው ነገር ገባችሁ" እንዳንባል እንጂ፣ የኢማሌድህ ጸሐፊ እንደጠቀሰው በፕሮግራሙ ላይም ማሌሪድም እንደዚህ ቢል በግልፅ ጽፎ ነበር:-

"በተለይም የሰፊውን ሕዝብ መደራጀት ለማፋጠን ለጥያቄች ብቻ የሚሆን የዲሞክራሲ መብታቸውን የመንጠቅ ጉዳይ የጊዜው ፍና ጥያቄ ነው::... የዲሞክራሲ ታጠቅ ጉዳይ ከዲሞክራሲያዊ ጥያቄ ጋር እንደ አውራ ሆኖ ቀርቧል::... የሰፊው ሕዝብ የመደርጀት /ማሌሪድ/ በቅድሚያ የሚታገለለት ይህ የሰፊው ሕዝብ የዲሞክራሲና የትጥቅ ጥያቄ በሪቮሉሽናዊ መንገድ ካልተገኘ እንዲሟላ ነው" /19/

ማሌሪድ ይህንን በግልፅ ያሳተ የፀፈውን ፕሮግራሙን፣ እንደገና ተመልሶ ቢያነበው፣ "ታዲያስ በተገላቢጦሽ ብለን እየታገልን አይደለም ወይ?" ይል ይሆናል:: የናም መልስ አጠር መጠን ያለ ነው::

የመደቦችን ትግል ተክለ "በተገላቢጦሽ" ማለት፣ መንበብ የምበላው እያንኩ ነው የማለት ያህል ነው:: የመጀመሪያው ሰዎች በወጉትም ባይወጉትም፣ ቢጠሉትም ቢፈልጉትም ያለና ነባራዊ የሆነ የሕብረተሰብ ሕግ የሆነውን ያህል፣ የኋለኛው ደግሞ ነባራዊ የተፈጥሮ ህግ ነው:: ስለዚህም "በተገላቢጦሽ" የሚለው በዚህ ነባራዊ ህግ ምክኒያት "ባይገባዊ" የሚሆነውን ያህል፣ "አሁኑኑ" ደግሞ በዚህ ምክኒያት "ኢ-ባይገባዊ" አይሆንም:: እንደውም "አሁኑኑ" የሚለው ዉዲያ ወዲህ ባይል እንደሚባለው "ምስማረን ጥንቅላት ይመታል":: "በተገላቢጦሽ" የሚለውን "ባይገባዊ" ማለት፣ ባይገበን አስማት ለማድረግ እንደሁ እንጂ፣ ለሌላ ለምንም አይጠቅምም:: እውነትም አንዳንዱ በገመለከቱት፣ ሰዎች "ባይገባዊ" ባሉ ቁጥር አስማት የሚሠሩ ባይመስላቸው አስቀረም::

መኢሶን "አሁኑኑ" በማለት ያነሳው የዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ በዙ መዝገቦል እንደደረሰ በት የማይባል ነው:: ይህም የሆነው በመኢሶን ላይ የዘሩ ከፍሎችን ዛይን ያወጡ አድርባዮች በበጡት የትርጉም ትርጉምና ካካሄዷቸው አጉል ቀስቀሳዎች የተነሳ ነው:: ይሁንና፣ መኢሶን እንደገና የምንዘረዝራቸው አብዮታዊ እርምጃዎች "አሁኑኑ" ይወሰዱ ማለት ነበር:: ነውም:: ከዚህ በታች እንባቢዎች ጥያቄዎችን በጊዜው ከነበረና ዛሬም ካሉት የፀረ አብዮት ሁኔታዎች ጋር ጥምር አገናዝበው እንዲመለከቷቸው በቅድሚያ በማስታወስ እንቀጥል:: "አሁኑኑ" ማለት:-

- የፊውዶ ቡርዧው ሥርዓት ቢሮክራቢ አሁኑኑ ይመታ ማለት ነበር፤ ነውም::
- የሰፊውን ሕዝብ በበሰለ መደራጀት፣ መንቃትና መታጠቅ አሁኑኑ በበሰለ እናጠይፍ፣
ማለት ነበር፤ ነውም::
- የሕዝባዊ ድርጅቶች ዲሞክራሲያዊና ነፃ ህልውና አሁኑኑ ይታወቅ፤ ይከበር ማለት
ነበር፤ ነውም::
- የሰፊው ሕዝብ ነፃ እርምጃዎች አሁኑኑ ይቀጥሉ፣ ይፋፋሙ ማለት ነበር፤ ነውም::
- በሰፊው ሕዝብ ድርጅት ውስጥ የሚያቀጠቁጡትን መሥፍንነትና አምባገነንነት አሁኑኑ
እንቀጭ፣ እንቆጣጠር ማለት ነበር፤ ነውም::
- በታሠረት የኢህአፓ ቁጥር ነፍስ ገዳዮች ላይ አሁኑኑ እርምጃ ይወሰድ ማለት
ነበር፤ ነውም::
- የታሠረት ሃቀኛ ታጋዮችና የሕዝብ ወገኖች አሁኑኑ ይፈቱ ማለት ነበር፤ ነውም::
- በተራማጆች መካከል ያሉት ልዩነቶች አሁኑኑ በዲሞክራሲያዊ ዘዴ ይፈቱ ማለት
ነበር፤ ነውም::
- የተራማጅ የፖለቲካ ድርጅቶች ዲሞክራሲያዊና ነፃ ህልውና አሁኑኑ ይታወቅ ማለት
ነበር፤ ነውም::
- በሲቪል/ሚሊቴሪው አሻጥረና ቢሮክራቶች ላይ አሁኑኑ እርምጃ ይወሰድ ማለት
ነበር፤ ነውም::
- ከዚህ ሁሉ በላይ ረቂቁ የተቀመጠው የዲሞክራሲ መብቶች አዋጅ፣ አሁኑኑ በሥራ ላይ ይዋል ማለት ነበር፤ ነውም::... ወዘተ





እንግዲህ እነዚህ ሁሉ ዲሞክራሲያዊ ጥያቄዎች በዚያን ጊዜ ሆነ አሁን ለአብዮታችን መገፋት ወሳኝ አልነበሩም ወይ? አይደሉም ወይ? ለመሆኑ ጥያቄዎቹ በተግባር ቢተረጎሙ ከዲሞክራሲያዊ መብቶች ሌላ ምንድና ናቸው? በዚያን ጊዜ የነበረውን የፀረ አብዮት ውጥረት ለመከላከል የዘረዘርናቸው ዓይነት አብዮታዊ እርምጃዎች ወዲያውኑ /"አሁኑኑ"/ መውሰድ አያስፈልግም ነበር ወይ? አይቻልም ነበር ወይ? አብዮትና ፀረ አብዮት ዛሬስ እንደምን ተሰልፈዋል?

ኢማሌድህ በዲሞክራሲ መብቶች አስቸኳይነት ጥያቄ ላይ ለመተንፈስ እንኳ አይፈልግም:: አስቸኳይነታቸውን ለመግለፅ የሚፈራውን ያህል፣ "በተገላቢጦሽ" እያለ ይሞሃል:: ነገር ግን ወደመቻል አለመቻሉ ስገመጣ፣ ኢማሌድህ:-

"በሰፊው ሕዝብ 'ነፃ እርምጃ፣ የውስጥ ፀረ አብዮት ኃይሎችን መፍጨርጨር በመገታትና' በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ 'መደናገጥ'/መካከል/ ያለውን ግንኙነት የደርግ የመደብ ጠባይ መሆኑ ግልፅ ነው" /25/

በማለት "አቀውን" ይመልስና ያልፈዋል::

እንደእውነቱ ከሆነ፣ ኢማሌድህ ይህንን ከተናገረ አይቀር፣ በዚያን ጊዜ በደርጉ ውስጥ የነበረውን አሰላለፍ የኃይል ሚዛን ቢያብራራልን ኖሮ በዙ ነገሮችን ለንረዳ በቻልን ነበር:: ሆኖም፣ ከኢማሌድህ ጸሐፊ ውስጥ ስለዚህ ጉዳይ የምናነበው አንድም ነገር የለም:: እናንም ለብዙ ጊዜ አስቸግሮን የቆየው የአብዮታችን ጥያቄ፣ በአብዮታዊ ሰደድና "ከደርግ" መካከል ያለው ልዩነት ነው:: በጊዜው "የተለያዩ መሆናቸውን አስያለሁ" እያለ ሲፎከር የነበረው ወዝ ሊግ እስከዛሬ ድረስ አይፍጧል:: አስገራሚ ደፈጣ!!!

በእውነትም እርምጃዎቹ በዚያን ጊዜ ያልተወሰዱት "የደርግ የመደብ ጠባይ" አንደ አይደለም:: በደርጉ ውስጥ የነበረው አሰላለፍና የኃይል ሚዛን እንደው አይደለም:: የዘረዘርናቸው ዓይነት እርምጃዎች በዚያን ጊዜ ያልተወሰዱት፣ አንደኛ፣ ባጠቃላይ በተራማጆች መካከል በተፈጠረው አለመተማመን:: ሁለተኛ፣ አንዳንድ ድርጅቶች በአድርባይነት ከእጃቸው በመንሸራተታቸው:: ሶስተኛ፣ በተለይ በመኢሶን ላይ በነበረት ጥርጣሬዎችና እንደዚሁም ጥያቄዎች መኢሶን "ሊበላ፣ ሊያበጥ፣ ሊፈነዳ፣ ሌሎችን ድርጅቶች ሊውጥ...ወዘተ" ያቀረባቸው ጥያቄዎች ናቸው በሚል ስለተገመቱ ነው:: መኢሶን በዚያን ጊዜ ይህንኑ በማመልከት እንደሚከተለው የፃፈውም ስለዚህ ነው:: እንጥቀሰው:-

"... ሕብረቱ በዲሞክራሲያዊ አሠራር በቀም ነገሮች ላይ የተመሠረተ መሆኑ ቀርቶ፣ አንድም እርምጃ ወደፊት ለመራመድ እንዳይችል ተሰንኩሎ የማይተማመን ቢለገፀራ በየወገኑ ይማማላል'እንደሚባለው ሁሉ፣ በወረቀት ላይ የሚቀሩ ፕሮግራሞችን ብቻ ደጋግሞ በመንደፍ ተወስኗል:: የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ህልውና ለማስጠበቅና አብዮቱ ሥር እንዲሰድ ይጠቅማል በማለት፣ በህጋዊ ሥራ በተሰማሩት ጊዜ አማካይነት፣ መኢሶን ለጊ.ወ.አ. ደርግና ለተራማጆች ሕብረት በየወቅቱ ያቀረባቸውን አሳቦች በቀን መንፈስና ከአብዮቱ እንፃር በመመልከት ፋንታ፣ አሳቦቹ ከመኢሶን በመመንጨታቸው ብቻ ደርግና አንዳንዶቹ ድርጅቶች በጥርጣሬ ዓይን እያዩአቸው ከሥራ ላይ ሳይውሉ በመቅረታቸው ለውጥረቱ መፍትሄ፣ ለአብዮቱ የተፈለገውንና የሚጠበቀውን ያህል አስተዋጽኦ ለማድረግ አልተቻለም" /ሰሕድ 61 - ነሐሴ 1969/

ነገር ግን መኢሶን ይህንን ሲናገር፣ ኢማሌድህ እንደሚባለው "ወደ ይመናፃች ገርማዊ የሆነ ማሽገሽግ" ያደርግና:-

"መኢሶን በአሉባልታ በዙ ያምናል:: በአሉባልታ ይደናገጣል:: እድሃሪያን ባወረና ጥረገባቸውን በነፈ ቁጥር የገውን ከበርቴ ወገኑ ይከደዋል:: ስሚን አጠፋት፣ አትያሉኝ፣ ሊያስመቱኝ ነው'በማለት ሮሮውን ያሰማል እንጂ፣ ችግሮችን አብዮታዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት ሙከራ አላደረገም" /26/

በማለት ከባድ "ሂስ" ይሰነዝራል:: እንግዲህ በናም በኩል፣ ወደነበረት ሁኔታዎች ተመልሰን አንዳንድ ነገሮችን ማስታወስ የግዴታ ሊሆን ነው:: ሆኖም፣ እዚህ ላይ ልብ እንበልና፣ ዋናው "ሂስ"፣ "መኢሶን... ሮሮውን ያሰማል እንጂ፣ ችግሮችን አብዮታዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት ሙከራ አላደረገም" የሚለው እንደሆነ ሁልጊዜም እንደናስታውስ እንጠይቃ:: "ሙከራው ተደርጓል አልተደረገም? - የሚከተሉት ክፍሎች የዚህ ጥያቄ መልሶችምና ናቸው::

## 4. ከጥር እስከ ነሐሴ 1969 - "ህብረትና" ፀረ ህብረት

የኢማሌድህ "የህብረት ደምጸ" ጋዜጣ በደገብ ያነበቡ ሰዎች እንደተገነዘቡት ሁሉ፣ ኢማሌድህ "ደምፁን" የማያሰማበት ጉዳይ ቢኖር፣ ከጥር 69 እስከ ነሐሴ 69 በነበረት የህብረቱ ችግሮችና ጥያቄዎች ላይ ነው:: በተጨማሪ፣ አንባቢው፣ በኢማሌድህ ጸሐፊ ውስጥ የህብረቱ ችግሮችና ጥያቄዎች ላይ ነው:: በተጨማሪ፣ እንባቢው፣ በኢማሌድህ ጸሐፊ ውስጥ የሰሕድ አትሞች ቢጠቀሱ ቁ.60ና 61 ብቻ እንጂ፣ ከዚያ በፊትም ሆነ በኋላ የወጡት ቁጥሮች አንደም በታ ላይ ቢሆን እንዳልተወሱ እንኳ ይገነዘባል:: ደግሞ፣ ከሁሉም በላይ የሚያስገርመው ነገር፣ እንደናን፣ የተጠቀሱት አትሞች በደገብ አልተጠቀሱም:: ሁለተኛ፣ የተጠቀ

ሱተዎ "ጥቆቦች" ቢሆኑ ፈፀም አለተተነተኑም:: በፓ መኢሶን በራሱ ጽሑፍ መለሰው የገሬ ፊት ለማስመሰል፣ "ከጥቆቦች" በፊት ወይንም በኋላ "መኢሶን እንዲህ ቢል ገለፀ ነበር"፣ "ያለ ቢገባ እንዲህ ብሉ ነበር"፣ "በውሸት ሰምሮና ቢገዘተ"፣ "ማስመሰልና የአዘ አገባ ማገባት"... የሚሉ አያያዝ ጠረጉች ተደርድረዋል:: "ትንተናውም" በዚህ ያበያና ስሚተን በፓ ለመማፀን ሌሎች ጠረጉች ይፈለጋሉ::...

ስለዚህ፣ አሁንም እነርሱ ከተውት፣ እና ደገሞ እንመለሰበተና የነገሮችን ዕድገት ከወቀተ ወቀተ በጥሬ እናስታውስ:: አንባቢያች በአንዳንድ ጥቆቦችን እርዝማኔ ምክኒያት እንዳይሰለቹ ቢሁኑ ተዕግሥታቸውን እንጠይቃለን:: በተጨማሪ የህብረቱን ታሪክ ትንሽ ቀደም በለን እንጀምራለን:: በተረፈ ሰሕድ ቁ.60 በዚያ መስከ ለምን እንደወጣ ወደፊት ጊዜ ሰመጣና ሁኔታዎች ሲያመች እንደሚገለፅ እናሰውቃለን::

### 4.1. ከኢማሌድህ በፊት

ሰሕድ ቁ.60 /21.11.69/ በትክከለ እንዳመለከተው:-

"የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ህብረት የተቋቋመው፣ ከረጅም ጊዜ ፖለቲካና ርዕዮተ ዓለማዊ ትግል በኋላ እንጂ፣ ባለፈው የካቲት /1969/ ወር የጋራ መግለጫው በወጣበት ጊዜ በድንገት የተፈጠረ አይደለም:: በህብረቱ ድርጅቶች መካከል፣ ከዛሬ ዓመት ገደማ ጀምሮ፣ ረዘም ያሉ የሁለት ወገን /ባይላተራል/ ውይይቶች ተካሂደዋል:: አንዳንዶቹ ድርጅቶች፣ ለምሳሌ መኢሶንና ሊግ፣ በጸሑፎቻቸውም ጥምር አባቦች ተለዋውጠዋል:: ክርክሮችም አካሂደዋል::"

ይህንን ጥቀስ የኢማሌድህ ጸሑፍ ጠቀስታል:: ነገር ግን እንደዚህ መሆኑ "ሃቅ ነው" ከማለት በስተቀር፣ ሌላ ተጨማሪ ነገር አይነገረንም:: እና እናስታውስና ገና ጊ.ወ.አ. ደርግ ከመመሥረቱ በፊት፣ መኢሶን ከ1966 ዓ.ም. ጀምሮ "የተራማጆች ህብረት" በተሰኘው ጋዜጣው አማካኝነት በዚያን ጊዜ ከነበሩ ከሌሎች ቡድኖች ጋር /ከኢሕአፓ ጋር ጥምር/ የጸሑፍ ለውውጥ ሲያደርግ ነበር:: ኢሕአፓን በሚመለከተው በ1966/67 በቃል ጥምር ብዙ ውይይቶች ተካሂደው ነበር:: ሊግን በሚመለከተው በ1968 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ "የአዲስ ፋና" መጽሔት በጋራ በማውጣት በተግባር እንዲተባበሩ ጥምር መኢሶን አሳብ አቀርቦ ነበር:: ሁለቱ ድርጅቶች አንድ ለዚህ መጽሔት የተመሠረተ የጋራ ኮሚቴ አቋቋመው ለጥቂት ጊዜ ሠርተው ነበር:: ይሁንና፣ ወዝ ሊግ በመካከል በአንድ የውስጥ ጸሑፉ ባሰራጨው ፀረ ህብረት ጸሑፍ ምክኒያት በ1968 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ተጀምሮ የነበረው ተግባራዊ ህብረት ተቋረጠ::

ሆኖም፣ ሕዝብ ድርጅት ጽ/ቤት እንደተቋቋመ፣ መኢሶን፣ ሊግና ኢጭአት በዚያው በሕዝብ ድርጅት ጽ/ቤት ውስጥ አንድ "ኮከብ" /የሥራ ቡድን/ የጋራ ቡድን አቋቋመው በህብረቱ ለመሥራት ጀመሩ:: የሕዝብ ድርጅት ጽ/ቤትንና የፖለቲካ ት/ቤትን በመምራትና... ወዘተ አያሌ ሥራዎችን ይሠሩ የነበረትም በዚህ የጋራ የሥራ ቡድን /"ኮከብ"/ በተሰኘው የጋራ መድረክአማካይነት ነበር:: ማሌሪድና አብዮታዊ ሰደድ በዚያ ሰዓት አልተመሠረቱም ነበር:: ይሁንና፣ ማሌሪድ ከተቋቋመ ከጥቂት ወራት በኋላ፣ የማሌሪድ አባሎች በሕዝብ ድርጅት ጽ/ቤትና በፖለቲካ ት/ቤት እንዲገቡ ሆነ:: በቢሮክራሲውም ውስጥ እንደዚሁ:: ከዚያም በኋላ፣ በመኢሶንና በማሌሪድ መካከል "ህብረት" ተፈጠረ:: እነርሱም "እውነት" የተሰኘውን ጋዜጣ በጋራ ማውጣት ጀምረው ነበር:: አለፈውም፣ በአስቸኳይ ወደ ውህደት ለመሸጋገር እንዳገዱ የጋራ ተግባራዊ ኮሚቴዎችን አስከማቋቋም ደርሰውም ነበር:: ሆኖም፣ ይህናው ክፍለ ገና ከመጀመሩ፣ በተፈጠረት መሠረታዊ የአቋምና የአሠራር ልዩነቶች የመኢሶን-ማሌሪድ "ህብረት" በጥቂት ወራት ውስጥ አከተመ::

በዚህ ጊዜ ውስጥ ከሐምሌ/ነሐሴ 1968 ዓ.ም. ጀምሮ መኢሶን ሰፊ ህብረትን ለመመሥረት በአንድ በኩል ከወዝ ሊግ፣ በሌላው በኩል ከኢጭአት ጋር አያሌ የሁለት ወገን /ባይላተራል/ ውይይቶችን ያካሂድ ነበር:: በወቀቱ የማሌሪድ አቋም "እናንተ /መኢሶን/ ተወያዩና በተስማማችሁበት እንስማማለን" የሚል ነበር:: አብዮታዊ ሰደድን በሚመለከተው፣ ይህ ድርጅት ምንም እንኳ ከሐምሌ/ነሐሴ 1968 ዓ.ም. ጀምሮ መቋቋም ቢጀምርም፣ ከርሱ ጋር የነበረው ግንኙነት በደርግ ደረጃ እንጂ፣ በነፃ የፖለቲካ ድርጅት ደረጃ አልነበረም:: ከአብዮታዊ ሰደድ ጋር እንደዚህ ዓይነት ግንኙነት የተጀመረው በጥር 1969 ነው:: ይህም ቢሆን፣ በየጊዜው በአብዮታዊ ሰደድና በደርግ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ለይቶ ማስቀመጡ አስቸጋሪ እንደሆነ ነበር:: ስለዚህም፣ በህብረቱ ጥያቄ ላይ ከፍተኛ ችግሮች ተደቅነው እንደቆዩ ለመረዳት አስቸጋሪ አይመስለንም:: መኢሶንም፣ አንድነታቸውና ልዩነታቸው እንዲገለጸለት በተደጋጋሚ ሳቀረባቸው ጥያቄዎች መልስ ባያገኝ ቆርጧል:: ከደርግ ጋር "ሂሳዊ ድጋፍ"፣ ከአብዮታዊ ሰደድ /=ደርግ/ ጋር "ህብረት" የቱን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ መረዳት ቀላል ይመስለናል::

እንደሚታወቀው ጥር 1969 በደርጉ ውስጥ በነበሩት የኢሕአፓ የውስጥ አርበኞች ጥምር አብዮታችን ተወጥሮ የተያዘበት ጊዜ ነበር:: ይህንን ሁኔታ ተራማጆችም በትክክል ተገንዝበውት ነበርና፣በዚህ ጊዜ ውስጥ በጋራ ተሰለፍ ከመቀደቀ በስተቀር ሌላ አማራጭ እንደሌላቸው በመረዳት፣ የተራማጆችን ህብረት ወደመመሥረት አመሩ:: ስለዚህም፣ ከያንዳንዱ ድርጅት ሁለት ሁለት አባሎች የተወከሉበት የህብረት ስብሰባ ለመጀመሪያው ጊዜ ጥር 24/1969 ዓ.ም.





በብሄራዊ ሸንጎ ውስጥ ይደረጋል::

ይህ በራሱ አንድ ትልቅ እርምጃ ወደፊት ነበር:: ወቅቱን በትክክል በናስተውለ፣ በጥር 22 በአብዮት አደባባይ ቀጣ የተመለበት የሰፊው ሕዝብ አብዮታዊ ሰልፍ ከተደረገ ሁለት ቀኖች በኋላና፣ እነዓለማየሁ/መገስ ከመወገዳቸው ሁለት ቀኖች በፊት ነው:: ጥር 26 1969 በእነዓለማየሁ/መገስ ላይ ፈጣንና አብዮታዊ እርምጃ ሲወሰድ፣ አብዮታችን ባጠቃላይ "ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት" ተሻገረ:: በእውነትም፣ ተራማጆችን ለረጅም ጊዜ ሰንከሉ ያሠራቸው የውስጥ አርበኞች ሴራ ተበጣጠሰ:: ከዚህ ጊዜ በኋላም፣ የህብረቱ መመሥረት በሙሉ ኃይሉና ቸሉታው ይጣደፋል::

ነገር ግን ህብረቱ፣ እውነተኛ ህብረት ሊሆን የሚችለው በተለይ አብዮታዊ ሰደድ /="ደርግ"/ ዲሞክራሲያዊ ሲሆንና የዲሞክራሲ መብቶችን ሲያውቅና ሲያከብር ብቻ እንደሆነ እጅግ ገለፀ ነበር:: ምክኒያቱም፣ ህብረቱ በአንድ በኩል በፖለቲካ ሥፍራና በማቴሪያላዊ ኃይል ተመጣጣኝነት በሌላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል የተመሠረተ ነበር:: በሌላ በኩል፣ ዕኩልነታቸው ሊረጋገጥ የሚችለው በዲሞክራሲ ብቻ ነበር:: በየካቲቱ የጋራ መግለጫ ላይ:- "በአስቸኳይ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ መታወጅ አለባቸው" በማለት "ታፍ ነው ስለሚሠረት ተራማጅ ድርጅቶች" ጥምር የተገለፀው ስለዚህም ነበር:: መኢሶንም፣ በተደጋጋሚ "የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ ይታወጁ" እያለ የወተወተው እንደም በዚህ ምክኒያት የተነሳ ነው:: የድርጅቶች እኩልነት ሊጠበቅና ሊከበር የሚችለው፣ ወይ እኩል በሆነ የፖለቲካ ሥፍራና ማቴሪያላዊ ኃይል፣ ወይ ደግሞ በዲሞክራሲ እንደሆነ መረዳቱ ቀላል ይመስለናል::

ወደ ርዕሳችን እንመለስና:-

### 4.2. የመጀመሪያው ወቅት

የመጀመሪያው ወቅት አይነተኛ የሚሆነው፣ ባንድ ወገን ህብረቱን ለመመሥረት ይደረግ በሚደረገው ጥድፊያና፣ በሌላው ወገን የአብዮቱን ወደአጥቂነት መሸጋገርእውነት ለማድረግ በወዝአደሮች፣ በቀበሌ ገበሬዎችና በአብዮታዊ ወጣቶች ይወሰዱ የነበረት ነፃ ሕዝባዊ እርምጃዎች ነበር:: ይህ ወቅት በተጨማሪ አብዮታችን ከብቸኝነት መውጣት የጀመረበትና የአንዳንድ የወዳጅ አገሮችን ድጋፍ ማግኘት የጀመረበት ወቅት በመሆኑም ዓይነተኛ ይሆናል::

የመጨረሻዎቹን ሁለቱን በሚመለከተው፣ባንድ ወገን በየፋብሪካው፣ በየትምህርት ቤቶችና ቀበሌዎች ከሚካሄዱት ሕዝባዊ ነፃ እርምጃዎች አንስቶ እስከ መጋቢት 1969 "የመንጥር ዘመቻ" ድረስ የነበረት ተጥቃዊ እንቅስቃሴዎች የሚታወሱ ናቸው:: በሌላው በኩል ከፊዴል ካስትሮ/ሶምበርተስና ሌሎችም መሪዎች አንስቶ ይጎርፉ የነበሩት የውጭ አገር መልዕክተኞችን የባህል ተጓዦች ሁሉ ይታወሳሉ:: ይህ የመጨረሻው በራሱ አራሱን የቻለ ታሪክ ነው::...

ህብረቱን በሚመለከተው በኩል፣ ከጥር 24 እስከ የካቲት 18/69 ድረስ በተደረጉት ስምንት ስብሰባዎች ብቻ፣ የህብረቱ "የጋራ መግለጫና መርሃ ግብር" ፀድቀው ይወጣሉ:: የህብረቱ ኮሚቴ በስንት የሃላፊነት ሥራዎች መካከል በ24 ቀኖች ውስጥ ብቻ ያገባደደው ሥራ እጅግ የሚያኮራና የሚያስደስት ነበር:: በየካቲት ወር የህብረቱ "የጋራ መግለጫና መርሃ ግብር" ሲወጣም፣ እነዚሁ እንደ አንድ ታላቅ ድል ያልቆጠራቸው አንድም ሃቀኛ ተራማጅ፣ አንድም የአብዮቱ ወገን አልነበረም:: በዚያን ጊዜ በህብረቱ አባሎች መካከል "እውነተኛ ልዩነቶች" ቢኖር በብሄረሰቦች ጥያቄ ላይ ነበር:: በግልፅም የተነገረው በዚህ ጥያቄ ላይ ስላሉት ልዩነቶች ብቻ ነበር:: መኢሶንን በሚመለከተው በኩል፣ በነዚያ ውይይቶች ላይ በተለይ በዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ ላይ ቀደም ሲል ከጠቀስነው ስምምነት ላይ በመደረሱ ከፍተኛ መርካት ሰፍኖ ነበር:: ይሁንና፣ በደርግና በአብዮታዊ ሰደድ /="ደርግ"/ መካከል ያለው ሁኔታ አሁንም አሳሳቢ ሆኖ ቀርቶ ነበር:: ወደኋላም እንደታየው፣ ለምሳሌ አንድ ነገር ደርሶ ወደደርግ ሲኬድ፣ "ይህ የአብዮታዊ ሰደድና የህብረቱ ጉዳይ ነው" ይባል ነበር:: ወደነርሱ ሲኬድ ደግሞ፣ "ይህ የደርግ ጉዳይ ነው" ይባል ነበር::

### 4.3. ሁለተኛው ወቅት

የመጀመሪያው ወቅት፣ አያሌ የህብረት ግንኙነቶችና ሥራዎች የተከናወኑበት ወቅት ነበር:: ለዚህ ምንም ጥርጥር የለውም:: ነገር ግን በዚህ ወቅት ውስጥ ህብረት የነበረውን ያህል፣ ፀረ ህብረት ሥራዎችም እያቆጠቆጡ መታየት ጀምረው ነበር:: አንዳንድ ምልክቶች መታየት እንደጀመሩም፣ መኢሶን ለመጀመሪያው ተዕግስትና ትሁትና በተመላባቸው አቋሞች ድምፁን ያሰማል:: በጥርና የካቲት ወሮች በስብሰባዎች ላይ የሚከተለውን ጽፎ ነበር:-

ሰሕድ 50/ጥር 30.1969

ይህ እትም፣ የመኢሶንን ታሪክ ባጭሩ ለማሳወቅ የተደረሰ ነበር:: ጽሑፉ በወቀቱ እንዳመለከተው፣ "የዚህ ዓይነቱ ትንተና አሁን ባለንበት ወቀት /ጥር 69/ አስፈላጊ የሆነበት አንደኛው ምክኒያት" እንደሚከተለው ተገለጸ ነበር::

"ከማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ጋር በመጀመሪያ ደረጃ ህብረትን፣ ከዚያም ውህደትን በመፍጠር፣ የወዛደሩን ፓርቲ ለመመስረትና ለመገንባት ጽኑ ፍላጎት አለን:: እነዚህ የህብረት ጓደኞቻችን የመኢሶንን አጭር ታሪክ ቢያውቁ፣ የበለጠ መግባባትንና መቀራረብን እንደሚፈጥር እናምናለን:: የዚህ ዓይነት ዕውቀት አጉል ጥርጣሬንና አለመተማመንን ሊያስወግድ ይችላል" /2/

ሰሕድ 52/ የካቲት 20. 1969

"የተራማጆችን ህብረት መፈጠር ሁሉም ሰው በቃል ቢደግፈውም፣ በገቢር ግን በሁሉም ወቅት አንጂ፣ ብዙ ፀረ ህብረት ሥራዎች ይካሄዳሉ:: የኢትዮጵያ አብዮት አሁን ባለበት ሁኔታ፣ መኢሶን የሚያቀርበው ሃሳብ ዲሞክራሲያዊና ሃቀኛ ውይይት፣ ሸኩቻን፣ አሉባልታንና የስም ማጥፋት ዘመቻን እንዲተዉ ነው:: እነዚህኞቹን መቀጠልና የህብረትን መቀራረብ አዝማሚያዎች ማደናቀፍ፣ ፍፁም አብዮታዊ ሃላፊነትን መዘንጋት ይሆናል::"

እነዚህ ቃላቶች በወቅቱ ያለምክንያት የተጻፉ አልነበሩም:: በዚያ ሰዓት በመኢሶን ላይ የሆኑ ያልሆኑ የማጥላላት ዘመቻዎች ተጀምረው ነበር:: የሆኑ ያልሆኑ ቅጽሎች /"ጠባብ ቡድን"፣ ጠባብ ብሔረተኛ".../ ይለጠፉበት ነበር:: አያሌ የፈጠራ ክሶች እናት ባናት ይተረተሩ ነበር::... ወዘተ::

ደግሞ፣ የነዚህ ሁሉ ፀረ ህብረት ፈጣሪዎች ሌሎች ሳይሆኑ፣ አንዳንድ የህብረቱ አባል ድርጅቶችና ግለሰቦች ጭምር ነበሩ:: ዛሬ እነዚህ ክፍሎች "መኢሶን በአሉባልታ ይደናገጣል:: አድሃሪያን ባወሩና ጡሩንባቸውን በነፉ ቁጥር የንዑስ ከበርቴው ወኔው ይከዳዋል"...ወዘተ በማለት እንደተመለሰብን በገበናቸው፣ "ጅራፍ ራሱ ተገርፎ ራሱ ይጮሃል" ከማለት በስተቀር የምንመልስላቸው ተጨማሪ ነገር አይኖረንም::

የሆነው ሆኖ፣ ሸኩቻውና አሉባልታው፣ የፈጠራ ክሶችና የስም ማጥፋት ዘመቻው በመጋቢት ወር እየባሰ ይመጣል:: ከነዚህ ፀረ ህብረት ዘመቻዎች መብዛትና መባዛት የተነሣ፣ ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለ ማሪያም በመጋቢት ወር ላይ አራት የመኢሶንን አባሎች አቢሮአቸው ድረስ ጠርተው ለሁለት ሰዓት ያህል ያነጋገሯቸዋል:: የታሪክ ምፀት መስሎ ቢታይም፣ በዚያን ጊዜ በቤተ መንግሥት ውስጥ "ከአሉባልታዎችና በፈጠራ ክሶች ላይ" ውይይት ሲካሄድ፣ በዚያኑ ሰዓትና ደቂቃ ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ "የመንጥር ዘመቻ" እየተካሄደ ነበር:: በሁለቱ ሁኔታዎች /"ህብረትና" ፀረ ህብረት/ መካከል የነበረው ቅራኔ እስከዚህ ድረስ አፍጦና አግጥጦ ነበር ለማለት እንችላለን::

ለማንኛውም፣ በውይይቱ ወቅት መኢሶን ለሚነሡበት አሉባልታና የፈጠራ ክሶች አንድ በአንድ ማብራሪያዎቹንና መልሶቹን ይሰጣል:: "ገለልተኛ ዳኛ" ይጠይቃል:: በተጨማሪ፣ አንደዚህ ዓይነት ውይይት ከሌሎቹም ድርጅቶች ጋር ተራ በተራ እንዲደረግ ሃሳብ ያቀርባል:: ዲሞክራሲያዊና ሃቀኛ የሆነን የተራማጆች ህብረት በጋራ ለመመሥረት ጽኑ ፍላጎት እንዳለው ደጋግሞ ያስታውቃል::...

የተባለው ዓይነት ውይይት ከሌሎች የህብረቱ አባል ድርጅቶች ጋር ተራ በተራ ተካሂዶ እንደሆነ፣ መኢሶን የሚያውቀው ነገር የለም:: መኢሶን የሚያውቀው ነገር ቢኖር፣ በተፈጠሩት ጥርጣሬዎችና እንቅፋቶች ምክንያት ብቻ፣ የህብረቱ ስብሰባዎች ሙሉ በሙሉ መቀዛቀዛቸውንና መቋረጣቸውን ነው::

ከየካቲት 18 እስከ ግንቦት 10/1969 ድረስ የተደረጉት የህብረቱ ስብሰባዎች ሁለት ብቻ መሆናቸውን ነው:: ሁኔታዎችን ለማመዛዘን እንዲረዳን፣ በመጀመሪያው ላይ በአማካይ ቁጥር በየሰባቱ ቀን አንድ ስብሰባ ሲደረግ፣ በሁለተኛው ዙር አንድ ስብሰባ የተካሄደው በ35 ቀኖች ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ነበር ማለት ነው:: በዚህ ጊዜ ውስጥ፣ ገና ከህብረቱ የመጀመሪያ ቀኖች ተረቅቆ የነበረው የህብረቱ የመተዳደሪያ ደንብ የቀኖችን ብርሃን ለማየት እድል ሳያገኝ ቀርቶ፣ የጠረጴዛ መሳቢያዎችን ቢያጥቅ ከርሟል:: በምትኩ ተፋፍሞ የነበረው፣ በመኢሶን ላይ ይደረግ የነበረው ዘመቻ ነበር:: ስለሆነም፣ በመጋቢት ወር አጋማሽ፣ መኢሶን የሚከተለውን እንዲጽፍ ተገደደ::

ሰሕድ 53 – መጋቢት 15/69

"... አነ ዓለማየሁ ኃይሌ ከሰኔ 68 ጀምሮ ጽ/ቤቱ ላይና በተለይም ደግሞ በድርጅታችን ላይ ኃይለኛ ዘመቻን በይፋ ሲያካሂዱ እንደቆዩ፣ ጽ/ቤቱን የመኢሶን ጽ/ቤት ነው በማለት እንዲፈርስ መጠየቃቸውና በመጨረሻም ይህንኑ የማፍረስ ዓላማቸውን በጉልበት ከሥራ ላይ ለማዋል እንደሞከሩ ይታወቃል::

"አሁን በጥር 26 በደርጉ ውስጥ የነበሩት የኢሕአፓና የኢምፔሪያሊዝም ወኪሎች ከተደመሰሱ በኋላ፣ በጽ/ቤቱና በርሱም ሳቢያ በመኢሶን ላይ የሚደረገው ዘመቻ በተፋፋመ ሁኔታ ቀጥሏል:: የዚህ ዘመቻ ዋነኛ ኃላፊዎች በየቦታው የተሰማሩ አድሃሪ ቢሮክራቶች ናቸው:: በሲዳሞ፣ በከፋ፣ በሌሎችም ክፍለ ሃገር ቢሮክራሲው ጽ/ቤቱን በሚመለከተው በኩል ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ተሸጋገረ"





ካድሬዎቻችን እስከማስገደልና እስከማሳሰር ደርሷል::"

እንደዚህ ያለው ዘመቻ በመኢሶን ላይ በሚያዝያ፣ ግንቦት፣ ሰኔ፣ ሃምሌና ነሐሴ ወሮች ውስጥ ተስፋፍቶ እንደቀጠለ ነበር:: በነዚህ ወሮች ውስጥ መኢሶን ያሰማቸው ጥያቄዎች ጩኸት ብቻ እንጂ፣ እንዲያውም ፍሬ ሊሰጡ ሳይችሉ ቀርተዋል:: በዚህ ጊዜ ውስጥ ባንድ በኩል እንደዚህ ያለው ዘመቻ እየተካሄደ፣ በሌላው በኩል ደግሞ፣ አንዳንድ የህብረቱ አባል ድርጅቶችና ግለሰቦች ጭምር በመኢሶን ላይ ግልፅና ኃይለኛ ዘመቻ ይከፍታሉ:: በተለይ ከሚያዝያ ወር የሜይ ዴይ በዓል በኋላ፣ ፀረ መኢሶን ዘመቻ ተፋፍሞ ይቀጥላል::

በሚያዝያ ወር በተደረገ አንድ የህብረቱ ስብሰባ ላይ፣ "በሜይ ዴይ ዕለት፣ እያንዳንዱ ድርጅት የራሱን አርማ፣ የህብረቱን ድርጅቶች አርማዎችና መፈክሮች ይዞ እንዲወጣ" ከስምምነት ላይ ይደረሳል:: መኢሶን ስምምነቱን አክብሮ ይሠራል:: በዚሁ መሠረትም በአዲስ አበባና በክፍለ ሃገር ከፍተኛ ዝግጅቶችን ያደርጋል::... ወዘተ ይሁንና፣ ዕለቱ ከመድረሱ ሁለት ቀኖች በፊት "የእምነት ክህደት" ክርክሮች ይነሳሉ:: "ተስማምተናል፣ አልተስማማንም" የሚል... በመጨረሻም፣ በዓሉ እንደነገ ሊሆን እንደዛሬ፣ መኢሶን ዝግጅቱን እንዲያቆም ትዕዛዝ ይደርሰዋል:: መኢሶንም በዚህ ጊዜ፣ ትዕዛዙ ዘግይቶ እንደመጣ በማስታወቅ፣ ምንም ለማድረግ እንደማይችል ያስታውቃል:: ትዕዛዙን አፈጻጸም ለመተርጎም በቂ ጊዜ እንደሌለው ያስረዳል:: ትዕዛዙን በሥራ ይውላል:: ሜይ ዴይ 1969 በተከበረበት መልክ ተከበረ

ነገር ግን ያበለቱ ደማቅ የነበረውን ያህል፣ ብዙ ድክመቶችም ነበሩበት:: መኢሶንም በወቅቱ አድርጎት በነበረውም ግምገማ፣ ከዚህ በታች የምንጠቅሰውን ጽፎ ነበር:: ይሁንና፣ ከዚያ በፊት ደግሞ፣ በጊዜው ባንዳንድ አካባቢ የነበረው ስሜታዊነት፣ ከዚህ በታች የምንጠቅሰውን አጠቃላይ ግምገማ በጥሞና ከመመልከት አግዶ እንደነበርም ባናስታውስ አናልፍም:: እስቲ የመኢሶንን ግምገማና አቋም እንደገና አስታውሰን እንመልከተው:—

ሰሕድ 54 – ሚያዝያ 30/69

የዘንድሮውን /1969/ ሰልፍ በመመልከት፣ ከተያዙት መፈክሮች ምናልባት እስከ 80 በመቶው የፖለቲካ መፈክሮች ነበሩ:: 'አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት!' 'የተራማጆች ህብረት ይለምልም'፣ 'ሃቀኛ የወዛደር ፓርቲ እንመሥርት'፣ 'ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ'፣ 'ዲሞክራሲያዊ መብቶች አሁኑኑ'፣ 'የመንጥር ዘመቻ ይቀጥል'፣ 'ለአብዮታዊው የዘመቻ ጥሪ ተዘጋጅተናል'... የሚሉት በብዛት የወጡ መፈክሮች ነበሩ:: ሁሉም የኢትዮጵያን አብዮት አንገብጋቢ ጥያቄዎች የሚያነሱ ናቸው:::

መፈክሮችን በሚመለከተው በኩል የሚያበረታታና ተስፋ የሚሰጥ ሁኔታ ሲታይ፣ የሰልፉን ዝግጅት በሚመለከተው በኩል ደግሞ በርከት ያሉ ድክመቶች ታይተዋል:: ባጠቃላይ፣ ሰልፉ የዲሲፕሊን ጉድለትን አሳይቷል:: ለምሳሌ ብዙ ድርጅቶች የራሳቸውን የሥነ ሥርዓት ጠባቂ አላሰለፉም ነበር:: በርከት ያሉ በዛኞቹ በየድርጅቱ መካከል ከመግባታቸውም በላይ፣ ቅጥ የለሽ አሰላለፍ፣ ብዙ ድንፋታና ሁካታን አልፎ አልፎ አሳይተዋል::

እነዚህ የዝግጅትና የዲሲፕሊን ጉድለቶች ሲሆኑ፣ በተለይም መኢሶንን በሚመለከተው በኩል፣ አንዳንድ የድርጅታችን ደጋፊዎች የፖለቲካ ስህተቶችን ፈጽመዋል:: 'መኢሶን ፓርቲያችን ነው'፣ 'መኢሶን አስታጥቆናል' የሚሉ የቃል መፈክሮች ተደጋግመው ተሰምተዋል:: እነዚህን መፈክሮች ያሰሙ የነበሩት ግለሰቦች የመኢሶን ደጋፊ ሆነው የተሳሳቱና የድርጅታችንን የፖለቲካ መሥመር በቅጡ ያልተገነዘቡ ጓዶች ናቸው:: አለበለዚያም፣ በአሉባልታ አካባቢ በሚደረገው ትግል ላይ ብቻ ስላተኮሩ፣ ለጊዜው በስሜት ብቻ በመገፋፋት የተሳሳቱ ጓዶች ናቸው:: መኢሶን ፓርቲም አይደለም:: ይህንን በፕሮግራሙ ውስጥ ጭምር ገልጿል፣ በተደጋጋሚ በጽሑፎቹ ውስጥ ከሌሎች ሃቀኛ ተራማጆች ጋር ህብረትንና ከዚያም ውህደትን አድርጎ የወዛደሩን ፓርቲ አብሮ ለመፍጠር እንደሚታገል ገልጿል:: ትጥቁን በሚመለከተው በኩል፣ መኢሶን ከሌሎች ሃቀኛ ተራማጆች ጎን በመሰለፍ፣ ሰፊው ሕዝብ እንዲነቃ እንዲደራጅና እንዲታጠቅ ታግሏል:: ሰፊውን ሕዝብ ያስታጠቁትና በማስታጠቅ ላይም የሚገኘው ግን ጊ.ወ.አ.ደርግ መሆኑ የታወቀ ነው::

የአሁኑን ሰልፍ አይነተኛ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ፣ የተራማጆች ህብረት አባል ድርጅቶች፣ ማለትም የመኢሶን፣ የማሌሪድ፣ የኢጭአት፣ የወዛደር ሊግና የአብዮታዊ ሰደድ አርማዎች በይፋ መውጣታቸውና ወዛደሩ ለህብረት የቆመ መሆኑን ማሳየቱ ነው:: እንደዚሁም፣ ካምናው ይልቅ ዘንድሮ፣ የመኢሶን – የማሌሪድ አርማዎችና መፈክሮች በርከት ብለው በመታየታቸው ባንዳንድ የህብረቱ ጓደኞቻችን ዘንድ ቅሬታ እንደተፈጠረ ሲሰማ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ባንዳንድ የመኢሶንና የማሌሪድ ጓዶች ዘንድ፣ በወዛደሩ ውስጥ የሰፈነውን ድርጅታዊ ሥራ የማጋነን አዝማሚያ ይታያል::

ለጓደኞቻችን ሁሉ የምንነግረው ነገር ቢኖር፣ የሰልፉን አንድ ጎን ብቻ ከማየት፣ ጠቅላላውን እንድንመለከት ነው:: ከተሰለፉት 150 ወይንም 200 ሺህ ወዛደሮች

ሠራተኛ፣ የማንንም ይሁን የማንን አርማ ይዘው የወጡት ምናልባት 15 ወይንም 20
በመቶ ያህሉ ብቻ ናቸው!! ይህም እንግዲህ ሃቀኛ ተራማጆች ገና ከወዝአደሩ ጋር
በሚገባ አለመዋሃዳቸውን ስለሚያሳይ፣ ለወደፊቱ፣ የኢትዮጵያ አብዮታዊያን የሚ
ጠብቃቸው ተግባር በጣም ከፍተኛ ነው ማለት ነው:: ነገሮችን ከሁሉም ማዕዘን
ሳይሆን ከጎዱ ጎን ብቻ፣ የወደፊት ዕድገታቸውን ሳንገመግም የዛሬውን ብቻ ከተመ
ለከትን እንሳሳታለን::
ድርጅታችንን በሚመለከተው በኩል፣ መኢሶን ለተራማጆች ህብረት መጠንከር፣ ለዲሞክ
ራሲያዊ መብቶች፣ ለወዝአደሩ ፓርቲና ለአብዮታዊ ግንባሩ መፈጠር እስከመጨረሻው
ድረስ ይታገላል::"

መኢሶን ይህን ሁሉ ቢናገርም፣ አቋሙን በግልጽ ቢያሳውቅም፣ ስህተቶችን ለማስረዳት ቢጥ
ርም፣... ወዘተ፣ እንዳለነው በጊዜው የነበረው ስሜታዊነት ነገሮችን በአንክሮ ከመመልከት
አገደ:: ይልቁኑ በመኢሶን ላይ የሚደረጉት ዘመቻዎች ተፋፋሙ ነጉዱ:: አንዳንዶቹ "ለመ
ኢሶን ጠባብ ቡድንነት" ከዚህም የበለጠ ማስረጃ አንደሌለ ያሳውቁ ጀመር:: ሌሎች መኢሶንን
"እጁሱ ሊሕስ ፲" አድርገው ሳሉት:: ሌሎቹም "የመኢሶንን የስልጣን ጥም" አነበቡ:: ስምምነቱ
ተረሳ:: በጭፍን ተከዩ:: በየቱኩ፣ ጥርጣሬዎችና አለመተማመን ሠፈሮችን ሁሉ አዳረሱ::
በተጨማሪ፣ በተለይም በመጀመሪያው ላይ፣ በክፍለ ሃገር ውስጥ ካድሬዎችንና ደጋፊዎችን ማሳ
ደድና ማሰር ተፋፋሞ ቀጠለ:: በህዝብ ድርጅት ጽ/ቤት ሳቢያ በመኢሶን ላይ የሚደረገው ዘመቻ
በራፖር ከቦች የደርግ ጽ/ቤትን በር አጥለቀለቀው:: በወዝአደሩ አካባቢ /በአቃቂና በወንጂ
.../ ከፍተኛ ሽኩቻ ተቀሰቀሰ:: መኢሶንን ለመከሰስ "ኤረኛዎች" ይቃረሙ ጀመር:: ስለላው
ጦፈ:: ... ወዘተ::
በግንቦት ወር የህብረቱ ስብሰባ እንደገና ሲቀጥል፣ ሁኔታዎች ከዚህ በላይ እንደገለፀነው
በአያሌ ፀረ ህብረት ሥራዎች ተወሳስበው ነበር::

4.4. ሦስተኛው ወቅት

የህብረቱን ጉዳይ በሚመለከተው በኩል፣ የግንቦት ወር ባንዱ ወገን በጥቂት ቀኖች ውስጥ
እንደገና አያሌ የህብረት ስብሰባዎችን ያየ ሲሆን፣ በሌላው ወገን በአያሌ የፖለቲካ ጥያቄ
ዎች ላይ ከፍተኛ የአቋም ልዩነቶች ገሃዱ የወጡበት ጊዜም ነበር:: ቀደም ሲል በአሉባልታ
ዎችና በረጠሩ ክሶች የተፈጠረው አለመተማመንና እርስ በርስ መጠራጠር ከከፍተኛ ደረጃ ላይ
የደረሱበት ወቅት ነበር::
ከግንቦት 10 እስከ 30 ባሉት ጊዜያት ውስጥ ብቻ 13 ስብሰባዎች ይካሄዳሉ:: ይህናው
በአማካይ ቁጥር በአንድ ቀን ተኩል አንድ ስብሰባ ማለት ነበር:: ስብሰባዉ በተጨማሪ ወኪ
ሎች /ከያንዳንዱ ድርጅት አሁን ሁለት ሁለት ተጨማሪ ወኪሎች ታክለው/ የተካሄደ ነበር::
ከነገዚህም ቃለ ጉባዔዎችን በደንብ መያዝ ተጀምሮ ነበር::...
ይሁንና ደግሞ፣ እነዚህ ስብሰባዎች የዋሉት እስከዚህም ድረስ ለአዲስ ነገር ሳይሆን፣
በሰነድ ቁ.60 እንደተገለጸው፣ "በየካቲቱ የጋራ መግለጫ ውስጥ በፀደቁት የውይይትና
የስምምነት ነጥቦች ላይ እንደገና "ለመከራከር" ነበር::
ነገር ግን ስብሰባዎቹ እርስ በርስ ባለመተማመን አየር የታመቁ ነበሩ:: በመኢሶን ላይ
የሚደረጉት ዘመቻዎች ሁሉ እንደዕውነት ተወስደው ለፍርድ የቀረቡባቸው ስብሰባዎች ነበሩ::
መኢሶን፣ እንደሚባለው "በመሃሉ ገዢት" ጥምር፣ አቋሙን ደጋግሞ ቢገልጽም፣ ጥርጣሬዎች
ለመወገድ ያልቻሉበት ስብሰባዎች ነበሩ::
የዚያኑ ያህል ደግሞ፣ የግንቦት ወር ስብሰባዎች፣ የድርጅቶች አሰላለፍና የፖለቲካ
አቋም ለውጦች በገሃዱ የተከሰቱባቸው ስብሰባዎች ነበሩ:: በዚህ አንፃርም፣ ወዝ ሊግ፣
ማሌሪድና አብዮታዊ ሰደድ በአንድ ወገን ተሰልፈው ነበር:: ኢጭአትና መኢሶን ደግሞ በሌላው
ወገን ሁነው ነበር:: ደግሞ ከሁሉም ድርጅቶች ይልቅ፣ ማሌሪድ አስደናቂ የሆኑ የአቋም
ለውጦች ያሳየባቸው ስብሰባዎች ነበሩ:: እንደዕውነቱ ከሆነ፣ በነዚያ ስብሰባዎች ላይ የማ
ሌሪድ አቋም ለውጦች ለሁሉም ድርጅቶች እጅግ ፈጣን ከመሆናቸው የተነሳ፣ ሁሉም ቢሆኑ ለማመ
ን፣ ለመከተልም ተቸግረው ነበር ብንል ፈፅሞ ስህተት አይሆንም:: የማሌሪድ መሪዎች ከኢሕ
አፓ ዘመናቸው አንስቶ ያደረጉት ጉዞ በራሱ እንደዚሁ አስደናቂ ነው::
የነዚያ ስብሰባዎች ቃለ ጉባዔ በሁሉም ድርጅቶች ዘንድ ለታሪክ ተቀምጧል:: ሁኔታዎች
ሲጠይቁ የቀኖችን ብርሃን ማየት አይቀርም::
ለማንኛውም፣ ሰነድ ቁጥር 60 እንዳለው "በየካቲቱ የጋራ መግለጫ ውስጥ የፀደቁት
የውይይትና የስምምነት ነጥቦች እንደገና ለውይይት እስከመቅረብ የደረሱት"
"በነዚህ ነጥቦች ላይ የያንዳንዱ ድርጅት አቋም ግልፅ ባይሆን በመቅረቱ ቁርቱ
ባይሆን፣ በድርጅቶች መካከል የመጠራጠር መንፈስ ሊጠፋ ባለመቻሉ ነው:: መኢሶን
በልዩ ልዩ እትሞቹ ደጋግሞ እንደገለጸው ሁሉ፣ ይህም ጥርጣሬ ሊጠፋ ያልቻለው፣
ህብረታችንን ገና ከፊውዳላዊው ሥርዓት የአስተባበር ዘዴዎች ባለመላቀቁና ዲሞ
ክራሲያዊ መብቶችም ሆኑ ዲሞክራሲያዊ የአስተባበርና የአሠራር ዘዴዎች በፍፁም
ያልተለመዱ በመሆናቸው ነው::"





ዕርግጥ፣ ዛሬ ደግሞ በተጨማሪ ደርግ /=አብዮታዊ ሰደድ/ የመኢሶን "የሥልጣን ጥም"
የሚለውን የአድሃሪዎች ቅስቀሳ እንደ ዕውነት በመውሰዱም ጥምር ነው ለማለት እንችላለን::
በመሆኑም፣ መኢሶን የሚገለፅባቸው የፖለቲካ አቋሞች ላይ ሁሉ ከፍተኛ ጥርጣሬዎች አደሩ::
አሉባልታዎችና የፈጠራ ክሶች ሁሉ እንደዕውነት ተወሰዱ::
"የሥልጣን ጥም" የሚባለው ነገር ለማገናኘት ተሞከረ:: በነገሮች ውስጥ ሁሉ "የመኢሶን
"መኢሶን ለመስፋፋት፣ ለማበጥ፣ ለመፈንጠቅ፣ ሌሎችን ለመዋጥ::.." መኢሶን የሚያቀርባቸው ጥያቄ
ዎችና ሃሳቦች ናቸው በሚል ተገመቱ:: መተማመን ጠፋ:: ውይይቶች ለመኢሶን እጅግ አስቸጋሪ
ሆነው ነበር::

የዚህ ሁሉ መሠረት ግን፣ መሠረታዊ በሆኑት የፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ እየተቀጠሉ የመጡት
የመሥመር ልዩነቶች ነበሩ:: ልዩነቶቹ በየካቲቱ ወር በብሄረሰቦች ጥያቄ ላይ "ካቻ" የነበረ
ትን ያህል፣ አሁን ደግሞ በዲሞክራሲ መብቶች፣
በህዝባዊ ነፃ አርምያ፣ በራስን መቻል ጥያቄዎች፣ በቢሮክራሲው፣ በተቋሙ፣ በአብዮታዊ አመራር፣
እንደሚታወሰው እነዚህ ሁሉ የአብዮቱ ጥያቄዎች፣ ላይ ሁሉ አያሌ ልዩነቶች መታየት ጀመሩ::
1970/ ለውይይት ጋበዘ በነበረበት ጊዜ፣ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አንድ ሰሞን /ህዳር
ነገር ግን በጥያቄዎች ላይ ተደምሮ የውይይት አርዕስት እንዲሆኑ የተገለፁ ነበሩ::
ርበት የነበረው የዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ ላይ እንኳ፣ ውይይቱ ወዲያውኑ ታፈነ:: ውይይቱ ተጀም
ተደረገበት:: ቀደም ብለን ጠቀስን እንዳመለከትነው፣ ወዲያውኑ ፀረ ዲሞክራሲያዊ አንዳ
ላይ "መኢሶን በርዕዮተ ዓለም ትግል ተሸንፏል:: በተለይ በዚህ የዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ
በሚል የተበየነው ፍርድ ለመስጠት የበቃነው ገና አሁን ነው:: ተጋልጧል:: ሰፊው ሕዝብ አልተቀበለውም"
ይሁንና፣ በተነሱት የአብዮቱ ጥያቄዎች ላይ ሁሉ አሁንም ቢሆን በሃቅ የሚያከራክሩ አያሌ
ጉዳዮች ተሸፍነው እንዳሉ ናቸው:: ስለዚህም፣ "አሰባበሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ" ነውና፣ የኢት
ዮጵያ ሕዝቦች በነዚህና በሌሎችም ጥያቄዎች ላይ አንድ ሁኔታና እንደጊዜው እየደጋገሙ
መመለሳቸው አይቀርም:: አብዮታዊው ትግል በሁለት መሥመር ትግል እንደሚቀጥል ፍፁም
የሚያጠራጥር ጉዳይ አይደለም::

ወደ ርዕሳችን እንመለስና፣ ግንቦት 69 የብዙ ስብሰባዎችን አያሌ የአቋም ለውጦች
የታዩበት ወቅት የሆነውን ያህል፣ በመኢሶን ላይ የተፋፋመው ዘመቻ እጅግ የጦፈበት ወቅትም
ነበር:: ባንዱ ቃል፣ "ህብረትና" ፀረ ህብረት አንድ አምሳል፣ አንድ አካል ሆነው የታዩበት
ወቅት ነበር:: ስለዚህም ነበር፣ መኢሶን በነበሩት ፀረ ህብረት እርምጃዎች ላይ በየእትሞቹ
ላይ ደግሞ ደጋግሞ እንዲያመለክታቸው የተገደደው:: ይህንኑም ሃቅ፣ የሰነዱን ቁጥሮች አለፍ
አለፍ በመጥቀስ ለማሳየት ይቻላል:: እንመልከተው:-

ሰነድ 55 – ግንቦት 7/69

"የተራማጆችን ህብረት ለማጠናከርና አብዮታዊያን በይበልጥ ከሰፊው ሕዝብ ጋር እን
ዲቀራረቡ ለማድረግ፣ የወዝአደሩን ፓርቲና ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባሩን በመፍጠር
የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ ከዳር እስከዳር ለማንቀሳቀስ፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶች
እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ፣ እነዚህ መብቶች በፍጥነት ለሰፊው ሕዝብ መሰጠት እን
ዳለባቸው መኢሶን ያምናል:: በአሁኑ ወቅት በተራማጅ ድርጅቶች መካከል ኃይለኛ
ሽኩቻና አለመግባባት የሚፈጠረው፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶች በሌሉበት፣ ዕውነተኛ የል
ዩነት ነጥቦች እንዳሉ እነርሱን በይፋ አውጥቶ በሰፊው ሕዝብ ፊት ለክርክር
ለማቅረብ ስላልተቻለ ነው:: እነዚህ መብቶች በሌሉበት ሁኔታ፣ በድርጅቶች መካከል
የሚካሄደው "ትግል"፣ በአሉባልታ፣ በሃሜት፣ በጥርጣሬና በስም ማጥፋት ዘመ
ቻዎች ላይ የሚያተኩር ከመሆኑም በላይ፣ የዚያ ዓይነቱ "ትግል" ሰፊውን ሕዝብ
በማስተማር ፈንታ ያወናብዳል፣ በመሰብሰብ ፈንታ ያከፋፍላል...
"መኢሶን የሚፈልገው ሃቀኛ የተራማጆች ህብረትና ከዚያም ዕውነተኛ የወዝአደሩ
ፓርቲ እንዲፈጠር፣ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ተመሥርቶ ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ
ከዳር እስከዳር እንዲያንቀሳቅስና፣ ይህ ሕዝብ እንደ አንድ ሰው ሆኖ በስተ
ጠላቶቹ ላይ እንዲነሳ ለማድረግ ነው::"

ሰነድ 57 – ሰኔ 7/69

"ድርጅታችን ከፕሮግራሙ መውጣት በፊትም ሆነ በኋላ፣ በርከት ባሉ ጽሑፎቹ፣ ምና
ልባት ከማንኛውም ሌላ ድርጅት ይበልጥ፣ ደጋግሞ ስለወዝአደሩ ፓርቲ አመሠራረት
ጽፏል:: ችግሩ በፊውዳላዊት ኢትዮጵያ፣ የክርክር መብትም ሆነ ልምድ ስላልነበረና
ዛሬም ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለሰፊው ሕዝብ ገና ስላልተለቀቁ፣ የሚደረገብን ዘመቻ
በሃቅና ተጨባጭ ነገሮችን እያዩ በማመዛዘን፣ ለዕውነት በመቆም ሳይሆን፣ ቀደም
በነበረው የመደብ ትግል ስልት፣ በወሬ፣ በአሉባልታ፣ ከንቱ ጥርጣሬን በመንዛት
ላይ የተመረኮዘ ሆኖብን ነው:: የኢትዮጵያን አብዮታዊያንና ሰፊውን ሕዝብ የምን
ለው፣ የኛን ብቻ ባይሆን የሁሉንም ድርጅቶች ጽሑፎች በሚገባ አንብቡ፣ የሁሉንም
ድርጅቶች የቅስቀሳ ይዘት አጥኑ፣ በጽሑፍና በተግባር መካከል ያሉትንም ግንኙ
ነቶች በሚገባ አስተውሉ ነው..."

የሰሕድ እትሞቻችን ሁሉ እያገላበጥን ጥቀሶችን በማቅረብ መቀጠል እንችላለን፡፡ ይሁንና፣ ጽሑፉ አለቅጥ ይረዝምብናል፡፡ ስለዚህም፣ አንባቢያችን በተለይም ወደ ሰሕድ 59 /4.11.69/ እና ሰሕድ 60 /21.11.69/ ጋብዘናቸው ብቻ እዚህ ላይ እናቁም፡፡ ከዚህ በላይ ተጠቅሰው በቀረቡት አንቀጾች ብቻ እንኳ፣ የመኢሶን ያልተቋረጠና ያልተናወፀ አቋም ግልፅ ሆኖዋል ብለን እንገምታለን፡፡ ወደሚቀጥለው ክፍል እንሻገር፡፡

## 4.5. የህብረቱ የመተዳደሪያ ደንብ ጥያቄ

እንደማናቸውም ድርጅት ሁሉ፣ የህብረቱም ድርጅት እንደተመሠረተ የመተዳደሪያ ደንብ እንደሚያስፈልገው የታወቀ ነው፡፡ ስለዚህም በየካቲት 69 የህብረቱ የጋራ መግለጫና መርሃ ግብር በወጡ በኋላ፣ ወዲያዉኑ የሚከተለው ተግባር፣ በተመሠረተው የህብረቱ ድርጅት የመተዳደሪያ ደንብ ላይ ተወያይቶና ተስማምቶ መስመርና ሥርዓት ማስያዝ ነበር፡፡ እንደዕውነቱም ከሆነ፣ ይህ ግልፅ የሆነ ተግባር ወዲያውኑ በየካቲት ወር ተጀምሮም ነበር፡፡ በዚህ ወር ውስጥም፣ የህብረቱ የመተዳደሪያ ደንብ ረቂቅ ለውይይት ቀርቦ ነበር፡፡

ሆኖም፣ በመኢሶን ላይ በነበረት ጥርጣሬያች ምክንያት፣ ውይይቱ ለረጅም ጊዜ ታገደ, ቆየ፡፡ መኢሶን በመተዳደሪያው ደንብ ላይ፣ ባስቸኳይ ውይይት እንዲደረግ ደጋግሞ በወተወተም፣ "እምቢ ብቻ!!" በሚሉ መልሶች ነገሮች ሁሉ እንዲራዘሙ ተደረገ፡፡ እና እንደምናስታውሰው፣ የመተዳደሪያ ደንቡ ለውይይት ሊቀርብ የቻለው፣ የጋራ መግለጫው ከወጣ ከአምስት ወሮች በኋላ፣ በሃምሌ 1969 ነበር፡፡ በመጨረሻም፣ በዚህ ወር ውስጥ ይፀድቅና የፍችን ብርሃን ለማየት ይበቃል፡፡ ይሁንና፣ በዚህ ወቅት ደግሞ፣ ለወራት እየተጠራቀሙ በመጡት መራራቆች ምክንያት አዲስ ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፡፡ በዚህ ጥያቄ ላይ "የተግል በለተ ለውጥ ለምን?" በሚለው የዚህ ጽሑፍ አምስተኛ ክፍል ውስጥ እንመለስበታለን፡፡ አሁን ለማመልከት የምንፈልገው ሶስት ፋሬ ነገሮችን ብቻ ነው፡፡

<u>አንደኛ</u>፣ ቀደም ሲል እንዳልነው "ህብረቱ" ዕውነተኛ ህብረት ሊሆን የሚችለው፣ ወይ ተባባሪያቹ ድርጅቶች ተመጣጣኝ የሆነ የፖለቲካ ሥፍራና ማቴሪያላዊ ኃይል ሲኖራቸው፣ ያለዚያም በተለይ አብዮታዊ ሰደድ /=ደርግ/ ፍፁም ዲሞክራሲያዊ ሲሆን ብቻ ነበር፡፡ እንደሚታወቀው፣ የመጀመሪያው ያልነበረውን ያህል፣ አብዮታዊ ሰደድም /=ደርግ/ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ለማወቅ፣ ለመጠበቅና ለማክበር ዝግጁ አልሆነም፡፡ ይባሱኑ ከህብረቱ አባል ድርጅቶች መካከል ማሌሪድና ወዝ ሊግ አቋማቸውን በ180 ዲግሪ ለወጡት፣ በየካቲት 69 የጋራ መግለጫ ላይ በምልነት የተደረሰበት የዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄም ተፋቀ፡፡

<u>ሁለተኛ</u>፣ ከሐምሌ በፊት ለስድስት ወሮች የተካሄዱት ፀረ ሕብረት ሥራዎች፣ መርህዊ ህብረት እንደማይኖር የሚያረጋግጡ ነበሩ፡፡ ይህ ደግሞ፣ በወረቀት ላይ በሰፈረ የመተዳደሪያ ደንብ ብቻ መስመርና ሥርዓት ሊኖረው እንደማይችል ግልፅ ሆኖ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት መኢሶን ሰሕድ 60ን አውጥቶ ብዙ ቢጽፍም፣ ምክንያቶች ነበሩት፡፡

<u>ሶስተኛ</u>፣ በስድስቱ ወሮች ውስጥ በተፈጠሩት አሰላለፎች እንደታየው፣ <u>የ3 ለ2</u> አሰላለፍ እንደዚሁ ለረጅም ጊዜ የማይለቀቅ መሆኑም የዚያኑ ያህል ግልፅ ሆኖ ነበር፡፡ በደንቡም መሠረት ቢሆን፣ የአንድ አባል ድርጅት ዲሞክራሲያዊና ነፃ ሀሳብና የማይጠበቁና የማያከብሩ እንደሚሆን ቀደም ሲል የተከናወኑት አያሌ ድርጊቶች ሁሉ ግልፅ አድርገውት ነበር፡፡

እነዚህ በወቅቱ መኢሶን በተከበለ የተረዳቸው መሠረታዊ ጉዳዮች የቀን ያህል ተከከለና ግምገማዎች እንደሆኑ ለመረዳት እርቀ መሄድ አያስፈልገንም፡፡ እነሆ ዛሬ በገቢር ተረጋግጠው እናያቸዋለን፡፡ የሊጥለቱ ከህብረቱ መታገድ ጉልህ የሆነው የታሪክ ምስክር ነው፡፡ ስለዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥያቄ ሰፊው ሕዝብ ብዙ ብዙ ለመናገር ይችላል፡፡

ስለዚህም ነው፣ መኢሶን በሐምሌ 69 እንዳለው ዛሬም ቢሆን ለሃቀኛ አብዮታዊያን ሁሉ እንደሚከተለው የሚለው፡- "ደንቡን በሚገባ እንዲያጠኑትና በተከበለ አሥራ ላይ መዋል አለመዋሉን እንዲከታተሉት" /ሰሕድ 60/

ከዚህ የተለየ ጥሪ የለንም፡፡ የዲሞክራሲያዊ ተግላቻን ጥሪ፣ <u>አንዳም</u> ይህንን መሠረታዊ ጉዳይ የሚመለከት ነው፡፡ የድርጅቶች ዲሞክራሲያዊና ነፃ ሀሳብና እስከሊተጠበቁ ድረስ፣ ስለዚህም በፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ ዲሞክራሲያዊ፣ ነፃና ሃቀኛ ውይይቶችን ለማድረግ እስካልተቻለ ድረስ፣ የህብረቱ ድርጅት ጥንካሬና ጥራት <u>ቢያገስ</u> አከራካሪ ሆነው ይቀያሉ፡፡ ውህደትና የወዝአደሩም ፓርቲ ጥያቄ የቀሉ ቀሉ የአቋራጭ መንገዶችን መሥመር ይይዛሉ... ወዘተ፡፡ ብቻ ይህንውን ታሪክ ደግሞ፣ ለሚቀጥሉት ጽሑፎቻችን ማቀየት ባይኖርብን አይቀርም፡፡

## 5. የመጀመሪያ ማጠቃለያ

የተራማጆች ህብረት መመሥረት አንድ አብዮታዊ እርምጃ ወደፊት እንደነበር፣ አንድም ሃቀኛ ተራማጅ፣ አንድም የአብዮቱ ወገን የሆነ ሰው የማይክደው ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን ለስድስት ወሮች ሙሉ የተራማጆችን ህብረት ሰንከለው የያዙት ጉዳዮች ደግሞ፣ በአያሌ አሉባልታዎችና የፈጠራ ክሶች የተፈጠረ አለመተማመንና አጉል ጥርጣሬዎች እንደነበሩም የዚያኑ ያህል

.../19



ዕውነት ነው፡፡ ሆኖም፣ ከሁሉም በላይ እንቅፋቶች የሆኑት ደግሞ፣ ባንድ ወገን እነዚህ ጉዳ ነገሮች በአንዳንድ የህብረቱ አባል ድርጅቶችና ግለሰቦች ጭምር <u>መወሰዳቸው ነው፡፡</u> በሌላው ወገን፣ ዲሞክራሲያዊና ሃቀኛ ውይይቶች <u>መስፋፋታቸውና እንደ ዕውነት ነው፡፡</u> እንደዚሁም፣ የፖለቲካ አቋሞች ባጭር ጊዜ ውስጥ ለመካሄድ ባለመቻላቸው ሌላው ተጨማሪ ምክንያት ሆኗል፡፡ በመጨረሻም፣ ዛሬ በገሃድ ለንናገረው የማንችለው በበሄራዊ ፖለቲካችን ውስጥ የገባ ወሳኝ ምክንያት አለ፡፡ ለርሱ ጊዜው ይመጣል፡፡ ይሁንና፣ ዞር ዞር <u>ገን፣ መሠረታዊውና ዋናው ምክንያት ዲሞክራሲያዊ መብቶች በተለይ በአብዮታዊ ሰደድ /="ደርግ"/ አለመታወቃቸው ነው፡፡</u>

በክፍል አራት ውስጥ የመኢሶንን ሰነድ በሰፊው እየጠቀስን እንዳሳየነው፣ መኢሶን "<u>ዲሞክራሲያዊና ሃቀኛ ውይይት</u>" ሽኩቻን፣ አሉባልታንና የስም ማጥፋት ዘመቻን እንዲተው "ያልወተወተበት አንድም ጊዜ አልነበረም፡፡ እንደዚሁም፣ "የመኢሶን እምነትና ምኞት፣ <u>ሃቀኛ የተራማጆች ህብረት እንዲመሠረት</u>፣ ከዚያም ዕውነተኛ የወዝአደሩ ፓርቲ እንዲፈጠርና ህዝባዊ አብዮታዊ ግንባር እንዲቋቋም መሆኑን" ያላሳወቀበት አንድም ጊዜ አልነበረም፡፡

ይሁንና፣ የመኢሶን ስድስት ወሮች ሙሉ "ማልሰና መገዘት" የተፈጠረትን ጥርጣሬያች ሊያስወግዱ አልቻለም፡፡ አለመተማመንን በመተማመን ሊተካ አልቻለም፡፡ በተቃራኒ፣ ፀረ መኢሶን ዘመቻን በሚከለከተው በኩል፣ አሉባልታዎችና የፈጠራ ክሶች በስድስቱ ወሮች ውስጥ፡- "መኢሶን የነፍጠኞችና የተምክህተኞች ድርጅት ነው፤ መኢሶን የጠባብ በሄረተኛ ድርጅት ነው፤ መኢሶን የኤርትራን መገንጠል ይደግፋል፤ መኢሶን የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤትንና የፖለቲካ ት/ቤትን በሞኖፖል ይዟል፤ መኢሶን የቢሮክራት ማርክሲስቶች ድርጅት ነው፤ መኢሶን የጠባብ ቡድን ድርጅት ነው፤ መኢሶን ስልጣን የጠማው ድርጅት ነው፤ መኢሶን አጉል ሊሕስ ነው፤ መኢሶን ህብረቱን አይፈልግም፤ መኢሶን፣ መኢሶን..." ከሚሉት አልፈው፣ በሰኔና በሐምሌ ወሮች ውስጥ፡- "መኢሶን ተ/ቤቶችን ለማስቆም አድማ እየቀሰቀሰ ነው፤ መኢሶን በፋብሪካዎች ውስጥ የሥራ አድማ ሊጠራ ነው፤ መኢሶን በሊቀ መንበሩና በደርግ ላይ ሰላማዊ ሰልፍ ሊያስ ደርግ ነው፤ መኢሶን ዘመቻውን አይደግፍም፤ መኢሶን ከውጭ የምናገኘውን ድጋፍ ይቃወማል፤ መኢሶን፣ መኢሶን..." ወደሚሉ ተሻገረ፡፡

መንግሥቱም በደረሱት "እረዳቶች" መሠረት አንዳንድ እርምጃዎች መውሰድ ጀመረ፡፡ ሰላዮችን አሠማራ፡፡ ዜና ደብዳቤያችን በተነ፡፡ እንቅስቃሴያችን መቆጣጠር ጀመረ፡፡ አንዳንድ አባሎች ከህዝብ ድርጅት ጽ/ቤት ታገዱ፡፡ አንዳንድ ካድሬዎችም ይታሠሩ ጀመር፡፡ አንዳንድ ቹ ተረሸኑ፡፡ በመኢሶን ላይ የሚደረገው ቀስቀሳ፣ ከነጭራሹ "የፀደይ መጽሔት፣ የጋዜጦችና የቴሌቪዥን ቲያትር መድረኮችን እስከመያዝ በቃ፡፡ እያለም፣ ወደ ሲሚናር አዳራሾች ዘለቀ፡፡ በአደባባዮች ተስተጋባ፡፡ "ታጠቅ" ጦር ሠፈር ገባ፡፡ መኢሶን "የመታው" ብቻ ባይሆን፣ <u>እየተመታ ያለው</u> ድርጅት ሆነ፡፡

ሆኖም፡ የኢማሌድህ ጽሑፍ እነዚህን ሁሉንጉዳዮች፡-

> "መኢሶን በአሉባልታ ያምናል፡፡ በአሉባልታ ይደናገጣል፡፡ ስሟን አጠፉን፣ አጥላሉን፣ ሊያስመቱን ነው"በማለት ሮሮውን ያሰማልእንጂ፣ ችግሮችን አብዮታዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት ሙከራ አላደረገም" /26/

በማለት ያልፋቸዋል፡፡ እኛም እንግዲህ አንባቢ ያገናዝብ ብለን ከመጠየቅ በስተቀር ሌላ አማራጭ አይኖረንም፡፡

<u>አንደኛ</u>፣ መኢሶን "ችግሮችን አብዮታዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት" የወሰዳቸው አቋሞችና ያቀረባቸው ጥያቄዎች ሁሉ፣ በሰሕድ ቁጥሮች ውስጥ በገሃድ ተጽፈው ይገኛሉ፡፡ እንደዚሁም፣ የአብዮት ፋናን፣ የአዲስ ፋናንና የታጋይ ኢትዮጵያዊትን እትሞች መመልከት ይቻላል፡፡ በዚህም ጽሑፍ ውስጥ አለፈን አለፈን እየጠቀስን ለማመልከት ሞክረናል፡፡ በተጨማሪ የዚህን ጽሑፍ ክፍል ስድስት ለማገናዘብ ይቻላል፡፡

<u>ሁለተኛ</u>፣ ሌሎች ድርጅቶች "ችግሮችን አብዮታዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት" በዚያ ወቅት ውስጥ የወሰዱትን ወይንም ያልወሰዱትን አቋም ከሰነዳቸው ላይ አንብቦ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ እንደ ወዝ ሊግ ማድረጥም አቋም እንደሆነ ማመልከት ተርፍ ይመስለናል፡፡

<u>ሶስተኛ</u>፣ በጊዜው በመኢሶን ላይ የተወሰዱት የጭቆና እርምጃዎች የታወቁ ናቸው፡፡

<u>በመጨረሻም</u>፣ በአሉባልታዎችና በፈጠራ ክሶች ላይ፣ በዚያን ጊዜም ሆነ አሁን ያለው ግልፅ አቋም፣ የድርጅቱን ሰነድ በማንበብ ለመረዳት የሚቻል ነገር ነው፡፡ እንደሚከተለው ነው፡-

> <u>ሰሕድ 59 – ሐምሌ 4/69</u>
> "ዛሬ አገራችን በበገነት ችግሮች ተውጣ እያየናት፣ እዚህ ላይ /አሉባልታዎችን/ ማንሳታችን ለነሱ ዋጋ ለመስጠት አይደለም፡፡ አሉባልታ፣ ሃሜት በተገለፀ አቋም ላይ ሳይሆን፣ ባልተባለ፣ ባልተፃፈና ባልተነገረ ጉዳይ ላይ አንዱን ገቦናቴ መተቸት የሚያሳየው ምንድነው? ቢያንስ ሁለት ችግሮችን ያሳያል፡፡ <u>አንደኛ</u>፣ አድሃሪዎችና አድርባዮች በአንድ ገቦናቴ ላይ አሉባልታ ቢያስዙ፣ ያ ገቦናቴ በያዘው አብዮታዊ አቋም የተነሳ፣ ለጠላቶች ከአሉባልታና ከፊውዳል ሃሜት ሌላ መፍናፈኛ ነስቷቸዋል ማለት ነው፡፡ <u>ሁለተኛ፣ደግሞ</u>፣ ሊነገ እንዳለው በአሉባልታ መጠቀም የፖለቲካ ክስረት አስተማማኝ ምልክት ነው፡፡

.../20

"ነገር ግን ይህንን ስላልን፣ አሉባልታዎች አደጋ የላቸውም ማለት አይደለም:: ዝም በለው ከተጠራቀሙ አድሃሪዎችና አድርባዮች የአብዮቱን ሰፈር ለመከፋፈል፣ ለማጋጨትና ለማዳከም ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ:: እንዲያውም ዛሬ አገራችን በበዙ ችግሮች ተወጥራ፣ በነዚህ ጉዳዮች ለመሟገቻ መነሳታችን፣ ዛሬም በመኢሶን ላይ የተጠራቀሙት አሉባልታዎች ከመግነናቸው የተነሳ፣ ተራማጆችን ሊያጋጩና የአብዮቱን ሠፈር ሊከፋፍሉ የሚችሉበት አደገኛ ደረጃ ላይ ደርሰዋል ብለን በማመናችን ነው:: ስለሆነም፣ የዚህ ጽሑፋችን ዓላማ፣ በአድሃሪዎች የመከፋፈል ሤራ በተራማጆችና በሰፊው ሕዝብ ሰፈር የተነሳው አደገኛ ውዥንብር እንዲጠራና የአብዮቱ ሠፈር በዚያው ለከ ጥራቱና ጥንካሬ አገኝቶ ትግሉን ለማድረግ ነው::"

ውጅ፣ በአሉባልታና በፈጠራ ክሶች ላይ ከዚህ የበለጠ ገለጻ ለመሆን አስቸጋሪ ነው:: ደግሞ መፍትሄያቸው ዛሬም ቢሆን ዴሞክራሲና ሃቀኛ ውይይት ብቻ ነው::

ስለዚህም ነው፣ መኢሶን ዛሬም ቢሆን ዴሞክራሲያዊና ሃቀኛ ውይይቶችን ያለማቋረጥ የሚጠይቀውና ለዚሁ የሚታገለው:: ጥራትና ጥንካሬ ያለው ሃቀኛ፣ ታጋይ፣ አብዮታዊና ዴሞክራሲያዊ የሆነ የተራማጆች ህብረት ለመሠረትና እንደብረት ጠንክሮ ሊገነባ የሚችለው:- በዚህ ዓይነት የአንድነትና የትግል መሥመር ብቻ ነው የሚለው:: ጊ.ወ.አ. ደርግና ኢማሌድህ፣ አሁንም ቢሆን ለዚህ ለመኢሶን ተደጋጋሚ ጥያቄ ጆሮአቸውን እንዲሰጡ፣ ለውይይት አመቺ የሆኑ ዴሞክራሲያዊ ሁኔታዎችን እንዲፈጥሩ አጥብቆ የሚጠይቀው::

ይሁንና፣ እዚህ ላይ ደግሞ፣ መኢሶን ውይይትና ሃቀኛ ህብረት ባለ መጠን፣ የመንግሥት ጥቃት በመኢሶን ላይ እየከፋና እየተባባሰ እንደመጣ ሳይገለፅ ለማለፍ አንችልም:: በዚህም፣ መኢሶን ሳይሆን ጊ.ወ.አ. ደርግና ኢማሌድህ በኢትዮጵያ ህዝቦችና በዓለም ተራማጆች ፊት እየተጋለጡበት ናቸው::

## 6. የትግል ስልት ለውጥ ለምን?

የትግል ስልት ለውጥ ለምንና መቼ? የሚሉትን ጥያቄዎች፣ የኢማሌድህ ጽሑፍ ከፊል ዕውነት በመናገር መለሷቸዋል:: ነገር ግን፣ ልብ ብሎ ያነበበው ሰው ደግሞ፣ የኢማሌድህ መልስ በበረዛ የተከሸነና ተጥቆ አስረፂ እንደሆነ ወዲያውኑ ይረዳል:: እርሱኑ እንጠቅሳለን::

> "ማርክሳዊ ሌኒንያዊያን ከሰፊው ሕዝብ ጋር ተዋህደው ለመታገል የጎርጋንጋናና የትስስባ ተግባር በሚገባ ለማካሄድ፣ ያለበትን ታሪካዊ ወቅት፣ የህብረተሰብ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን እንዲሁም ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን በማጥናት፣ በመተንተንና ተከክለና ገምገማ በማድረግ፣ የአብዮቱን ሰፈር አስተራቴጂያዊ ዓላማ እንጉ ለማድረስ የሚያስችሉ ህጋዊና ስውር የትግል ስልቶችን በማቀናበር መታገል አለባቸው::" /22/

የኢማሌድህ መልስ እስከዚህ ነጥብ ድረስ እኛንም የሚያከራክር አይደለም:: መኢሶንም ከግንቦት 67 እስከ ነሐሴ 69 የታገለው 'ህጋዊና ስውር የትግል ስልቶችን በማቀናበር" ነበር:: ይህንንም ያደረገው "የአብዮቱን ሰፈር አስተራቴጂያዊ ዓላማ እንጉ ለማድረስ" ለማገዝ ነበር::

ይሁንና፣ ኢማሌድህ ከዚህ ተጥሎ ደግሞ፣

> 'አብዮታዊያን ህጋዊ ትግል ለማካሄድ በፍፁም የማይችሉበት ደረጃ ከደረሱ ግን፣ ያላቸው ብቸኛ አማራጭ መንገድ በስውር የሚደረገውን ትግል ማስፋፋትና ማጠናከር ነው:: ከትግል ስልታቸው አንዱ ስለሆነ፣ ይህን ማሊያቸ ሁሉ ይደገፉታል::" /22/

ሌሉ ግን የበር ሃገና የዉለማን ያህል እንለያያለን::

አንባቢያች የኢማሌድህ "ማርክሲስት ሌኒኒስት" አባል ድርጅቶች የዘቀጡበትን በራዥነት ልብ ብላችሁ ተመልከቱት::

የመጀመሪያው እኛ 'ህጋዊና ስውር የትግል ስልቶችን ለማቀነባበር መታገል" ነበር:: ነገር ግን እነፍ ባይሉ ደግሞ፣ "በስውር የሚደረገውን ትግል ማስፋፋትና ማጠናከር" የሚገባው 'ህጋዊ ትግል በፍፁም ለማካሄድ ካልተቻለ ነው" ይላሉ:: ደግሞ፣ ይህንም፣ ማሊያዊ እኛ በለውት፣ 'ይህን ማሊያቸ ይደገፉታል" ይላሉ::

ይህ ምን ማለት ነው? ይህ ባጭሩ፣

አንደኛ፣ "አስተራቴጂያዊ ዓላማ" በህጋዊ ትግል እንጉ ይደርሳል:: ምክኒያቱም በኢትዮጵያችን ላይ ፍፁም ዴሞክራሲ ሰፍኗል ማለት ነው:: መንግሥት ከመደቦች ትግል ውጭ ነው ማለት ነው::

ሁለተኛ፣ 'ህጋዊ ትግሉን" በፍፁም ለማካሄድ እስካልተቻለ ድረስ፣ የህቡዕ ትግሉን ለማስፋፋትና ለማጠናከር የሚታገሉትን ተራማጅ የፖለቲካ ድርጅቶች እናወግዛለን ማለት ነው:: ብቻ እዚህም ላይ፣ የኢማሌድህ ጽሑፍ ደራሲያች ይህች "በፍፁም" መቼ 'ፍፁም" እንደም ተሆነ ቢገለፁልን በተገባ ነበር::

.../21



ሶስተኛና በመጨረሻም፣ ጭቁኑ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ፣ ህዝባዊ መንግሥትን ከምርጫ ባገኘን በሚመነጭ ኃይል ላይ መሥርቶ፣ የፖለቲካ ስልጣንን ሊጨብጥ ይችላል ማለት ነው:: ከዚህም ከተነሳን፣ "ለነፃ፣ ለተደራጀና ለታጠቀ ሕዝባዊ አመጽ" ጥሪ የሚያደርጉትንና ለዚህ እውን የሚታገሉትን ተራማጆች ከፍሎች እንደ "ቀኝ መንገደኛ"፣ "ደብደና"፣ "በራዥ"... ወዘተ ከሚታዩበት አስተያየት ላይ እንደርሳለን:: ነገ ጥያቄ፣ "ከህጋዊ ትግልና"... ዓይነት "የወዝአደሩ ፓርቲ" ከተመሠረተልን በኋላም፣ "ኢትዮጵያ ተአምር አሳየች"፣ በህነው "ማርክሲስም ሌኒኒዝም ቢያገስ በዚህ በፖለቲካ ስልጣን ጥያቄ ላይ መታረም አለበት" ነው:: "ነገሩ በገብፀ፣ በቺሊ፣ በሱማሊያ፣ በሱዳን፣ በአንጎላ... ባይሠራም፣ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ለምሰሶ፣ ፈገዱቶ፣ አበበ ታየ" ለገበሰ ነው::

እንግዲህ የኢትዮጵያ ሕዝቦችና ሃቀኛ ተራማጆች ምን ተፈለጋላቸሁ?!! የኢትዮጵያ ሰማያት ቀለተቀለ!!! ምድሪም ገነት ሆኗል!!! ሌላው ቀርቶ የኢትዮጵያ ደሮቻችና ለአቀፋት እንኳ በሽሊስት የሆኑትን ቀያይ እንቁላሎች እየጣሉ ናቸው!!! ...ወዘተ:: እሳስ ፣ "ያለምንም ደም፣ ኢትዮጵያ ተቀደም" ::

ለማንናውም፣ በነሐሴ 1969 መኢሶን የትግል ስልት ለውጥ እንዳደረገ የታወቀ ነው:: መኢሶንም፣ የትግል ስልት ለውጥ ያደረገው በነሲብ ሳይሆን፣ "ታሪካዊውን ወቅት፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ጉዳዮችንና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን አጥንቶ፣ ተንትኖና ገምግሞ፣ የአብዮቱን ሰፈር አስተራቴጂያዊ ዓላማ ከግቡ ለማድረስ" በማለት ነው:: ይሁንና፣ እዚሁ ላይ ስንደርስ ደግሞ፣ "ሁኔታዎችን በተከከለ አጥንቷል፣ ተንትኗል፣ ገምግሟል" ወይ? የሚለው ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም:: አንዳንዶችም "አማራጭ መንገድ" አልነበረም ወይ? እያሉ ራሳቸውን ይጠይቁ ይሆናል:: ኢማሌድህ ደግሞ፣ 'ህጋዊ ትግልን ለማካሄድ በፍፁም ከማይቻለበት ደረጃ" "ፍፁም" መቼ ደረሰብን ይላሉ::

ኢማሌድህ ለነዚህ ጥያቄዎች የሚሰጠው መልስ ፍፁም አጭር ነው:: እርሱን በመጥቀስ እንደምር:-

> 'መኢሶን ዘባዝንኩውን፣ ዘንንተሉን፣ እንደምክኒያት ከደረደረ በኋላ ፈረጠጠ" /26/

የሚል ነው:: የኢማሌድህ መልስ እቺው ብቻ ናት:: እናም እንግዲህ እኛም 'ዘባዝንኩውንና ዘንንተሉን እንደመደርደር" አይቀጠርብንና፣ የአንባቢያችን ትዕግሥት ጠይቀን እነርሱን ወደ መደርደር እናምራ:: ወደ ነበሩት ሁኔታዎች ተመልሰን በዕውነት ስለዕውነት እናስተውል::

— መኢሶን የትግል ስልት ለውጥ ያደረገው:-

አንደኛና ከሁሉም በፊት፣ ባለው አጀንዳ ቸሉታው ሁሉ "ለዘለቄው ትግል" /የሰሕዴ 61 ርዕስ/ አመቺ የሆኑ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ነው:: ስለዚህም ጉዳይ ፣ የትግል ስልት ለውጥ ማድረጉን ባስታወቀበት የሰሳኑ እትም ቁ.61 ውስጥ እንደሚከተለው ተናገረ::

> 'መኢሶን የትግል ስልት ለውጥ ያደረገው አብዮቱን ተከከለኛውን ፈር ለማስያዝ፣ ያገሪቱን በሄራዊ ነፃነት ለማስከበርና ምገም ተፅእና በማይኖረው መንገድ የቡድኑን አስተዋፅኦ ለማድረግ ነው::"

ሁለተኛ፣ "ለጊ.ወ.አ. ደርግና ለተራማጆች ህብረት በየወቅቱ ያቀረባቸውን ሃሳቦች በቀን መገፈሱና ከአብዮቱ አገፀር በመመለከት ፈንታ፣ ሃሳቦቹ ከመኢሶን በመመንጨታቸው ብቻ ደርግና አንዳንድ ድርጅቶች በጥርጣሬ ዓይን እያዩአቸው ከሥራ ላይ ባይውሉ በመቅረታቸው ነው:: ስለዚህም፣ ለአብዮቱ የሚፈለገውንና የሚጠበቀውን ያህል አስተዋፅኦ ለማድረግ ባለመቻሉ ነው::" /ሰሕዴ 61/. ነሐሴ 1969/ በዚህም አገፀር በየከፍሉ የሚከተሉት ሃሳቦችና ጥያቄዎች ቀርበው ነበር::

ሀ/ ዘመቻውንና አብዮታዊ አመራርን በሚመለከተው በኩል

1. የሃረርጌ፣ ባሌ ሲዳሞ አርሲ አደሮች ባስቸኳይ እንዲታጠቁ፣
2. ከህብረት አባል ድርጅቶች የተውጣጡ ካድሬዎች ባስቸኳይ ወደነዚህ ሥፍራዎች በብዛት እንዲላኩ፣
3. በታጠቀ ጦር ሰፈር ውስጥ የህብረት አባል ድርጅቶች ካድሬዎች እንዲመደቡ፣
4. በርዕዮተ ዓለም አስተባባሪ፣ በአሠራር ዘዴና በአብዮታዊ ዲሲፕሊን የተሳሰረ የፖለቲካ አንቂዎች ከሠራዊት ጋር እንዲዋሃዱና ከተራው ተዋጊ ጋር በጥብቅ እንዲተሳሰሩ፣
5. የተራማጆች ህብረትን ለማጠናከር ጥረት እንዲደረግ፣
6. የጠላትን ሠፈር ቅራኔዎች በብልህነትና በአስተዋይነት እንዲገጠሙ፣
7. የታወቁ አድሃሪዎችን በቁጥጥር ስር ለማዋል፣
8. ዴሞክራሲያዊ መብቶች በሥራ ላይ እንዲውሉ፣
9. የህዝባዊ ድርጅቶች መንፃት፣ መደራጀትና መታጠቅ ተጠናክሮ እንዲፋፋም፣
10. የታሠሩት ተራማጆችና አገር ወዳዶች እንዲፈቱ፣
11. የብሄረሰቦችን መብት ደረጃ በደረጃ ከሥራ ላይ ማዋል፣
12. በመሃል አገር አብዮቱን ማፋፋም::

.../22

ነገር ገን፣ የኢማሌድህ ጸሑፍ እነዚህን ሁሉ ጉዳዮች "ዝብዝንኪና ዝገገተል" ብሎ በመተቸት ምክንያቱም ለእያንዳንዱ ነጥብ መልስ ለመስጠት አይ ያሩፋቸዋል:: ምክንያቱም ገለጸ ነው:: ለማቅረብ የሚፈለገው፣ ይልቁኑ "ፈርቀ እንደፈረጠመ"፣ ቶለምና::

ስለዚህም፣ ኢማሌድህ መኢሶንን "ማርክሲዝም" ሲቸገረው፣ ወደፊውዳል ስብስብ ይዞርና፣ "ፈርቀ እንደሸሸ" ድርጅት ነው:: ብርቅ ይላል:: "ፈረጠመ"፣ "ሸሸ"... ነገሮችን ሁሉ "የወገድነት" ጥያቄ አድርጊቸው ቆጥ ይላል:: ከዚህ በታች የምንጠቅሰውን ቃል ነበር:: ወዘተ. ይላል:: ከና ሲለዎ ከዚህ በታች ያሉት አብዮቱና ድርጅት፣ ታጋይ ድርጅት እኔ ብቻ

"መኢሶን ራሱን ካሰወደደና ያለሁት አብዮቱና ድርጅት እኔ ብቻ ሊፈፀሙትና ሊቀርጡት የሚችሉበት ነን" ካላለ በስተቀር፣ እሱን ብቻ አድሃሪያን ሊፈሪጡትና ሊቀርጡት የሚችሉበት ምክንያት የለም:: ዐርገጥ፣ የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ገዚያዊ ጸ/ቤት ሰፊውን ሕዝብ በማስተማር፣ በማገያትና በማደራጀት በኩል ከፍተኛ ሚና መጫወቱን የተረዱ አዉሃሪ ያን /ከደርግ አካባቢ ጭምር — ቀገና የሀይ/ ሊያፈርሱትና ካድሬዎችን ለማሳደድ ከፍተኛ ዘመቻ ያደርጉ ነበር:: ሕዝብን በማገያት፣ በማደራጀት ተገባር የተሰማሩት አባላቶች ብቻ አልነበሩም" /26/

ለአብዮቱ የሞቱት የመኢሶን ደጋፊዎችና አባሎች ብቻ ናቸው" ብሎም ይህ የኢማሌድህ ጸሑፍ ውስጥ የጠቀሰነው አነጋገር እንደሚታየው በዐውነቱ ሰበን የሚበለ ነው:: ይሁንና ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር ሲገናዘብ ደግሞ፣ በሚትን ለመማፀን የተጫረ እንጂ፣ ሌላ ትርጉም የለውም:: ከመጀመሪያው መኢሶን "ያለሁት አብዮቱና ድርጅት፣ ታጋይ ድርጅት እኔ ብቻ ነን" አይለም:: በሎም አያውቅም:: ይህ አንቲያው በባደ ሚላ ነገር ግሳመርና አንገብ ጋቢ ጥያቄዎችን ለመሸወዉ መገሸዋረር ነው::

ሁለተኛ፣ መኢሶን "ለአብዮቱ የሞቱት የመኢሶን አባሎችና ደጋፊዎች ብቻ ናቸው" ብሎም አያውቅም:: መኢሶን የሚያምነው፣ ለብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የሞቱት ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ናቸው ብሎ ነው:: ነገር ገን ኢማሌድህም "ለአብዮቱ ከሞ ደገሞ፣ እንደዚህ ባሉት ርካሽና የቦዘኔ ከርከሮች ዘዴዎች መሳቀቅ አለበት::

በበተኛ፣ በለዚህም፣ እነዚህም ላይ ቢሆን ዕውነቱን መናገር ያስፈልጋል:: በወቅቱ በነበረው ሁኔታ በህጋዊ መስክ ላይ ይገኙ የነበሩት አብዛኛዎቹ ጓዶች የመኢሶን አባሎችና ደጋፊዎች ነበሩ:: አብዛኛዎቹ በቀጥር ነፍሰ ገዳዮች እየተረሸኑ የወደቁት ጓዶችም የመኢሶን አባሎችና ደጋፊዎች ነበሩ:: ይህንን እውነት፣ የህዝብ ድርጅት ጸ/ቤት፣ የፖለቲካ ት/ቤት፣ የቀበሌ ማህበራት፣ የወዝአደር ቤቶች... ወዘተ. እስታቲስቲክስ በቀላሉ ያረጋግጡታል:: ኢማሌድህ፣ ይህንን ዕውነት ለመናገር የሚፈራበት ወይንም የሚያፍርበት ምክንያት ሊኖረው ባለ ተገባ ነበር::

አራተኛና በመጨረሻም፣ "እርገጥ... አድሃሪያን ጸ/ቤቱን ሊያፈርሱትና ካድሬዎችን ለማሳደድ ዘመቻ ያደርጉ ነበር" ካለ አይቀር፣ በጸ/ቤቱ ስም የሚደረገው ዘመቻ በተለይ በመኢሶን ላይ እንደነበር መገለፅ ነበረበት:: ይህ ጉዳይ ከእነዓለማየሁ — ሞገስ ዘመን ጀምሮ የታወቀ መሆኑን ማሳወቅ ነበረበት:: ከነርሱስ በኋላ ለምን ቀጠለ?

"እርገጥ" እንበል፣ እና ደገሞ፣ "እርገጥ" ይህንን ማለት፣ "አድሃሪያን ሊፈልጡና ሊቀርጡ" የተነሱት መኢሶንን ብቻ ነው ማለት አይደለም:: በአገባሩ፣ አድሃሪያን በኢትዮጵያዊያን ሃቀኛ ተራማጆች፣ አገር ወዳዶች፣ ዲሞክራቶች፣ የሕዝብ ተመራጮች... ወዘተ. ላይ የሚያጡት ሣራ ሁሉ ደገሞ፣ የመኢሶን ጉዳይ ብቻ ነው ማለትም አይደለም:: የአብዮታችንና የአብዮታዊ ኃይሎች ሁሉ ጥያቄ ነው::

ይልቁኑ፣ እንደዚያ ባለው ሰዓት ሃቀኛ ተራማጆችና አብዮታዊያን በጋራ ምን ዓይነት አቋም ይወስዱ ነበሩ?

በዚያ ሰዓትስ፣ ለምን ከገዳች ዓይነት የጋራ አቋም ላይ ለመድረስ ሳይቻሉ ቀሩ?

የኢማሌድህ ጸሑፍ መመለስ የነበረበት እነዚህን ጥያቄዎች ነበር:: እና በዚህ ጽሑፉቹን ውስጥ በሙሉ በመሠረቱ የመለሰነው እነዚህን ጥያቄዎች ነው::

የኢማሌድህ ፃሑፍ ደራሲዎች እነዚህ ላይ እንደገና ጣሪያዎችን ካማተሩ በኋላ፣

"እክ! ተራማጆች ታገለው ደርገን እንደገና ከአብዮት ሠፈር እቅመውታል" ቢሉን፣ ወገዶች! የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትንና ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን በጥገቀላታቸው ተቀብለዋል በለን እንመለስላቸዋለን:: የኢትዮጵያዉችን ሁኔታ ይናገር::

የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮታችን ፕሮገራም ለዘለዐለም ይኑር!

ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ለዘለዓለም ይኑር!

እንገዲህ ወደ መጨረሻው ጥያቄ እንመለስ::

እና እንደተረዳነው፣ በመኢሶን ላይ የሚቀርበው "ሂስ" እስከዚህም መኢሶን የትገል ስልት ለውጥ በማድረጉ ምክንያት ሊሆን አለቻለም:: ይልቁኑ "በዚያ ሰዓት" የትገል ስልት ለውጥ በማድረጉ ነው:: እስቲ ይህንን ደገሞ እንመልከተው::

እርገጥ፣ ይህ ጥያቄ ከዘጠኝ ወሮች በኋላ ሲቀርብ አደናጋሪ ሊሆን አይቻልም:: በሌላ በኩል ደገሞ፣ በሚትን ለመቀስቀስ፣ ለጓማገዥ... ወዘተ. አመቺም ነው:: ይሄው በየአደበበዩ እንደሚሰማው፣ እንደናው መኢሶንን ከገዥ ኃይለ ሥላሴ ጋር ለማነፃፀር ይሞከራል:: ሌላው፣





የመደብ መገሸራተት ነው ይላል:: ሌሎችም እንደ "ክህደት" ሊቀጥሩት ይቃጣቸዋል:: ሁሉም ስሚትን ለመቀስቀስ፣ ጓማገዥን ለመገዛት የታቀዱ ናቸው::

ይሁንና፣ በነዚህ ምክንያቶች ደገሞ፣ በዚያ ሰዐት የነበሩት ነባራዊ ነገሮችና ሁኔታዎች፣ ከምድረ ኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ሕዝቦች የትገል ታሪክ ውስጥ በቀላሉ የሚፋቁ አይሆኑም:: ስለዚህም፣ በዚያን ጊዜ በነበሩት ሁኔታዎች ምክንያት ዛሬ ያሉትን ገና ለረጅም ጊዜ እንደ ነቀርሳ ተተክለዉ የሚቀየዩ ሁኔታዎች ከምድረ ኢትዮጵያ አይጠፉም:: ዕውነትና ማርክሲስቶች፣ "አብዮትና ፀረ አብዮት በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ ሥር ለሚፅፉት ድርሰት፣ ከዕንቁ የሚከብሩን መረጃዎች እየሰበሰቡ ናቸው:: የናም ገለፃ ተገቢት አይደለም:: የምንናገረው ስላሉ ነገሮች ነዉ::

ለማንኛውም፣ ማርክሳዊ ታሪክ ነገሮችን የሚመረምራቸውና የሚገመግማቸው፣ ነገሮቹ በተከና ወኑበት ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ... አድርጉ ነው:: ከሰሚትና ከቂም አርቆ ነው:: የኢማሌዐህ ጸሁፍ ራሱ ካገድ በታ ላይ እንዳለው:-

"የነገሮችንና የክስተቶችን አስተሳደግ በማጤንና ሁኔታዎችን በተጨባጭ በመገምገም፣ አዝማሚያዎችን በመገንዘብ፣ ቀራኒዎችን በየደረጃቸው በመመደብ" /31/ ነው::

በእውነቱ፣ ኢማሌደህም በመኢሶን የትገል ስልት ለውጥ ጥያቄም ላይ ማርክሳዊ ለመሆን ጨምከር በተሻለ ነበር:: ከዚህም አልፍ በፍፁም እውነት ያልሆኑ ነገሮችን እስከመጻፍና እስከ መናገር ደርሷል:: ለምሳሌ፣ "ለሰፊው ሕዝብ ሽቀጣ ሽቀጥ ያመጡ ይመስል ወደ አውሮፓ ተበ ደሩ" /23 — 24/ ሲል፣ አነጋገን ማለቱ እንደሆነ ገራ የሚያጋባ ነው:: ለሰፊው ሕዝብ "ሽቀጣ ሽቀጥ" እንደቸገረው ለመናገር ፈልጉ እንደሆነ፣ ሌላ መድረክ ጨምርጥ በተሻለ ነበር::

ለማንኛውም እውነቱ እንደሚከተለው ነው:: በመኢሶን በኩል በድርጅቱ የውጭ ሥራ ተመድቦ ወደውጭ የተላከው አንድ ሰው ብቻ ነው:: ይህም ደገሞ፣ ኢማሌዐህ ጨወደውም ጨጠላውም የድር ርጅቱ መብት ነው:: ሌሎች የመኢሶን አባሎች፣ ደጋፊዎችና ወዳጆች ገን ፓሪሠውም ይሁን ተገ ዐለው አዚህ በኢትዮጵያ ምድር የሚገኙ ናቸው:: ሌሎችም እንደሁኔታውና እንደጊዜው እየታገሉ ናቸው::

በእውነት ኢማሌዐህ እንደዚህ ዓይነቱን ርካሽና የቦዘኔ የከርከር ዘዴዎች መጠቀሙ አይገ የሚያስገርም ነው::

ይልቁኑ፣ የኢማሌዐህ ጸሑፍ ደራሲዎች፣ ደጋገመው የጠቀሱትን በሕዳ 61ን በደገብ ቢያነ ቡት ኑሮ፣ ከእንደዚህ ዓይነቱ አሳፋሪና የሚያስገምት ስህተት ውስጥ ባልወደቁ ነበር:: መኢ ሶን በትገል ስልት ለዉጡ ሌላ ምንም አላደረገም "በህጋዊ የትገል መስክ ያሰማራቸውን አንዳን ዱ አባሎቹን ወደ ህቡዕ የትገል መስክ አዛወረ እንጂ" :: "አዘሰቂው ትገል" ብሎ ቀረጥ አርምጃ ወሰደ እንጂ:: ለአብዮታዊ አመራር፣ ለዲሞክራሲና ለብሄራዊ ነፃነት የሚደረገውን መራራ ትገል ለማገዝ ወሰኝ የሆነን ለውጥ አደረገ እንጂ... ወዘተ::

እንግዲህ እስቲ ኢማሌዐህን እንጠይቀው:-

ለመሆኑ አንድ የፖለቲካ ድርጅት እንደዚህ ዓይነቱን አርምጃ የመውሰድ መብቱ አለው ወይ ንስ የለዉም?

ለመሆኑ አንድ የፖለቲካ ድርጅት፣ ባንድ በኩል ፀረ አብዮት እንደዚያ እያስገመገመ በመ ጣበት ወቅት፣ በሌላው በኩል፣ ህጋዊዉ የትገል መድረክ እንደዚያ እየጠበበ በሄደበት ወቅት፣ እንደዚሁም የተራማጆች ህብረት በአያሌ ፀረ ሕብረት አድራጎቶች ተበገኩሎ በፈመበት ወቅት፣ የዲሞክራሲ መብቶች እንደሚታፈኑ ግልፅ በሆነበት ወቅት፣ በሄራዊ ነፃነታችን ከከፍተኛና አሳሳቢ ከሆነ ሁኔታ ውስጥ በወደቀበት ወቅት፣ የወዝአደሩም ፓርቲ በዚያም በዚህ ለመጠፍጠፍ በሚሞከርበት ወቅት፣ በመጨረሻም፣ አባሎቹ፣ ደጋፊዎቹ፣ ወዳጆችና በጠቀላላዉ የአብዮቱ ወገ ኖች መከላከያ አጥተው እንደቀጠለ በሚረገፉበት ወቅት... ወዘተ፣ እንደዚህ ዓይነቱን አርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለበት ወይንስ የለበትም?

## 7. ከትገል ስልት ለዉጥ በኋላ

ስለዚህ ጉዳይ ሲነሳ፣ የኢማሌዐህ ጸሑፍ የሚጀምረው እንደተለመደው መኢሶንን በመኢሶን ጸሑፍ የገረፈው ለማስመሰል፣ ስህዶን በመጥቀስ ነው:: ስለዚህም፣ "የት ላይ ይሆን?" ይላል፣ የኢማሌዐህ ጸሑፍ ገና ከመጀመሪያው::

"መኢሶን የትገል ስልት ለውጥ ካደረገ ዘጠነና ወሬን ይዟል:: ገን የት ላይ ይሆን፣ መኢሶን 'አብዮቱን ተከኩለናውን ፈር ለማስያዝ፣ ያገሪቱን ብሄራዊ ነፃነት ለማስ ከበርና የሕዝቦቿን አንድነት ለመጠበቅ በሚደረገው ጥረት...' ሃቡኩሉን' ያበረ ከተው?" /22/

በእውነት አስገራሚ ጥያቄ ነው:: ወይ ኢማሌዐህ አብዮታችን ዛሬ ስለያዘዉ "ፈር" ዉርስ አላሰበበትም ወይንም አልተረዳውም:: እንደዚሁም፣ ስለብሄራዊ ነፃነታችን ምንም አልታየውም:: ... ወዘተ.:: በተጨማሪ፣

የኢማሌድህ ጽሑፍ ደራሲዎች፣ መኢሶን ከትግለ
አንደኛ ነገር፣ ቀደም ሲል እንዳልነው፣ የኢማሌድህ ጽሑፍ ደራሲዎች፣ ወይንም አልተረዷቸውም፣
ሸሽቶ ሰዉር በፊቱና በኋላ ያወጣቸውን ጽሑፎች ወይ አላነበቧቸውም፣ ያለዚያም ሊረዷቸው አልፈለጉም::

ሁለተኛ ነገር፣ ሀበረተን በሚመለከተው በኩል፣ በዚህ ጽሑፍ ክፍል ሁለት ውስጥ ያመለከ
ተናቸውን ጉዳዮች ሁሉ ወይ ወርሰው "እያውቋቸውም"፣ ወይንም ደግሞ አያወቋቸውም ቢሆን፣ ተነስተዋል::

ሦስተኛ ነገር፣ ሲያው ቀርቶ "ከዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ" ላይ አንዷ በገሃድ የተደረ
ገ ሆነ በሰው ለመርጋትና ለማስረገጥ የርጠው ትግሎች ወይ ዘንግ ተቀጥቀዋል፣ ወይንም
ጉታን "ወይዘሮቹና" ዛሬም እንደሆኑ የሚደረጉትን "ከወገኑ" ዘገቦውት ነበር::
ጉዳዮን በበፊም "ከወገኑ" ዘገቦውት ነበር:: ጽሑፎች፣ "አበዩቱን ምንም ተፅእና አልቻሉም፣

አራተኛ ነገር፣ ይህንንም ፀሀፍ ወይም የሚቀርቡት ጽሑፎች "አበዩቱን ምንም ተፅእና ለማስያዝ" በማለት እንደሆነ ወይ ሊረዱት አልቻሉም፣
በሰለው መንገድ ትከከለናውን ፈር ለማስያዝ አልፈለጉም::
ወይንም ተረድተውት እንደሁ ሊቀበሉት አልፈለጉም:: እያሉ ኃይቶችና ሃቀኛ ታጋዮች እንደ ተሰው፣

አምስተኛ ነገር፣ በዚሁ ትግል ላይ እንዳሉ፣ እያሉ ኃይቶችና ሃቀኛ ታጋዮች እንደ አንዱ ነገር
ኢማሌድህ ወይ ሬዕም "እያውቀም"፣ ወይንም አበዩትና ፀረ አበዩትን እንደ አንዱ ነገር
አድርጉ ወስደውታል::

ስድስተኛ ነገር፣ በዚህ ትግል ላይ እንዳሉ፣ እያሉ ኃይቶችና ሃቀኛ ታጋዮች እንደ ታሠሩና
እንደታረዱ... ወዘተ.፣ ኢማሌድህ ወይ ሬዕም "እያውቀም"፣ ወይንም አሁንም አበዩትና ፀረ
አበዩት ተቃዋሚዎች አየተገደሉ፣ እየታሠሩ፣ እየታረዱ
ናቸው ... ወዘተ:: ዛሬም እያሉ ኃይቶችና ሃቀኛ ታጋዮች

በመጨረሻም፣ "የት ላይ ይሆን?" የሚለው ጥያቄ፣ አድራሻዎችን የሚጠይቅ እንደሆ፣ በበ
ዐራቸን እንደ ማገጠም ገለፀ ይመስለናል:: ነገር ግን፣ መኢሶን ከትግለ ስለተ ለውጡም
በኋላ፣ አበዩቱን ለማረመድ በሚጠቀሙ አበዩቶቹና ዲሞክራሲያዊ ዐርምጃዎች ውስጥ ሁሉ፣ እንደ
ሁኔታው በእያሉ ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ መንገዶች እንደ ተባተፈ ለንገልፅ እንወዳለን:: ለወደፊቱም
በዚሁ ይቀጥላል:: ሆኖም፣ በዚህ በታ፣ በዚህ ጊዜ፣ በእንደዚህ፣ በእነገሌ፣ በእነገሊት...
ወዘተ. ማለቱ የኛ ጉዳይ አይደለም:: ለዲሞክራሲ፣ ለአበዩታዊ አመራር፣ ለበ
በተረፈ ግን፣ ትግሉ ገና ረጅምና መራራ ነው:: ባጥሩ ለበሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አበዩት መታገል
ሄራዊ ነፃነትና ለኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነት፣ የጊዜና የውንፋታም ነገር አይደለም:: ዲማጎጊና
እንደሚባለው "የአራት ገበዛ አይደለም":: ... ወዘተ:: ተፀንሶና ተረግዞ ከ
የሥልጣን ተምክህተም የአበዩት አዋላጆች አይሆኑም ... ወዘተ:: ተፀንሶና ተረግዞ ከ
"ዝመት ወርቾች" በኋላ የሚወለደው፣ ሰው ብቻ እንደሆነ እናውቃለን::
ሆኖም፣ ባለፈተ ዘመን ወርቾች ውስጥ ከፍተኛ ገለጽና በውር ጥፍና በመኢሶን ላይ ተፈጸመ
ዋል:: እያሉ አባሎቹ፣ ደጋፊዎቹ ወዳጆቹ በገለጽና በስውር ታሠረዋል፣ ተገርፈዋል፣ ታፍነ
ዋል፣ ተረሽነዋል፣ ተሰይፈዋል:: ዛሬም ቢሆን በመኢሶን ላይ ከፍተኛ የከተተለ፣ የእሥራትና
የቀስቃሳ ዘመቻ እየተካሄደ ነው::
ይሁንና፣ በነዚሁም ምክንያቶች ደግሞ፣ መኢሶን ከእንቅስና ከመሥመሩ የቀጉጣት ያህል እንዷ
ዘገና አላለም:: ለወደፊቱም ዝገና አይልም:: ሃቀኛ ተራማጆችና የአበዩቱ ወገን የሆኑት
ታጋዮች ሁሉ ይህንን ሃቅ በውሉ ያውቃታል::
ከነገዲሁም፣ አንባቢያች የኢማሌድህን ጽሑፍና ይህንን የኛን ጽሑፍ <u>ከሰሚቶች ር ቀው</u> በለ
ገበርና በጥሞና እንዲያነቧቸው፣ እንዲያመዛዝኗቸውና በሰይገሱ እንዲመዝኗቸው ጠይቀን ብቻ ወደ
ሚቀጥለው ክፍል እንሻገር:: በሚቀጥለው ክፍል ውስጥ፣ የኢማሌድህ ጽሑፍ እዚህም እዚያም
ሳስቀመጣቸው አንዳንድ ጥያቄዎች ተናገጠ ማስታወሻዎችን ለናስቀምጥ እንሞክራለን::

## 8. <u>አንዳንድ ማስታወሻዎች</u>

### 8.1. <u>የብሄረሰቦች ጥያቄ</u>

የኢማሌድህ ጽሑፍ በተከከለ እንደጠቀሰው፣ በበሕድ ቁ.60 ውስጥ:—

"የብሄረሰቦች ጥያቄ እንደሌሎቹ ዲሞክራሲያዊ መብቶች <u>የሚሟላው</u> የመንግሥት ሥልጣን
በሰፊው ሕዝብ እጅ ውስጥ ሲገባ ብቻ ነው"

የሚለው የመኢሶን አቋም ተጽፏል:: ኢማሌድህም ይህን ከጠቀሰ በኋላ፣ ይህ "አቋም
ትክክለኛ ቢሆን የዲሞክራሲ መብቶች ለጥቂቶች ያለገደበ አሁኑኑ' የሚለውን መፈከር <u>በቀጥታ
ይቃረናል</u>" /20/ ቢል ተቾቷል::
በኛ አስተሳሰብ፣ ነገሩ እንዲህ እስከዚህ ደረሰ የሚያከራከር አይደለም:: ይልቁኑ የሚ
ያስገርመው ነገር፣ ኢማሌድህ የጠቀሳቸውን ጉዳዮች እንደ "<u>ተቃራኒ</u>" ወይንም "<u>ከቀጥታ ተቃ
ራኒ</u>" አድርጉ ማቅረቡ ነው:: ይህንንም በገመለከተ፣ በእውነተ ኢማሌድህ በመኢሶን ጽሑፍ
ውስጥ "ተቃራኒ" ነገሮችን ፈልጉ ፈልጉ አይቷል ብለን አሰብን:: ኢማሌድህ "ተቃራኒ" ነገ
ሮችን ለማጋለጥ ሲል፣ የገባበተን ቅራኔ ስናስበውም፣ ለባቸን በሳቅ ፈረሰ::
ምክኒያቱም የጠቀሳቸውን ጥቅሶች ተመሰስ በመለከታቸው ኖሮ፣ እንዳቸውም "ቅራኔ" ባላገኘ
ባቸው ነበር::

.../27



ባጥሩ አንዱ የፖለቲካ ገበ፣ በዚህ ጊዜ "ይሟላል" ስለተባለ፣ ለርሱ "አሟላተ" <u>አሁኑኑ</u>
እና ዛሬ "ዲሞክራሲያዊ መብቶች" አያስፈልጉም ማለተ አይደለም:: እርሱ "እንዲሟላ" <u>አሁኑኑና</u>
ዛሬ ዲሞክራሲያዊ እርምጃዎችን መውሰድ አያስፈልገም ማለተ አይደለም:: መኢሶን፣ በብሄረሰቦች
ጥያቄ ላይ <u>አሁኑኑ</u> እንዲወሰዱ የሚያቀርባቸው ሃሳቦችም "ከሰጣን በሰፊው ሕዝብ እጅ ውስጥ
መግባቱን" የሚያገዙ እንጂ፣ "የሚያረጉ" አይደሉም:: አለበለዚያ ከዚህ በላይ እንዳልነው፣
ፕሮግራምን እንደ ገገርተ መውሰድ ያስፈልጋል:: መኢሶን በገገርተ አያምንም::
ወይንስ ኢማሌድህ ዲሞክራሲያዊ መብቶች አሁኑኑ መለቀቃቀቸውን የሚያወመው፣ ሥልጣን ወደ
ሰፊው ሕዝብ እጅ መግባቱን በመፍራተ ይሆን?
ይህ ካልሆነ፣ ኢማሌድህ የጠቀሳቸውን ጉዳዮች "ከቀጥታ ተቃራኒ" አድርጉ የሚያቀርባቸው
ለምንድነው? ጉዳዩን አጥተተ ይሆን? ወይንስ "ከበተ ካልቆለበተ ከበተ ለቀሟ" ሂዷል?

### 8.2. <u>የዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ</u>

ስለዚህ ጥያቄ በአጭሩ ዘመን ጋዜጣ ላይ ጥምር "ውይይት" ተካሄዶበት እንደነበረ የሚ
ታወስ ነው:: "ውይይቱም" እንዴት እንደ ተመራና በኋላም እንዴት ታፍኖ እንደ ተቋረጠ በሁሉም
ዘንድ ይታወቃል:: እንደዚሁም፣ በዚያን ጊዜ ለአጭሩ ዘመን ጋዜጣ የተላኩት እያሌ ጽሑፎች
እስከዛሬም ቢሆን የመረቢዛያችን መሳቢያዎች እንዳሞቁ ናቸው::
የኢማሌድህም ጽሑፍ ይህንኑ በማስታወስ ይመስላል፣ በጽሑፉ ውስጥ "ማርክሲስት ሌኒኒስቶች
መቸም" ይላል:—

"ማርክሲስት ሌኒኒስቶች መቸም በመካከላቸው ያሉትን ልዩነቶች በቀዳሚያ የሚፈቱት
ወይንም የሚያስወግዱት <u>በውይይት ነው</u>:: ስለዚህም ውይይቶችንና ክርክሮችን፣ በየ
ስሳናቸቸው አማካኝነትና በህጋዊ መድረክም ለማካሄድ ሙከራ አድርገዋል" /19-20/

እርግጥ ነው:: የድርጅቶች ልሳናች፣ የየድርጅቶች <u>ነፃ ጋዜጣዎች</u> በመሆናቸው በነርሱ ላይ
እንደሁኔታውና ጊዜው ውይይት ዲሞክራሲያዊ በሆኑ መንገዶች ተካሄዷል:: በመኢሶንም በኩል ገና
የሚቀጥል ምዕራፍ ነው:: ይሁንና፣ "በህጋዊ መድረክ" የሚባለውን ግን፣ እነብ ቢባል <u>ገሃዱ
ሸፍጥ</u> በማለት እንድንገተቸው እንገደዳለን:: "የውይይቱ" አመራር፣ በኋላም መታፈንና መቋረጥ፣
በምንም ዓይነት ማስክ ቢሆን ሊሸፈኑ እንደማይቸሉ መገለፅ ተርፍ ነገር ይመስለናል:: የአደ
ባባይ ምስጢር፣ እገር ያወቃቸው ጉዳዮች ናቸው::
በቻ እዚህም ላይ ተመስስን እንጠይቃና፣ ኢማሌድህ "ልዩነቶች በቀዳሚያ የሚፈቱት ወይንም
የሚወገዱት በውይይት ነው" ካለ አይቀር፣ በዚህ ጽሑፍ ክፍል ሁለተ ውስጥ ያነሳናቸውን ጉዳ
ዮች ሁሉ የደበቀው ለምንድነው? ወይንስ ኢማሌድህ <u>አሁንም</u> እንዲ የእየተመፃደቀ ራሱን፣ አባ
ሎቹን፣ ሰፊውን ሕዝብ በገሃዱ እየደለለና እያታለለ ነው?
ነገር ግን የኢማሌድህ ጽሑፍ በዚህም ብቻ አያበቃም:: ቀደም ሲገለ እንደጠቀስነው፣ እር
ሰው ራሱ ዳኛና ጠበቃ ሆኖ የሚከተለውንም ፍርድ ተገበዋል::

"የዲሞክራሲ መብቶች ለጥቂቶች ያለገደበ፣ አሁኑኑ፣ ባስቸኳይ፣ ባፋጣኝ የሚለው
መሰሪና ጎጂ አስሬፌ መፈከር በርዕዮተ ዓለም ትግል ተሸንፏል:: ተጋልጧል::
ሰፊው ሕዝብ አልተቀበለውም::" /20/...

ኢማሌድህ በእውነተ እዚህ ላይ ሲደርስ ጣፊያ ጣፊያውን እየቀጠረ ነው:: ኢማሌድህ እተ
ኩሮ በመለከተ፣ ይልቁኑ ዛሬ በገሃዱ የሚታየው ነገር፣ ሰፊው ሕዝብ ስለዚህም ለመናገር ባይ
ቾለ ቁርተ እንደታፈነ መሆኑን በቀላሉ በተረዳው ነበር:: የነበረቱም ዲሞክራሲያዊ መብቶች
እድገ እንደጠበበና በኃይል እንደተገደቡ በተረዳው ነበር:: ሕዝባዊና ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች፣
የሕዝባዊነትና የዲሞክራሲያዊነት ባህሪያቸውን እያጡ፣ ወደመንግሥታዊ ድርጅትነት እየተለወጡ
መሄዳቸውን በተገነዘበ ነበር:: የመንግሥት የመወቀሚያና የበለላ ድርጅቶች እየበፉና እየደለቡ
መሄዳቸውን በተመለከተ ነበር:: ስለዚህም፣ ፍርሃት፣ እርስ በርስ መጠራጠር፣ ራስን ማዳን፣
"አሺ ጌታዬ"፣ ጥፍን ያለው አድርባይነተ መረገ ለቀው መስፋፋታቸውን በተረዳ ነበር:: እንደ
ዚሁም፣ እንደሚባለው "ቢቷን ዘግተ ደርገን የማያማ" እንደሌለ ባወቀ ነበር:: ስለዚህም
ደግሞ፣ ወዝአደሩ፣ ወጣቱ፣ መለዩ ለባሹ፣ አገር ወዳዱ፣ እርሶ አደሩ፣ ጭቁን ብሄረሰቦች፣
... ወዘተ.፣ የዲሞክራሲ መብቶችን አስፈላጊነት ከምንጊዜውም ይልቅ እየተረዱት መሄዳቸውን
በተገነዘበው ነበር::... ወዘተ:: በመጨረሻም፣ ሰፊው ሕዝብ ለዲሞክራሲያዊ መብቶች የሚ
ያደርገውን ትግል ከሁኔታዎች ጋር እንደዝበ እንደ ተያያዘው በተረዳው ነበር:: — ትግሉ
ይቀጥላል::

### 8.3. <u>ይህቾ "ዲሞክራሲ እንዱ የመንግሥት ገጸታ ነው" የሚሏተ ነገር</u>!

ይህቸን የሌኒን ጥቅስ፣ መቼም እንደሚለሪዱ የሚወዳት ፍጡር የለም:: ይሁንና፣ ይህቸኑ
ጥቅስ እንደሚለሪዱ ያለተረዳተ፣ ወይንም ሆነ በሎ አዘውትሮ ወዝገበር ለመገዛተ የሚጠቀም
ባተ ሌላ ፍጡር ደግሞ ተፈልጎ አይገኝም:: ለመሆኑ ምን ማለተ ናተ? ችግሩ ከምን ላይ ነው?
እንደኛው የአበዩታችን ችግር፣ በሃገራችን ውስጥ ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ገና <u>በመሠረቱ</u>
<u>ሰዎች</u> ላይ መሆኑም ነው:: ይህ ባይገስ ገና <u>መሠረተ አለመርገጡም</u> ነው:: ስለዚህም፣ ሰዎች ነገ
ሮችን ሁሉ "ጥገተ ጥገተ በጋር ዉጥ ሥርዓተ ዘመን" ከማለተ ተነስተው ለመገለፅ ይሞክራሉ::

.../28

ከዚህም የተነሳ በጣም ቀላል የሆነና ሽማቲክ አቀራረቦች እጅግ የተለመዱ ሆነዋል:: እስከ ዚያም አጠቃላይ ዕውነቶችን በመደርደር /በዚያት፣ ጥሬት፣ አመርታ.../ ሊያስፈቸው ይሞክራሉ:: በዚህም ደረጃ፣ የማቴሪያሊዝም ዲያሌክቲክስን ቃላቶችና ፀገስ ሃሳቦች በመወርወር ብቻ አስጣት "እንገዛለው..." በማለት፣ ተራር ለመሥራት ይሞክራሉ:: ወይም ጥቅሶችን በጥቅ በማውጣትና ለመተንተን ገን እስከዚህም ሙከራ፣ ችን ለመናድ ይሞክራሉ::

ባይገነሱን መሣሪያ አድርጉ ነባራዊና ጊዜያዊ ሁኔታዎችን ለመተንተን ገን እስከዚህም ጥረት አይደረገም:: አንድ አጠቃላይ ዕውነት፣ አንድ የሚሰበ ጥቅስ፣ አንድ የሚ... ከአንድ መጽሃፍ፣ ከአንድ የታሪክ "ተሰባይነት"...ወዘተ. ከተገኙ፣ እነርሱ ለአዳማጭ አስ ሰበ አባባል፣ ወይም አንድ የታሪክ ተፈላጊ ሆነ ባጋጣሚ ከተገኙ፣ እነርሱ ለአዳማጭ አስ ጋዜጣ፣ ከአገሪቱ በጣቂ ወረቀት ውስጥ ተፈላጊ ሆነ በአንድ በኩል በ"ጥቅስ" ሰም ከአንገብጋቢ ኪሳቾ ድረስ ይደጋገማሉ:: በእንደዚህ አይነትም፣ በአንድ በኩል በ"ጥቅሶች" በስተደርባ ይመሸጋል:: በሌላው በኩል፣ እንደሚ ጥያቄዎች ለመሸሸ ይሞክራል:: ከ"ጥቅሶች" በስተደርባ ይመሸጋል:: ይዳፈናሉ...:: ባለው "በጥቅስ ጩራፍ" አስረካሪ ጥያቄዎች ይተፏሉ:: ባይገነሳዊ ትንተናን "የጥቅሶች አምለከ" ይተ ነገር ገን በዚህ ዓይነት ከተጠለ ደግሞ፣ ግርክሲዝም የትግል መሣሪያ መሆኑ ቀርቶ፣ ካዋል:: አደገና የሆነ ቀኖናዊነት ይሰፋፋል:: ባይገነሳዊ ትንተና መሣሪያ መሆኑ ቀርቶ፣ የጥቅሶች መጋዘን ይሆናል:: ደግሞ ይሆናል:: የባይገነሳዊ ትንተና መሣሪያ መሆኑ ቀርቶ፣ በአባት ተለበለበ እንደተገተረ ገንዱ ደረቅ ይሆናል:: እንደህይወት ዛፍ ለምለም መሆኑ ቀርቶ፣ የቀን አድርባዮችና የከሃዶች መሣሪያ ይሆናል:: ...

እንግዲህ ሌኒን፣ "ዲሞክራሲ አንዱ የመንግሥት ገጽታ ነው" ሲል ምን ማለቱ ነው? ከሚለው የሌኒን መጽሃፍ ውስጥ ማሌሪዱ ይህችን ጥቅስ የሚወስደው "መንግሥትና አብዮት" በማለት የሚተረጉመው፣ ሌኒን ነው:: እርሱን በመጥቀስ እንጀምር:: ማሌሪዱ "ገጽታ" "ፎርም" ሲል የገለፀውን ነው::

"ዲሞክራሲ የመንግሥት ፎርም ነው:: አንደኛው የመንግሥት ዓይነት ነው:: ስለዚህም እሱ /ዲሞክራሲ/፣ እንደማንኛውም መንግሥት ሁሉ፣ ባንዱ ወገን፣ የተደራጀውን፣ በሰዎች ላይ የሚፈጸመውን የተቀናበረ ጥቃና ይወክላል:: በሌላው በኩል ደግሞ፣ የዜጎች እኩልነት ፎርማሊ መታወቁን ሁሉም የመንግሥትን መዋቅርና አስተዳደር በሚ መለከቱ በኩል ያላቸው የመወሰን መብት መጠበቁን ያመለክታል:: በዚህም ዲሞክራሲ እየዳበረ ሄዶ ከአንዱ የተወሰነ ደረጃ ላይ ሲደርስ፣ ከካፒታሊዝም ጋር በአብዮታዊ ትግል የተሰነቀውን የወዛደሩን መደብ በከፍተኛ ደረጃ ያስተባብረዋል:: ያስተሳ ስረዋል:: የወዛ አደሩ መደብ ቡርዧዎቹን እንዲደመስስ፣ ወደአፈር እንዲደለጠው የቡርዧዚውን ሪፐብሊክ መንግሥት ማሺን /ቋሚ ሠራዊትን፣ ፖሊሱን፣ ቢሮክራሲውን/ ከምድር ገጽ እንዲያጠፋ ያስችለዋል:: እነዚህን፣ የቡርዧዚውን የመንግሥት ማሺን የበለጠ ዲሞክራሲያዊ በሆነ የመንግሥት ማሺን እንዲተካ ያስችለዋል:: ይህኛው የመንግሥት ማሺን ግን፣ የታጠቁት ወዛአደሮች የሚንከባከቡበት እነርሱም ወደሚሊሺያ የሚ ደራጁበት፣ ህዝቡ በሙሉ የሚሳተፍበት ይሆናል::"

"Democracy is a form of the state, one of its varieties. Consequently, it, like every state, represents on the one hand the organized, systematic use of violence against persons; but on the other hand, it signifies the formal recognition of equality of citizens, the equal right of all to determine the structure of, and to administer, the state. This in turn, results in the fact that, at a certain stage in the development of democracy, it first welds together the class that wages a revolutionary struggle against capitalism - the proletariat, and enables it to crush, smash to atoms, wipe of the face of the earth the bourgeoisie, even the republican bourgeoisie state machine, the standing army, the police and the bureaucracy, and to substitute for them a more democratic state machine, but a state machine nevertheless in the shape of the armed masses of workers who develop into a militia in which the entire population takes part."

እንደሚታየው፣ የማሌሪዱን "ገጽታ" ሌኒን እንደዚህ ገለጸ በሆኑ ቃላቶች ነው የሚገልፃቸው:: ተጨማሪ የማብራሪያ ትችት እንኳ የሚጠይቅ አይደለም:: ይሁንና፣ ማሌሪዱ ይህንን የሌኒን ጥቅስ ያስተረጓውን ያህል፣ ወይም ባወቅኩን ባይነት ሆን ብሎ ወዘገበር የሚነዛውን ያህል፣ ሌኒን ደግሞ ከመቀሱ ጥቅስ ቀጥታ መሥመሮች ከፍ ብሎ እንዲህ ይላል::

"የወዛአደሩ መደብ ከካፒታሊስቶች ጋር ለነፃነቱ በሚያደርገው ትግል፣ ዲሞክራሲ እንደ ህይወት አስተገፋስ የሚያስፈልገው መሣሪያ ነው:: ነገር ገን ዲሞክራሲ የማይሻገሩት መጨረሻው ድንበር አይደለም:: ከፊውዳሊዝም ወደ ካፒታሊዝም፣ ከካፒታሊዝም ወደ ኮሙኒዝም ካሉት የጠገገር ደረጃዎች ውስጥ አንደኛው ደረጃ ነው"





"Democracy is of enormous importance to the working class in its struggle against the capitalists for its emancipation. But democracy is by no means a boundry not to be over-stepped; it is only one of the stages on the road from feudalism to capitalism, and from capitalism to communism"

/ሁለተኛ ጥቅሶች የተወሰዱት፣ ሌኒን "መንግሥትና አብዮት"፣ የቻይና እትም፣ 1973 ገጽ 118–119/

የህናው የሌኒን ገለፃም እንደዚሁ በጣም ገለጸ ነው:: ታዲያ የናንቱ "ሌኒኒስቶች" ሌኒንን በ"ሌኒን" ለመዋጋት ቆርጠው የተነሱት ለምን ይሆን? ጠፍቷቸው? ወይንስ የወዛአደሩ መደብ የትግል መሣሪያ የሆነውን የዲሞክራሲ መብቶች፣ የወዛአደሩን ጆሮ ሊነፍጉት ስለፈለጉ? እና፣ በዲሞክራሲ የደረደውን ወዛአደር ስለሚፈሩ ነው እንላለን::

በተጨማሪ ደግሞ፣ የፈለገነውን ዓይነት መንግሥት ለመውሰድ እንችላለን:: መንግሥቶች ባጠቃላይ መለካቸው አንድ፣ መንግሥት በመሆናቸው ብቻ፣ "ያው መንግሥት መንግሥት ነው" ብሎ ለማለት አይቻልም:: ሁለተኛ፣ በታሪክ የሚታወቁ የመንግሥት ዓይነቶች /ስቴት ፎርሚሽንስ/ አንዱ ዓይነት አይደሉም:. የባሪያ አሳዳሪና የባሪያ አሳዳሪ፣ የፊውዳልና የፊውዳል፣ የቡርዧና የቡርዧ... ወዘተ መንግሥት አሉ:: "በሽሊስት ነን" የሚሉና ሶሺሊስት መንግሥታትም አሉ:: ለምሳሌም፣ የዲሞክራሲን ጥያቄ እንውሰድ::

በዲሞክራሲያዊነት ሚዛን፣ ለምሳሌ ሁሉም የቡርዧ ሪፐብሊኮች አንድ ዓይነት "ገጽታ" የላቸውም:: እንደው ባጭሩ ከሌሴ ፌር /laisser faire/ የቡርዧ ዲሞክራሲ አገሮች እስከ ፋሺስት መንግሥትና አገዛዝ ድረስ ይደርሳሉ:: በዚህም፣ የቡርዧ ሪፐብሊኮችን "ዲሞክራሲያዊነት" ከ – እስከ ለንረዳ እንችላለን:: ስለዚህም፣ በፋሺስት የቡርዧ መንግሥት ስር የወዛ አደሩ የመደራጀት መብት የታፈነውን ያህል፣ በሌሎቹ የቡርዧ ሪፐብሊኮች ውስጥ ወዛአደሩ የተ ሻለ የመደራጀት ዕድል አለው:: ይህንን ዕውነት፣ "ገጽታ" በማለት እሌ ለማለት አይቻልም:: እንደዚሁም በተጨማሪ፣ ለምሳሌ ሌኒን በጊዜው ከነበሩት የቡርዧ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊኮች ሁሉ፣ በተለይ የስዊስን ቡርዧ ዲሞክራሲ ያደንቅ እንደነበር የታወቀ ነገር ነው:: ምክንያቱም ሌኒን እራሱ ይል እንደነበረው፣ "የቡርዧ ዲሞክራሲና የቡርዧ ዲሞክራሲ አሉና"::

"የቡርዧዚን ዲሞክራሲ በመናፈቅ ነው" የሚል አጉል ዘመቻ እንዲከፈትብን ጥሪ ማድረግ አይሁ ገብጋና፣ እናም የምንለው እንደሌኒን ነው:: አዎን! የአገራችን ገበሬ ከበርቱና ወዛአደሩ በታሪኩ ውስጥ የቡርዧ ዲሞክራሲን እንኳ ቢቀምስ ኖሮ፣ አብዮታችን የበለጠ ቀለጠ፣ ሥርዓትና ህይወት ይኖረው ነበር:: ይህንን የማይረዱት ቀኖናዊያን ብቻ ናቸው::

በሰተና፣ ሌኒን "ዲሞክራሲ አንዱ የመንግሥት አንዱ ገጽታ ነው" ሲል፣ በተጨማሪ፣ የአን ዱን መንግሥት "ገጽታ"፣ ያ የተባለው መንግሥት በሚፈቅደው ዲሞክራሲ መጠን /በአዋጅ፣ በህግ፣ በደንብ፣ በተግባር.../ ዲሞክራሲያዊነቱን ወይም ፀረ ዲሞክራሲያዊነቱን ለናነብ እንችላለን ማለት ነው:: ወደምሳሌያችን እንመለስና፣ ይህ ባይሆን ኖሮ፣ ለምሳሌ በቡርዧው ዲሞክራሲ ዓለም ውስጥ ወገ አጥባቂ፣ ሊበራል /ለዘብተኛ/፣ ሶሻል ዲሞክራሲ... ወዘተ የሚሉትን ስያሜ ቶች ባልተመለከትን ነበር:: ለለበለዚያ፣ እንደው በደፈናው "የቡርዧ መንግሥት የቡርዧ፣ የህዝባዊ መንግሥት የህዝባዊ..." ወደሚለው አጠቃላይ ደፍን አነጋገር እንገባለን:: ይህ ደግሞ "እንቅልፍ እንቅልፍ ነው" ከማለት በምንም አይለይም:: እዚሁ ላይ፣ እናም እንደሌኒን "ወዳጂ ቲዎሪ ደረቅ ነው፣ የህይወት ዛፍ ግን ለምለም ነው" እንላቸዋለን::

እንግዲህ ሌኒን ስለዲሞክራሲ ጉዳይ የተናገረው ከዚህ በላይ የተመለከትነውን ነው:: ይሁ ንና፣ ማሌሪዱ በዚህች የሌኒን ጥቅስ ለማወናበድ የቀን አድርባይነትን ለመሸፈን የሚጥረውን ያህል፣ ተወጥሮ ሲያዝ ደግሞ፣ ተራማጆችን ሁሉ "በገሬ" በኩል ይቀደማቸዋል፣ የሚገባተለውን ያህል፣ ተወጥሮ ሲያዝ ደግሞ፣ ተራማጆችን ሁሉ "ደርግ እስከ ገበሬ ከበርቴ ነው:: ወላዋይ ነው:: ዱንጉጥ ነው:: በደርግ ስር ይላል:– "ደርግ እስከ ገበሬ ከበርቴ ነው:: ወላዋይ ነው:: ዱንጉጥ ነው:: በደርግ ስር ዲሞክራሲ መብቶችን ያለገደብ ለማግኘት አይቻልም:: በተግላቻችን" ይላል:: "የሰም ዛሬም ዲሞክራሲያዊ መብቶችን በሰላም /አዎን! በአዋጅ/ ከጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ቢሆን እያሉ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን በሰላም /አዎን! በአዋጅ/ ከጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ለማግኘት ይቻላል" የሚሉትን ደግሞ፣ "አድርባይ፣ መሰሪ፣ ተጥቀ አሰሪ..." እያለ ይከሳ ቸዋል:: ከተራማጆች ሁሉ ተራማጅ ሆኖ ቁጭ ይላል፣ የኢትዮጵያን ሕዝቦች "ባለውም አላወቃ ችሁበት፣ በትግላችን" ይላቸዋል::

ሃቀኛ ተራማጆች፣ "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ከደርግ /=አብዮታዊ ሰደዱ/ ለማግኘት ካልተቻለ ቁርጥ ያለ አቋም እንወስድ" ሲሉ ደግሞ፣ የቀን አድርባዮቹ ድርጅቶች ሁሉ ባንድነት ይሆኑና "አብዮታዊያን ህጋዊ ትግል ለማካሄድ በፍፁም የማይቻልበት ደረጃ ላይ ወቶ ፍፁም ደረስንና" ይላሉ:: እነዚህ አድርባዮች ገን፣ አድርባዮች ስለሆኑ፣ ህጋዊ ትግል የሚቻለው አብዮታዊ ሰደዱ /="ደርግ"/ ዲሞክራሲያዊ የሆነውና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ያወቀውን፣ የጠበቀውን፣ ያከበረዉን ያህል እንደሆነ ፍፁም ሊረዱት አልቻሉም:: ወይም አለፈለጉም:: የደርግ ወላዋይነትና ዱንጉጥነት... ወዘተ ደጋግሞ ማሳወቅ ብቻ አገሪቱ እርምጃ ወደፊት እይ ወስደንም:: ይህ በዙ ስበላ ቀንጣን ይወጥረናል:: ምንም ባለበላ ረዥም ይዘናል የሚለውን ተፈጥሮያዊ ዕውነት ደጋግሞ የማሳወቅ ያህል ነው:: ደርግ የገበሬ ከበርቴው መደብ ከፍል መሆኑን ደጋግሞ መግለፅ ብቻ ቁጉ የለውም:: የገበሬ ከበርቴ መደብና የገበሬ ከበርቴ መደብ አሉ:: የገሬ ገበሬ ከበርቴና የገሬ ገበሬ ከበርቴም አሉ::

መንግሥት "ግራነት" እስከምን ድረስ ነው?
ይለቁኑ፣ የገዐብ ከበርቱ የደርግ መንግሥት ዲሞክራሲያዊ "ገጽታ" እስከምን ድረስ ነው?
የገዐብ ከበርቱ፣ ማሌሪድና ሌሎቹ የቀኝ አድርባይ ድርጅቶች "ዐርገጥ ነው"
እነዚህ ጥያቄዎች ቢነሱ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው አስተዳደር ለህዝብ ጥያቄዎች የዘሆነ ይላሉ:-

"ዐርገጥ ነው:: የረፐብሊኩን ሂደት አገዟል:: እስከሁን ከህዝብ ጐን ቆሟል:: ጅር አስለጠም:: የህዝብ አስተዳደር ስላልሆነ፣ አርግጠው የመንግሥት ገን፣ በመጨረሻ ትንተና ላይ፣ በዚህ ሁኔታ የዲሞክራሲ መብቶች ለጥቂቶች ያለገደብ አውታር ገና ስላልተደመሰሰ፣ በዚህ ሁኔታ የዲሞክራሲ መብቶች ለጥቂቶች ያለገደብ ሊገኙ አይችሉም:: በዚህ ሁኔታ የመንግሥት ገጽታ ነው" የሚለዉ የሌኒን አባባል ትክክል ቢቸሉ ኖሮ፣ ዲሞክራሲ የመንግሥት ማቋቋም አስፈላጊነት አይኖርም ነበር::" ባልሆነም ነበር:: ህዝባዊ መንግሥት ማቋቋም አስፈላጊነቱ አይኖርም ነበር::"
/ረጠ. ቁ.21/

እንገዲህ ተመለከቱት:: ታዲያ ምን ይሻላል? ሲባል፣ መልሱ "በትግላችን" ማሌሪድ ይህንን ሁሉ ከተናገረ በኋላ፣ ..."ማን ከማን ጋር እንደሚታገልና በመታገል ላይ የሚለው ነው:: ለናም፣ "በመጨረሻ ትንተና" ይቀራል!! ይህ "እስከሁን ድረስ ከህዝብ ጐን የቆመው መንግሥት" እንዳለ ገለፀ ባይሆንለን "ዲሞክራሲያዊ ገጽታ" እንዳለው ለማወቅ ተቸገርናል!! ምን ዓይነት "ዲሞክራሲያዊ ገጽታ" እስከዚህም አስቸጋሪ አይደለም::

ነገር ግን ጉዳዩ እስከዚህም አስቸጋሪ አይደለም:: ከዚያም በኋላ "ደርግ" በመጀመሪያ አስተባባሪ ኮሚቴ ነበር:: ከዚያም ደርግ ነበር:: ከዚያም በኋላ "ደርግ" /=አብዮታዊ ሰደድ/ ሆነ::
በያንዳንዱ ደረጃ ራሱን የቻለ ባህሪይ እንደነበረው መግለፅ ትርፍ ነገር ነው:: በያን ያንዱ ደረጃ ሃያሎች ተራማጆችና ሰፊው ሕዝብም የተለያዩ አቋሞችን እንደወሰዱ ማበራራቱ፣ በሃገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃም አስላለፍች የታወቀውን መጽሐፍ ይሆናል:: በተለይ በመጨረሻው ደረጃ ላይ፣ በበሄራዊ ፖለቲካ ውስጥ ወሳኝ የሆኑ የውጭ ተለውጠዋል:: ... ወዘተ.
ኃይሎች እንደተቀላቀሉበት የታወቀ ነው:: "መጨረሻው" የሚደርሰው መቼ ይሆን?
እንግዲህ፣ የማሌሪድ "የመጨረሻ ትንተና" "ደርግና "ደርግ" አንድ ናቸው ወይ?
አስተባባሪ ኮሚቴ፣ ደርግና "የህዝብ አስተዳደር ከሌለ፣ አርግጠው የመንግሥት አውታር ገና ካልተደመሰሰ" ይለቁኑ
"ከዚህ ሁኔታ የዲሞክራሲ መብቶች ለጥቂቶች ያለገደብ" አሁኑኑ አያስፈልጉትም ወይ?

እና፣ "ለጥቂቶች ያለገደብ አሁኑኑ" በማለት፣ ከዚህ "በመጨረሻ ትንተና" የህዝብ አስተዳደር ካልሆነው" አስተዳደር እንጠይቃለን እንላለን::
ማሌሪድ፣ "ከቶ ሊገኙ አይችሉም" ይላል::
እና፣ ይህ ዐውነት ነው:: ይሁንና "የደርግ" መንግሥት እስከመደበና እስከ ዲሞክራሲያዊት ገደብ ድረስ ገደብ ቢያውጀው፣ አቋሙን በደስታ እንቀበለዋለን:: በሥራ ላይ እንዲውልም እንታገላለን:: "የደርግን" መንግሥት ዲሞክራሲያዊ "ገጽታ" ከማድነቅ ወደ ኋላ አንልም እንላለን::
ማሌሪድ፣ ይህማ ከሆነ፣ "ዲሞክራሲ የመንግሥት ገጽታ ነው የሚለው የሌኒን አባባል ትክክል ባልሆነ ነበር" ይላል::
እና፣ ስለዚህም "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጥቂቶች ያለገደብ አሁኑኑ" እንዲታወቁ የምናደርገውን ትግል እንቀጥላለን:: "ከደርግ" መንግሥት ዲሞክራሲያዊ "ገጽታ" ብቻ አንወሰንም" እንላለን::
ማሌሪድ፣ ይህማ ከሆነ፣ "ህዝባዊ መንግሥት ማቋቋም አስፈላጊ ባልሆነ ነበር" ይላል::
እና፣ "ደርግ" በዲሞክራሲያዊ "ገጽታው" ለከ ገደብ የሰጠው ዲሞክራሲያዊ መብት፣ የሰፊውን ሕዝብ ትግል ለማስተባበርና ለማስተባሰር ይጠቅማል እንላለን:: ህዝባዊ መንግሥት የበለጠውን የተቃረበ ይሆናል እንላለን::
ማሌሪድ፣ "በመጨረሻ ትንተና" ይላል::
እና፣ ታዲያስ ምን ይሻላል? እንላለን::
ማሌሪድ፣ "በትግላችን" ይላል::
እና፣ ማን ከማን ጋር ነው የሚታገለው? እንላለን::
ማሌሪድ፣ ጣሪያዎችን ካማተረ በኋላ፣ አሁንም መልስ "በትግላችን" ይላል::
እና፣ ጥያቄ አቀርበን ነበር፣ እንላለን::
ማሌሪድ፣ "በትግላችን" በለናል፣ "በትግላችን" ነው ይላል::
እና፣ ይህማ የማይቀረው ጉዳይ ነው፣ እንላለን:: የመደብ ትግልን ተቀብሉ፣ እንደ ፖለቲካ ድርጅት ተመሥርቶ፣ ካልታገሉማ፣ ወደ ደበረ ጸጌ መውረዱ የተሻለ ነው እንላለን::
ማሌሪድ፣ "አሁኑኑ" የሚለው ትቶቁ አስፈፂ ነው ይላል::
እና፣ "በመጨረሻ ትንተና" የማሌሪድ አቋም፣ የማሌሪድ ዲሞክራሲያዊ "ገጽታ" ነው እንላለን::

.../31



## 8.4. የመንግሥት ስልጣን ጥያቄ

ስለዲሞክራሲ መብቶች ሲነገር፣ ከኢማሌድህ አባል ድርጅቶች፣ በተለይ ከማሌሪድ፣ ተደጋግሞ የሚሰማው አንዱ ነገር፣ "ዲሞክራሲ ከመንግሥት ስልጣን ተነጥሎ አይታይም" የሚለው "ቲኦሪ" ነው:: "ስለዚህም" ይሏሉ እነዚህ ክፍሎች፣ መኢሶን "ዲሞክራሲያዊ መብቶች አሁኑኑ" ሲል፣ "የመንግሥትን ስልጣን በቀጥታ መጨበጥ ፈልጎ ነው:: መኢሶን የስልጣን ጥም አለበት..."::
ይህ አባባል፣ አነስ በገለ የየህ ነው:: በዐውነቱ ከሆነም፣ የቀኝ አድርባዮቹ በመኢሶን ላይ የሚሰነዝሩት ይህ ክስ፣ ከታናጋሪዎቹ አፍንጫ አርቆ የሚሄድ አይደለም:: ምክንያቱም የሚከተሉት ናቸው::
አንደኛ፣ አንዱን የዲሞክራሲያዊ መብቶችን የሚያከል ጥያቄ ይቀርና፣ ተገቢ የፖለቲካ ጥያቄ አንቧ ከመንግሥት ስልጣን ጥያቄ ጋር የተያያዙ ናቸው:: ስለዚህም፣ ይህንን መደጋገሙ ለጉዳዩ አንዳችም አዲስ ነገር አይጨምርለትም::
ሁለተኛ፣ የፖለቲካ ድርጅት ነኝ ብሎ ተደራጅቶና የፖለቲካ ትግል እያካሄዱ እያሉ፣ የፖለቲካ ሥልጣንን አለፈልገም ማለት አጉል መመፃደቅ ነው:: ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት የሚቋቋመና የሚታገለዉ የፖለቲካ ስልጣንን ለመጨበጥ ነው:: አንዱ የፖለቲካ ድርጅት ይህ ዓላማ እስከሌለው ድረስ፣ ወደ ዐድር፣ ወይንም ወደበጎነብቱ፣ ያለዚያም የአበ ገበርኤል ጠበል ቤቱ ወደሚተመስበት ማህበር ቢለወጥ ይሻለዋል::
ሶስተኛ፣ የፖለቲካ ሥልጣንን ይዞ፣ የመንግሥትን ስልጣን አለፈልገም ማለትም፣ አነስ ቢባል፣ መንግሥትን ከመደቦች ትግል ውጭ እንደሌለ ድርጅት አድርጐ መቁጠር ነው:: ተቀዋሞችንም፣ ወደቄድቃንና ቅዱሳን ዓለም ማሻገር ነው:: በዚህ ዓይነቱ፣ ህዝቦችም "የተባረኩ አማኞች" ሊሆኑ ነው:: ነገር ግን ለበፋቱ የመደቦች ትግል የሚሉት አለ:: መንግሥትም ከመደቦች ትግል ውጭ አይደለም:: እንደውም፣ የማርክሲዝምን ሀሁ መድገም አይሁንብንና፣ በከፍተኛ ደረጃ የተደራጀውና የገዢው መደብ ወይንም ክፍል ጠንካራ መሣሪያ ነው:: ተቃናቂዎች ቢሆኑ፣ ከመደቦች ትግል ውጭ "አይፀድቁም"::
አራተኛ፣ መኢሶን "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጥቂቶች ያለገደብ አሁኑኑ" የሚለውን መፈክር ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር አገናዝቦና አያይዞ አንጂ፣ እንዲሁ በሜዳ ላይ አይደለም:: "አሁኑኑ" ማለት ምን ማለት እንደሆነም፣ ከትግል ስልት ለውጥ ስፊትና በኋላም/ከዚህም ጽሑፍ ውስጥ ጥምር/ ተገልጿል:: ከነዚህ ዉጭ የተርገም ተርጉሞችን መስጠት ግን "ካበት ካልዋለበት ኩበት ለቀማ መሄድ" ይሆናል:: ነዉ::
አምስተኛ፣ ከየካቲት 1966 ዓ.ም. አንስቶ፣ በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ የመንግሥት ስልጣን ጥያቄ በከፍተኛ ደረጃ ሲያከራክር የቆየ ነው:: እንደሚታወሰው በ1966 ዓ.ም. የአገዛልካቸው መኮንን መንግሥት ነበር:: በዚህ ዓ.ም. "አስተባባሪ ኮሚቴ" ነበር:: በ1967/68 ዓ.ም. ባንድ በኩል ደርግ ነበር:: በሌላው በኩል የኢሕአፓ "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት" ጥያቄ ነበር:: ከሁለቱም በተለየ ደግሞ፣ ሃያሎች ተራማጆች የቀመሱት "የነቃ፣ የተደራጀና የታጠቀ የህዝብ ትግል" የሚለው መሥመር ነበር:: አለ:: ከ1969 አጋማሽ አንስቶ ደግሞ፣ የ"ደርግ" /=አብዮታዊ ሰደድ/ መንግሥት አለ:: እንደዚሁም፣ ደርግ የገባው "ቃል ኪዳንና" የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም አሉ::
ስድስተኛና በመጨረሻም፣ መኢሶን ለምን ዓይነት የፖለቲካ ስልጣን እንደሚታገል፣ ከፕሮግራሙ በይፋ መውጣት በፊት ሆነ፣ በፕሮግራሙ ውስጥ፣ ወይንም ከዚያ በኋላ ባወጣቸው ጽሁፎች ደጋግሞ ገለፀ አድርጓል:: የኢማሌድህ ጸሐፊ ደራሲያች፣ በጽሑፎቻቸው ውስጥ ደጋግመው የጠቀሱትን ስሕድ 60 ጠንቅቀው ቢያነቡት ኖሮ አንኳ፣ በዚያዉ ቁጥር ውስጥ ከዚህ በታች የምንጠቅሰውን ባጤኑት ነበር::

ሰሕድ 60/ሐምሌ 1969
"የመንግሥትን ስልጣን በሚመለከተው በኩል፣ መኢሶን ቀደምም ዛሬም በዚያው አቋሙ ጸንቷል:: የመንግሥትን ሥልጣን መያዝ ያለበትና የሚችለም አንድ ድርጅት ወይንም ቡድን ሳይሆን፣ የነቃ፣ የተደራጀና የታጠቀ ሰፊ ሕዝብ ነው:: የነቃ፣ የተደራጀ፣ የታጠቀ ሰፊ ሕዝብ ማለት ደግሞ፣ በማርክሲዝም ሌኒኒዝም የሚመራ /ዐውነተኛ/ የወዛአደር ፓርቲና በዚህ ፓርቲ አመራር ስር የቆመ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባርና ህዝባዊ አብዮታዊ ጦር ያሉት ማለት ነው:: እነዚህ በስተ መሣሪያዎች እስከሌሉት ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፊውዳሊዝምን፣ ኢምፔሪያሊዝምንና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ሊደመስስ አይችልም:: እነዚህን በስተ ጠላቶች ካልደመሰሰ ደግሞ፣ የመንግሥትን ሥልጣን ለመያዝ፣ ለመደላደልና አዲስ ህበረተሰብን ለመገንባት ፈፅሞ አይችልም::
"ድርጅታችን ለዚህ አይነቱ የህዝብ ሥልጣን እንደሚታገልና፣ ይህም ትግል ደግሞ የረጅም ጊዜ መራራ ትግል እንደሚሆን ዛሬ ባይሆን፣ ገና በጨለማው የኃይለ ስላሴ ዘመን አምርሮበት ሰፊውን ሕዝብ ሲቀሰቅስ የኖረበት የፖለቲካ መሥመር ነው:: ይሁንና፣ የቀኙም ሆኑ "የግራ" የመኢሶን ተቃዋሚዎች፣ ይህንን የድርጅታችንን አቋም እያጣመሙ፣ ነጩን ጥቁር፣ ጥቁሩን ነጭ እያሉ፣ ለማንም ሃቅና ገለጽ የሆነውን ነገር በአሉባልታ እየሸፋፈኑ "መኢሶን በቀጥታ ስልጣን ሊይዝ ይፈልጋል" በማለት

.../32

በናና በሌሎች ተራማጅ ድርጅቶች መካከል ጥርጣሬን ለመፍጠር ሲፍጨረጨሩ ቆይተዋል:: እየተፍጨረጨሩም ናቸው::"

እነዚህ ቃላቶች የተፃፉት ገና ከትግል ስልት ለውጥ በፊት ነው:: ዛሬም ቢሆን በዚህ ላይ የምንጨምርበት ሌላ ምንም ነገር የለንም:: በተጨማሪ፣ የኢማሌድህ አባል ድርጅቶች፣ በእጃቸው ውስጥ የሚገኙትን የህብረት ስብሰባዎች ቃለ ጉባዔ ሊመለከቱት ይችላሉ:: በዚህ ለታሪክ የቀረው ቃለ ጉባዔ ውስጥ፣ "የሃሳቡና ገዛቱ" ሠፍሮ ይገኛል:: እናም በቀድ ይዘነዋል:: ከዚህ በተረፈ መኢሶን የፖለቲካ ዓላማና ግብ ያለው የፖለቲካ ድርጅት ነዉ:: እንደ ፖለቲካ ድርጅት ተመሥርቶ "እድሜያችን እንዲያጥር እንፈልጋለን" /ወዘ ሊግ/ የሚሉትን ከናሉትም እንደፀጥን አንቆጥራቸዉም::

## 8.5. "የአብዮታዊ ሂስ" ጥያቄ

የኢማሌድህ ጽሑፍ፣ የመጨረሻ መጨረሻ እንደማፈዘም፣ እንደማንጋጠጥም በሉት የሚያቀርበዉ "ትችት" የመኢሶንን "አብዮታዊ ሂስ" መሥመር የሚመለከት ነው:: ስለዚህም ሲጽፍ እንደዚህ ይላል::

> "ሠገናው መኢሶን! እጉል ሲውጠረጠርና ሲደነፋ በጣም ያስቃል:: ህቡዐ ተገቢ አብዮታዊ ሂስ እንዴት ይሠራል! አብዮታዊ እንቅስቃሴን ለሚገታ ኃይል፣ ቢሮክራሲው ላይ እምነት ላለው ደርግ፣ ምን አብዮታዊ ሂስ ያስፈልገዋል? ደርግ ሲያታልሏት... ይባል የለ!! " /26 – 27/

በእውነቱ ይህንን "ትችት" ዝም ብሎ ማለፍ የተሻለ በሆነ ነበር:: ርካሽ ነው:: ስሜትን ለመቀስቀስ፣ ሽውድ ለማምለጥ፣ ባድ አነጋገሮችን አስጠብጦ ለማለፍ የተፃፈ "ዝባዝንኬ" እንጂ፣ ምንም የሚናገረው ነገር የለውም:: ይሁንና፣ ጥያቄዎች ተወርውረዋልና፣ ባጭሩ አንዱ ንመለስባቸውም እንገደዳለን::

ለመጀመሪያው፣ የመደብ ትግል ቁማር አይደለም:: "አሲሀይ፣ አሳሲሀይ" እንደሚባለዉም ዉዋታ አይደለም:: የተናወም መደብ ቢሆን፣ ሌላውን መደብ ሊያታልለው አይችለም:: እንደዚሁም፣ አንዱን የመደብ ድርጅት /መንግሥትንም ጭምር ማለት ነው/ ለማታለል አይቻልም:: መኢሶንም "ደርግን" የደርግ መንግሥት "ለማታለል" መጨና የሚጉትትበት ምክኒያት የለዉም:: ደርግ "ደር" አይደለም:: መኢሶንም "መጨና ነካሽ" አይደለም:: "ደርግ" መንግሥት ነው:: መኢሶንም፣ የፖለቲካ ድርጅት ነው::

ሁለተኛ፣ ስለ "አብዮታዊ ሂስ" ምንነት መናገር ከፈለግን፣ ስለርሱ መናገር እንጂ፣ እብሪተና ትምክህት የተመላባቸው አነጋገሮች መለደፍ ለመግርም ሆነ ለማስተማር የሚጠቅም አይደለም:: አብዮታዊም አያሰኝም:: ኢማሌድህ ይህንን መረዳትና ከርካሽ አባባሉች በላይ ለመሆን መጣር ነበረበት::

ሦስተኛ፣ ኢማሌድህ፣ መኢሶን ከትግል ስልት ለውጥ በኋላ የወሰዳቸውን የፖለቲካ እርምጃዎች ያቀረባቸውን ሃሳቦች፣ ጥሪዎችና ጥያቄዎች ሁሉ በአንክሮ በመለከታቸው ኖሮ፣ "አብዮታዊ ሂስ" ሁነው ያገኛቸው ነበር:: አለበለዚያ "የአብዮታዊ ሂስን" ትርጉም ጨርሶ አልተረዳም::

አራተኛ፣ ተጨማሪ ምሳሌ ከፈለግን፣ ይህ ጽሑፍ በራሱ እንኳ "አብዮታዊ ሂስ" ነው::

አምስተኛ፣ "አብዮታዊ ሂስ" እንደሚገባኝ፣ አብዮታዊና ዲሞክራሲያዊ እርምጃዎችን ሁሉ መደገፍ፣ ፀረ አብዮታዊና ፀረ ሕዝብ፣ ፀረ ዲሞክራሲያዊ እርምጃዎችን ሁሉ፣ አገናዝቦና አመዛዝኖ ይቅርታ በሌለው ሂስ መቋቋም ማለት ነው:: ስለዚህም ነው፣ መኢሶን ከሁኔታዎች ጋር ከትግል ስልት ለውጡ በኋላም ቢሆን አብዮታዊና ዲሞክራሲያዊ እርምጃዎችን ሁሉ ባለው አቅሙና ባሉት መንገዶች ሁሉ የደገፈዉ:: ባንፃሩ፣ ፀረ አብዮታዊና ፀረ ሕዝብ፣ ፀረ ዲሞክራሲያዊ እርምጃዎችን ሁሉ ባለው አቅሙና ባሉት መንገዶች ሁሉ በመታገል ላይ ያለው::

ስድስተኛ፣ ይሁንና፣ በተጨማሪ ደግሞ፣ ዛሬ መዓት ሂስና ተቃዉሞ የሚቀርብባቸው አያሌ አባባቢ ጉዳዮች እያሉ፣ መኢሶን በነርሱ ላይ አስተያየቱን በይፋ ከመስጠት ተቆጥቧልም:: ይህንንም መሥመር የተከተለው ዛሬም "የአብዮታዊ ሂስ" አቋም ስላለዉ እንጂ፣ በሌላ በምንም ዓይነት ምክኒያት አይደለም:: መኢሶን ነገሮችን ባያመዛዝን ሳንቃውን እንደማይስነጥቅ የታወቀ ጉዳይ ነው::

በመጨረሻም፣ የኢማሌድህ አባል ድርጅቶች አልተረዱትም እንጂ፣ የአብዮታዊ ሂስ አቋም ከ — እስከ የሚስተያየዉ፣ ከደርግ ጋር ሳይሆን፣ ከኢትዮጵያ ህዝቦች ገታት፣ ድርጅትና ተጥቆ ጋር ነው:: ማለትም፣ ከኢትዮጵያ ህዝቦች ህሊናዊ ሁኔታና አገሪቱ ከምትገኝበት ነባራዊ ሁኔታ ጋር ነው:: በዚህ ውስጥ፣ ደርግ ምንም እንኳ የማይታለፈው አንደኛው ክፍል ቢሆንም፣ ለአብዮታዊ ሂስ አቋም ወሳኙ ክፍል አይደለም::

እንግዲህ በዕውነቱ፣ መኢሶን ለምን ኩዴታ ሲጠነሰስ አልተገኘም? የሚል ቅሬታ ከሌለ በስተቀር፣ የመኢሶን መሥመር ዛሬም ቢሆን "አብዮታዊ ሂስ" ነው:: ይህንንም ታሪክ ገና ያሳየናል:: ምክኒያቱም፣ መኢሶን የኢትዮጵያ ህዝቦች የሚገኙበትን ነባራዊና ህሊናዊ /በተለይም ህሊናዊ/ ሁኔታ በቀጥታ ያውቃል:: እዚህ ውስጥ፣ "የደርግና የመጨና" ዉዋታ የለበትም:: የመደቦች አሰላለፍ፣ የኃይል ሚዛን፣ የአብዮታችን መገፋት አለመገፋት፣ የአመፅ ህሊናዊ ሁኔታዎች መኖር አለመኖር ጥያቄ ነው ያለው::





እንግዲህ ከዚህ ሁሉ በኋላ፣ የኢማሌድህ አባል ድርጅቶችና በውስጡ የሚገኙት አንጃዎች ግለሰቦች፣ አሁንም የነገሮችን ምንነት ባይረዱ በመቅረታቸው፣ "ታዲያ ይህ ከሆነ፣ የትግል ስልት ለውጥ ለምን አስፈለገ?" የሚል ጥያቄ ያነሱ ይሆናል:: እናም ጥሬ ጥያቄ ነው:: እንደዚህም ከሆነ፣ ይህ ዱሉፋችን በ"ህብረት ድምፅ" ጋዜጣ ላይ ታትሞ እንዲወጣ፣ እንዲሰራጭና ሰፊው ሕዝብ እንዲገነዘብ በዲሞክራሲያዊ መንገዶች እንዲወያይበት ይደረግ እንላለን::

## 9. ሁለተኛ ማጠቃለያ

የኢማሌድህ ውሳኔ የደረሰን፣ ቀደም ሲል እንደተመለከተነው፣ ለውይይት እንዲያመች በማለት "የሰሀዱ 66 እትም" በሚዘጋጅበት ወቅት ነበር:: በና ገምተ፣ ይህ ቀደም ሲል የተፃፈው ጽሑፍ የዚህኛው ጽሑፍ ማጠቃለያ ሆኖ ለመቅረብ ይችላል:: ስለዚህም፣ በቀዳሚያ የተነበበዉን ያህል፣ የዚህም ጽሑፍ ማጠቃለያ ሆኖ ሊወሰድ ይችላል:: ቅደም ተከተሉ በዚህ ምክኒያት አይዛባም:: አንባቢያች ልናስታውስ የምንፈልገው ነገር ቢኖር፣ "ስሕዱ 66" ለውይይት መነሻ እንዲሆን ለኢማሌድህ የተፃፈ ወረቀት እንደ ነበር ነው:: የኢማሌድህ መልስ በገቢር የምናየዉ እንደሆነ፣ በተጨማሪ ማውሳት የአደባባዩን ምስጢር መደገም ብቻ ይሆናል:: በኢትዮጵያ ሕዝቦችና በታሪክ ፊት ተጠያቂ የሆኑትን ክፍሎች ታሪክ እየመሰከረች ናት::

## 10. መደምደሚያ

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ፣ "የመኢሶንን ከኢማሌድህ አባልነት መሰረዝ" ምክኒያት በማድረግ፣ "የህብረት ድምፅ" የተሰኘው ጋዜጣ የደረሰውን ጽሑፍ በሃቅና በግልጽ ለመተቸት ሞክረናል:: የመኢሶንን አስተሳሰቦችና አቋሞች በመልክ በመልካቸው ለማቅረብ ጥረት አድርገናል:: የኢማሌድህ ጽሑፍ ባነሳቸው ፍሬ ነገሮች ላይ ሁሉ፣ ሁኔታዎችን ለማስታወስና ለመግለጽ ሞክረናል:: በአንፃሩ እንደ ዕውነቱ ከሆነ፣ ይህንን ጽሑፋችንን እዚህ ላይ መደምደሙ በቂ ነው ብለን እናምናለን:: አያሌ ሊነገሩ የሚገባቸውን ጉዳዮች እንዳልተናገርን ይቀሩናል:: ዉነው ባሁኑ ወቅት ልናነሳቸው ስላልፈለግን ነው:: አንዳንዶቹን የተናገርን እንደሆነ ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው ያመዝናል ብለን ስለገመትን ነው:: ሌሎቹን ደግሞ ጽሑፉን ያለቀጥ ያረዝሙታል በማለት ትተናቸዋል:: እንደዚሁም፣ በመኢሶን በተነገሩት አንዳንድ ተረፍ አባባሎች ላይ ብንተች አልፈለግንም:: በአደባባይ የሚነገሩት የውሸትና የሚዛናዊ ገለፃዎችም ላይ ስንመለስባቸው አልፈለግንም:: እነዚህን የተውነው፣ ከፍሬ ነገሮች ያርቃሉ ብለን በማሰብ ነው::

ይሁንና የማይሳቱ ዕውነት ነገሮች ደግሞ አሉ::

ኢማሌድህ መኢሶንን የሚከራከረው የመኢሶንን አቋም በመተቸት አይደለም:: ኢማሌድህ መኢሶንን የሚከራከረው የኢጫህንና የኢሕአፓን /በተለይም የኢሕአፓን/ አቋሞች በመኢሶን ላይ በመለጠፍ ነው:: ይህም፣ የኢማሌድህን ክሥረት የሚያሳየን ጉዳይ ነው::

ሁለተኛ፣ ኢማሌድህ መኢሶንን "ፈርጣጭ"፣ "ቀኝ መንገደኛ"፣ "ከሓዲ"... ወዘተ. እያለ "ለማጋለጥ" ከፍተኛ ጥረቶችን አድርጓል:: ይሁንና፣ በአንደኛውም ጥያቄ ላይ ቢሆን፣ ይህ ነው የሚባል የክርክር ነጥብ እንኳ ሊያቀርብ አልቻለም:: ይህም እንደዚሁ፣ የኢማሌድህን ክስረት የሚያሳየን ጉዳይ ነው::

ሦስተኛ፣ የዲሞክራሲ መብቶች "በደርግ" /=አብዮታዊ ሰደድ/ ዘመን ከምንጊዜውም ይበልጥ በአሁኑ ወቅት ታፍነዋል:: የቀን አድርባይነት ከምንጊዜውም ይበልጥ ተስፋፍቷል:: በኢትዮጵያችን ውስጥ፣ በአብዮታችንና በሶሻሊዝም ስም አስጊና አደገኛ ሁኔታ እየተፈጠረ ነው:: የኢትዮጵያ ህዝቦች አንድነትና በሃገራዊ ነፃነታችን አሳሳቢ ከሆነ አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ወድቋል::

በዚህና በሌሎችም ጽሑፎች ውስጥ ደጋግመን እንደገለጽነው፣ የመኢሶን ምኞት:—

- አብዮታዊና ዲሞክራሲያዊ የሆነ ሃቀኛ የተራማጆች ህብረት እንዲመሠረት ነው::
- በእንደዚህ ዓይነቱ የጠነከረ ህብረት ላይ ዕውነተኛ የወዛደሩ ፓርቲ እንዲደራጅና እንዲመሠረት ነው::
- በእንደዚህ ዓይነቱ ፓርቲ አመራር ስር፣ ህዝባዊ አብዮታዊ ግንባርና ህዝባዊ አብዮታዊ ጦር እንዲመሠረት ነው::
- መንግሥታዊ ሥልጣን ወደ ሰፊው ህዝብ እጅ እንዲገባ ነው::
- አብዮታዊና ዲሞክራሲያዊ የሆነችን፣ ኩሩና በሃገራዊ ነፃነቷ የተከበረችን፣ ዕኩልነት፣ ዲሞክራሲ፣ ሰላም፣ ፍትህና በእኩልነት የሰፈነባትን፣ የህዝቦቿ አንድነትና እኩልነት የተመሠረተባትን ህዝባዊትና ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ለማየት ነው::

መኢሶን ከዚህ ውጭ አንዳችም ፍላጎት፣ አንዳችም ምኞት የለውም:: ዳኛው የሰፊው ህዝብ ነው::

- የታሠሩት አብዮታዊ ምሁራን፣ ታጋይ ወዛደሮች፣ የቀበሌ ሠራተኞች፣ መምህራን፣ ሴቶች፣ መለዮ ለባሾች፣ ወጣቶች፣ አገር ወዳዶች፣ ዴሞክራቶች ይፈቱ !

- በሕዝብ ላይ የሚደረገው የግድያ፣ የአፈና፣ የክትትል፣ የእሥራት... ዘመቻ ይቁም !

- ዴሞክራሲያዊ መብቶች አሁኑኑ ይታወቁ !

- ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፕሮግራም በሥራ ላይ ይዋል !

———————///———————

ይዘት


ገጽ

1. መግቢያ . . . . . . . . . . . 1
2. ዘመኑ ወሮች — ከ"ቀይታ" እስከ "ሡሳኒ" . . . . . 2
3. ስለልዩነት ጥያቄዎች . . . . . . . . . 5
   3.1. ፕሮግራምና የፖለቲካ አቋም ጥያቄ . . . . . . 6
   3.2. የብሄረሰቦች ጥያቄ . . . . . . . . 7
   3.3. የዴሞክራሲ መብቶች ጥያቄ . . . . . . . 9
4. ከጥር እስከ ነሐሴ 1969 — "ህብረትና" ፀረ ህብረት. . . . 11
   4.1. ከኢማሌድህ በፊት . . . . . . . . 12
   4.2. የመጀመሪያው ወቅት . . . . . . . . 13
   4.3. ሁለተኛው ወቅት . . . . . . . . 13
   4.4. ሶስተኛው ወቅት . . . . . . . . 16
   4.5. የህብረቱ የመተዳደሪያ ደንብ ጥያቄ . . . . . 18
5. የመጀመሪያ ማጠቃለያ . . . . . . . . . 18
6. የትግል ስልት ለውጥ ለምን? . . . . . . . . 20
7. ከትግል ስልት ለውጥ በኋላ . . . . . . . . 25
8. አንዳንድ ማስታወሻዎች . . . . . . . . . 26
   8.1. የብሄረሰቦች ጥያቄ . . . . . . . . 26
   8.2. የዴሞክራሲ መብቶች ጥያቄ . . . . . . . 27
   8.3. ይህች "ዴሞክራሲ አገዛዝ የመንግሥት ገጸታ ነው" የሚሏት ነገር . 27
   8.4. የመንግሥት ሥልጣን ጥያቄ . . . . . . . 31
   8.5. የአብዮታዊ ህግ ጥያቄ . . . . . . . 32
9. ሁለተኛ ማጠቃለያ . . . . . . . . . 33
10. መደምደሚያ . . . . . . . . . . 33


———————